3227

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት / Attitude /

ታሪኩ ፋንታዬ

ግንቦት 1988 ዓ.ም.

# የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት (Attitude)


አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድህረ-ምረቃ ት/ቤት



በቋንቋዎች ተቋም

አማርኛን በማስተማር ትምህርት

ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ቴሲስ



በ

ታሪኩ ፋንታዬ



ግንቦት 26/1988 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

# የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት (Attitude)

በ

ታሪኩ ፋንታዬ

የቋንቋ ጥናት ተቋም

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | |
|---|---|
| ዮናስ፡ አድማሱ | Yonas Admassu |
| አማካሪ | ፊርማ |
| ሬናቴ፡ ሪክተር | Renate Richter |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| [illegible] | |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| | |
| ፈታኝ | ፊርማ |

# ማውጫ

| አርእስት | ገጽ |
|---|---|


አጠቃሎ .............................. i

ምስጋና .............................. ii

ምዕራፍ

1. መግቢያ

1.1 የጥናቱ መነሻ ሐሳብ .............................. 1

1.2 የጥናቱ አስፈላጊነት .............................. 2

1.3 የጥናቱ ዓላማ .............................. 3

1.4 የጥናቱ ወሰን .............................. 3

1.5 የቃላትና የሐረጎች ትርጉም .............................. 4

1.6 የጥናቱ አቀነባበር .............................. 5

2. የተዛማጅ ጽሑፍ ክለሳ

2.1 አማርኛ .............................. 7

2.1.1. የአማርኛ ዕድገት .............................. 7

2.1.2. የአማርኛ ተናጋሪዎች .............................. 9

2.1.3. አማርኛ በት/ቤት .............................. 9

2.1.4. አማርኛ አሁን ያለበት ሁኔታ .............................. 9

2.1.5. ፖለቲካዊ ገፅታዎች .............................. 11

2.2 የአመለካከት አጠቃላይ ባሕርያት .............................. 12

2.3 የተማሪው አዎንታዊና አሉታዊ አመለካከት አፈጣጠር ..... 15

2.4 ቋንቋና የቋንቋ ትምህርት አስመልክቶ በተማሪው አመለካከት ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ነገሮች

2.4.1 ወላጆች ኅብረተሰቡና እኩዮች .............................. 18

2.4.2 መምህራን .............................. 20

2.4.3 መማሪያ መጻሕፍት .............................. 23

2.4.4 ት/ቤቶች፣ መማሪያ ክፍሎች፣ ድጋፍ ሰጪ ነገሮችና

# ማ ው ጫ

ርእሰት | ገጽ

ምዕራፍ
2.5 አማርኛንና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አስመልክቶ
የተደረጉ የአመለካከት ጥናቶች
2.5.1. አንደርሰን አንደርሰ /1967/ ............ 27
2.5.2. ፀሐዬ ተፈራ /1977/ ................ 28
2.5.3. ዘርሃኑ ማርያም /1976 ዓ.ም/ ........... 30
2.5.4. ወርቁ በሻዳ /1982 ዓ.ም/ ............ 32

3 የጥናቱ ዘዴ
3.1 ናሙናዎችና መገለጫቸው .................... 35
3.2 የጥናቱ ተሳታፊዎች ...................... 37
3.3 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች ................... 39
3.4 የመጠይቁ ስርጭት ....................... 41
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ .................... 42
3.6 ሠንጠረዣዊ መገለጫዎች .................... 43

4 ውጤቶችና ማብራሪያዎች
4.1 የመላሾች አጠቃላይ ሁኔታ ................... 44
4.2 የመረጃዎች ስሌታዊ አሰራር .................. 48
4.3 ከያንዳንዱ ጥያቄ የተገኘ ምላሽ
4.3.1. የተማሪዎች ገላዊ አመለካከት ............ 49
4.3.2. የወላጆች፣ የኅብረተሰቡና የእኩዮች አመለካከት.. 62
4.3.3. የአማርኛ ቋንቋ መምህር ጠባይ፣ ችሎታና
አመለካከት ....................... 66
4.3.4. የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ሁኔታ........... 70
4.3.5. ት/ቤቶችን፣ ማማሪያ ክፍሎችን፣ ድጋፍ ሰጪ
ነገሮችንና የማስተማር ዘዴዎችን በተመለከተ.... 74
4.4 የምላሾች ንፅፅር ......................... 81
........ 84

# ማ ው ጫ


| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ምዕራፍ | |
| 4.6 ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች ንፅፅር... | 88 |
| 4.7 የምልከታ ሪፖርት ...................... | 90 |
| 4.8 የምልከታ ውጤትና የተማሪዎች ምላሽ ንፅፅር ...... | 90 |
| 5 ማጠቃለያ፣ ግኝትና አስተያየት | |
| 5.1 ማጠቃለያ ........................... | 92 |
| 5.2 ግኝት ............................ | 94 |
| 5.3 አስተያየት ......................... | 96 |
| ዋቢ መጻሕፍት ............................. | 100 |
| ሙዳየ ቃላት ............................. | 108 |
| አባሪዎች ............................... | 110 |

# የሠንጠረዦች ዝርዝር


ሠንጠረዥ — ገጽ

1. ከየዞኑ የተመረጡ ት/ቤቶች .................... 37
2. በት/ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎችና ለናሙና የተመረጡ ተማሪዎች .................... 38
3. በት/ቤቶች የሚገኙ መምህራንና ለናሙና የተመረጡ መምህራን .................... 38
4. የተማሪዎች ጾታ፣ ዕድሜ፣ ሃይማኖት ብሔረሰብና የአፍ መፍቻ ቋንቋ .................... 45
5. የቤተሰብ ወር ሃዊ ገቢ .................... 46
6. የአባቶችና የእናቶች የትምህርት ደረጃና የሥራ ሁኔታ... 48
7. ለ"ግ.11" ጥያቄ የድጋፍ ምክንያቶች ............ 56
8. ለ"ግ.11" ጥያቄ የተቃውሞ ምክንያቶች............ 57
9. ለ"ግ.12" ጥያቄ የድጋፍ ምክንያቶች ............ 59
10. ለ"ግ.12" ጥያቄ የድጋፍ ምክንያቶች ............ 59
11. ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተጠቆሙ ዘዴዎች.......... 79
12. አማርኛ ቋንቋን ሳለመውደዱ የቀረቡ ምክንያቶች ...... 80
13. የተሳታፊዎች የርስበርስ ተጣማሪነት.............. 84

## አጠቃሎ / abstract /

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅና፣ አመለካከታቸው አዎንታዊ ከሆነ፣ አዎንታዊነቱ ይበልጥ ጠንክሮ ዘላቂ እንዲሆን፣ አመለካከታቸው አሉታዊ ከሆነ ለአሉታዊነት ምክንያት የሆኑ ነገሮች እንዲታወቁና እንዲወገዱ የመፍትሔ ሐሳብ ለማቅረብ ነው::

ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረግ ልዩ ልዩ ዝዘጋጁ ጽሑፎች ተከልሰዋል፣ ለአራት መቶ ሃያ ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ተበትኖ መረጃዎች ተሰብስበዋል ፣ ከአሥራ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር ቃለ መጠይቃዊ ውይይት ተደርጎ ጠቃሚ ሐሳቦች ተገኝተዋል:: ከተማሪዎችና ከመምህራን የተገኙትን መረጃዎች በዓይን እይታ ለማረጋገጥ የት/ቤቶች አጠቃላይ ጉብኝትና የክፍል ትምህርት ምልከታ ተከናውኗል:: ከነዚህ ሁሉ ተግባራት በኋላ የሚከተሉት ውጤቶች ተመዝግበዋል::

አብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አማርኛንና የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት ይወዳሉ:: በተለይ የልብለድ ፣ የቅኔና የምሳሌያዊ አነጋገር ትምህርቶች ይበልጥ ያስደስቷቸዋል:: በሌላም በኩል በአዲስ አበባ ውስጥ የሚኖር አብዛኛው ኅብረተሰብና የተማሩ ወላጆች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ጥሩ አመለካከት ያላቸው ቢሆኑ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንም በአብዛኛው ተማሪ ዘንድ የተወደዱ ናቸው:: በአንጻሩ ደግሞ መማሪያ መጻሕፍትን ፣ ድጋፍ ሰጪ ነገሮችንና መማሪያ ክፍሎችን በተመለከተ የተወሰኑ ድክመቶች ታይተዋል:: በጥቅሉ ግን የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አዎንታዊ አመለካከት አላቸው::

## ምስጋና / acknowledgement /

ይህ ጥናት በሚደረግበት ጊዜ ሰለቸኝ ፤ ደከመኝ ባይሉ ወርቃማ ጊዜያቸውን በመሰዋት ሥራዬን ሲያስተካክሉልኝና ሲረዱኝ የቆዩትን አማካሪዬን ዶክተር ዮናስ አድማሴን ከልብ አመሰግናለሁ:: የሳቸው ዕርዳታ ባይታከልበት ኖሮ የኔ ሥራ ብቻውን ከዚህ ደረጃ ሊደርስ ባልቻለ ነበር::

ገና ከመጀመሪያው የርዕስ ምርጫ ጀምሮ ጥናቱ አስከተጠናቀቀ ድረስ በየጊዜው ሐሳብ በመስጠትና ቴክኒካዊ ዕርዳታ በማድረግ ሲረዱኝ የቆዩትን ዶክተር ታደለ አደሙን ፤ ዶክተር ደጀኔ ለታን ፤ ዶክተር ይመር ክፍሌን ፤ አቶ ደባለኝ ጫልቺሳን ፤ አቶ ቶላ ገመዳንና አቶ መሐመድ አሰንን በጣም አመሰግናለሁ::

በሥራዬ ላይ መሰልቸትና ድካም እንዳይሰማኝ ሁሌም ከጎኔ ሆና ስታበረታታኝ የነበረችውን ባለቤቴን ወይዘሮ ቀለሟ መንገሻን ፤ ረቂቅ ጽሑፎቼን በመገልበጥ ያገዘኙን ወንድም ፈዬ ሐይሉንና በመላላክ ብዙ የረዱኝን ልጄን ፍጹም ታሪኩን ላመሰግን አወዳለሁ::

በመጨረሻም ጥናታዊ ጽሑፉን ሌት ተቀን ተይባ ባጭር ጊዜ ውስጥ በማጠናቀቅ ለዚህ ያበቃችውን አህቴን ወይዘሪት ንጋት አሸቴንና ከሷ ጋር በመሆን የረዳችኝን ወይዘሮ ፈለቀች ዓለሙን ከልብ አመሰግናለሁ::

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ መነሻ ሐሳብ

አንድ ተማሪ በሚማረው የቋንቋ ትምህርትና በቋንቋውም ላይ ቀና
አመለካከት፣ እንዲሁም የመማር ፍላጎት እንዲኖረው ያስፈልጋል:: ታይ
ኖማን/1959/፤ ብሩምፊት /1966/፤ እና ቅቢን /1990/፣
ለቋንቋው ትምህርትና ልምድ ውስጥ ወሳኝ ነገሮች የመማር ፍላጎትና
አዎንታዊ አመለካከት ናቸው ይላሉ:: አንድ የቋንቋ ተማሪ አመለካከቱ
አሉታዊ ከሆነ ቋንቋውን ከልብ አይማርም:: እንዲያውም ከራሱ አለመማር
አልፎ ለሌሎች ወይም ለሚማሩትም ተማሪዎች እንቅፋት ሊሆን ይችላል ::
በአንጻሩ ደግሞ አዎንታዊ አመለካከት ያለው ተማሪ በንቃት ይማራል፤ ጥሩ
ውጤትም ይኖረዋል:: በመሆኑም የቋንቋ ተማሪዎች ሁሉ ስለሚማሩት ቋን
ቋና በቋንቋው ትምህርት ላይ አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው
ያስፈልጋል:: ስለዚህ የተማሪዎችን አመለካከት አሉታዊ ሊያደርጉ የሚች
ሉትን ነገሮች አጥንቶ የመፍትሄ ሃሳብ ማቅረብ አስፈላጊ ነው:: ይህ
ጥናት በተለይ ከላይ የጠቀስናቸው ምሁራን፣ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ
ለማዘጋጀትና ሌሎች ትምህርታዊ ግብአቶችን ለማደራጀት በቀዳሚያ ተማሪዎ
ችና ሌሎች የሚመለከታቸው ሁሉ አመለካከታቸው መጠናት እንዳለበት
ይናገራሉ:: ይሁንና የአገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ስንመለከት የተማሪዎች
ፍላጎትና አመለካከት ሳይጠና የአማርኛ ቋንቋ መርጠ ትምህርቶችና መማሪያ
መጻሕፍት እስካሁን ድረስ ሲዘጋጁ ቆይተዋል:: ይህ ደግሞ የቋንቋው
ትምህርት የሚፈለገውን ሲሳካ እንዳይመጣ እንቅፋት ሊሆን ይችላል ::
ማውንት ፍርድና ማከይ /1978/፣ ትክክለኛ የቋንቋ ኮርስ ለማዘጋጀት
ኮርሱ የሚመለከታቸውን ሰዎች በግልጽ ማነጋገር ተገቢ እንደሆነ ይጠቁ
ሙና ይህ ካልሆነ ግን ውጤቱ ብላሽ እንደሚሆን ይናገራሉ:: እንደገና
ፈርግሰን /1971 : 5/ ም በኢትዮጵያና በሌሎችም ቦታዎች በዙ ኀርገ
ራዎች የሚከሰቱት የተመሰረተ ቶለትን ሕዝብ አመለካከት ግምት ውስጥ ስለማ
ያስገቡ ነው በማለት በኢትዮጵያ-የአመለካከት ጥናት ትኩረት እንዳልተ
ሰጠው ተናገሯል:: የአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት አዘጋጅ ባለሙ
ያዎች ከዘጠነኛ እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ባሉት መርጠ —

ትምህርቶች / 1984 / መግቢያ ላይ "የመርጃ ትምህርት አዘገጃጀት በጥናት ላይ ያልተመሰረተ መሆኑ ገለጽ ነው" በማለት ያቀረቡት ሃሳብ የፈርጓሰን ሃሳብ የሚደግፍ ነው::

ከላይ እንደተጠቀሰው በአገራችን የአመለካከት ጥናት /attitude survey / ከትምህርት መሣሪያዎች ዝግጅት በፊት አለመደረጉ አንደኛው ትልቅ ጉድለት ሲሆን መሣሪያዎቹ ሥራ ላይ ከዋሉ በኋላም ተማሪዎች ስለመሣሪያዎቹ ያላቸውን አመለካከት አጥንቶ ማሻሻያዎችን ለማቅረብ አለመሞከሩ ደግሞ ሁለተኛው ጉድለት ነው::

ስለዚህ ለወደፊቱ ያገለገለ ዘንድ የተማሪዎችን ፍላጎትና አመለካከት አጥንቶ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ማቅረብ ተገቢ ይሆናል::

## 1.2 የጥናቱ አስፈላጊነት

ከላይ ስለ ጥናቱ መነሻ ሃሳብ ስንገልጽ በአገራችን የተማሪዎች ፍላጎትና አመለካከት ሳይጠና የአማርኛ ቋንቋ መርጃ ትምህርትና መማሪያ መጻሕፍት ይዘጋጃሉ ብለናል:: የዚህ ጥናት ውጤት ደግሞ፤ የተማሪዎችን ፍላጎትና አመለካከት፤በአማርኛ ትምህርት ላይ የሚታዩትን ችግሮችና ተማሪዎች ከመምህራን የሚጠብቁትን ሁሉ ማንፀባረቅ እስከቻለ ድረስ የሚመለከታቸው ወገኖች ሊጠቀሙበት ይችላሉ:: በመሠረቱ በአንድ አገር ውስጥ የሚደረጉ ጥናቶች በተገቢ ሰዎች እጅ ገብተው በአገባቡ ሥራ ላይ መዋል ይኖርባቸዋል:: በዚህ ረገድ ካርል /1965: 275 /"የቋንቋ ጥናት ውጤት ተጠቃሚዎች የመምህራን አሠልጣኞች፤ የትምህርት ፖሊሲ አውጪዎችና የትምህርት መማሪያ አዘጋጆች ናቸው" ይላል::

በካርል ሃሳብ መሠረት የዚህ ጥናት ውጤት ተገባር ቀደም ተጠቃሚ ትምህርት ሚኒስቴር ሲሆን በሦስት የተለያዩ መንገዶች ሊጠቀምበት ይችላል:: እነሱም:-

- የአማርኛ መርጃ ትምህርቶችና መማሪያ መጻሕፍት ከተማሪዎች ፍላጎት አኳያ እንዲሻሻሉ በማድረግ፤
- በመምህራን ሥልጠና ላይ ከተማሪዎች አመለካከት አኳያ ጠቃሚ የሆኑ ሥነ ልቦናዊ ሁኔታዎች እንዲተኮርባቸው በማድረግ፤
- ት/ቤቶች፣መማሪያ ክፍሎች፤እንዲሁም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጋዥ ነገሮች ከተማሪዎች አመለካከትና ፍላጎት አኳያ እንዲ

ሌሎቹ የዚህ ጥናት ውጤት ተጠቃሚዎች ደግሞ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የሚያሠለጥኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ሲሆኑ የጥናቱን ውጤትና የአጥኚውን አስተያየቶች በትምህርታቸው ውስጥ በማካተት የተሻሉ መምህራንን ሊያፈሩ ይችላሉ::

ስለዚህ ጥናቱ ከላይ የተዘረዘሩትን ጠቀሜታዎች ሁሉ የሚያስገኝ በመሆኑ በዚህ ወቅት መከናወኑ በጣም አስፈላጊ ነው::

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዝርዝር ዓላማዎች:-

- አማርኛ ቋንቋና የቋንቋው ትምህርት በተማሪዎች ዘንድ ተቀባይነቱ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ፤
- ወላጆች፣ኅብረተሰቡና የተማሪው እኩዮች ስለ አማርኛና ስለተማሪው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት ለመረዳት፤
- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በችሎታቸው፣በትምህርት አቀራረባቸውና በጠባያቸው ተወዳጅ መሆን አለመሆናቸውን ለመገንዘብ፤
- የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ከተማሪዎች ፍላጎት አኳያ ምን ያህል ተቀባይነት እንዳላቸውና እንደሌላቸው ለመለየት፤
- ት/ቤቶች፣መማሪያ ክፍሎች፣ድጋፍሰጪ ነገሮችና የማስተማር ዘዴዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ምቹ መሆን አለመሆናቸውን ለመፈተሽ ሲሆን አጠቃላይ ዓላማው:-

ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸውን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከቶችን በመረጃ ማረጋገጥና አሉታዊ የሆኑ ጉዳዮች ወደ አዎንታዊነት የሚቀየሩበትን፣አዎንታዊ የሆኑት ጉዳዮች ደግሞ ይበልጥ የሚጠናከሩበትን መንገድ መጠቆም ይሆናል::

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገኙት የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ላይ ሲሆን የግልና የኮሚዩኒቲ ት/ቤቶችን አይጨምርም:: ከመንግሥት ት/ቤቶችም የቴክኒክና ሙያ ት/ቤቶች በጥናቱ አልታቀፉም::

በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ውስጥ ያሉት የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣የቴክኒክና ሙያ ት/ቤቶችን ሳይጨምር ሃያ ስድስት ናቸው::

ታሪያ እነዚህን ሁሉ ት/ቤቶች በጥናቱ ማካተት ከጊዜ፣ከገንዘብና ከአቅም አኳያ አስቸጋሪ በለሚሆን ለናሙና ያህል በክልሉ ከሚገኙት ዞኖች አንዳንዱ በመምረጥ ስድስት ት/ቤቶች በጥናቱ እንዲታቀፉ ተደርጓል::

በተመረጡት ት/ቤቶች ውስጥ ካሉት ተማሪዎችም የአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ለናሙና ተመርጠው መጠይቁን እንዲሞሉ የተደረጉ ሲሆን፣ ቃለ መጠይቅ ወረቀት እንዲሰጡ የተመረጡት ደግሞ በት/ቤቶቹ የሚገኙት የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተጠሪዎችና የአሥራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው:: የናሙና አመራረጥንና አጠቃላይ መግለጫን በተለከተ በምዕራፍ ሶስት ውስጥ በዝርዝር ቀርቧል::

## 1.5· የቃላትና የሐረጎች ትርጉም / በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በገባበት ሁኔታ/

1. አመለካከት= አንዱ ሰው ስለአንዱ ነገር የሚኖረው ቀና ወይም ቀና ያልሆነ ውስጣዊ አስተሳሰብ ነው::
2. ገሃዊ አመለካከት= አንዱ ሰው በአንዱ ወቅት የሚኖረው የራሱ ብቻ የሆነ ውስጣዊ አስተሳሰብ ነው::
3. አዎንታዊ አመለካከት= አንዱን ነገር የመውደድ፣ የመቀበል፣ የመደገፍ፣ ወዘተ. ዝንባሌ ነው::
4. አሉታዊ አመለካከት= አንዱን ነገር የመቃወም፣ የመጥላት፣ የመንቀፍ፣ ወዘተ. ዝንባሌ ነው::
5. ኅብረተሰብ = ተማሪው በሚመላለስበት ክልል ውስጥ የሚገኙ የቅርብም ሆነ የሩቅ ነዋሪ ሰዎች ናቸው:: /ቃሉ ሰፋ ተደርጎ ሲታይ ለማዱ፣ወገን፣እምነትና የመሳሰሉትንም ያቅፋል/
6. እኩዮች = ከተማሪው ጋር በዕድሜ የሚመጣጠኑና አብረውት የሚመላለሱ የክፍል ውስጥ ወይም ከክፍል ውጭ ያሉ ጓደኞች ናቸው::
7. ታሳሚ ቋንቋ= ተማሪው እንዲማረውና እንዲያውቀው የሚፈለግ ቋንቋ ነው::
8. ዱጋፍ ሰጨ= በዋናው የትምህርት መሣሪያ ላይ ተጨማሪ ሆኖ የሚቀርብ አጋዥ ነው::

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ አጥኚው ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ የተረጎማቸው

ሙዳየ–ቃላት የተዘጋጀ ሲሆን ከዋቢ መጻሕፍት ቀጥሎ ይገኛል፡፡

## 1.6. የጥናቱ አቀነባበር

ይህ ጥናት በአምስት ምዕራፎች የተቀነባበረ ነው፡፡

እነሱም፡-

ምዕራፍ አንድ /መግቢያ/ በዚህ ሥር ስድስት ንዑሳን ርዕሶች የታቀፉ ሲሆን በቀደም ተከተል የጥናቱ መነሻ ሐሳቦች፣ አስፈላጊነት /ጠቀሜታ/፣ ዓላማ፣ወሰን፣የቃላትና የሐረጋት ትርጓሜ፣እንዲሁም የጥናቱ አቀነባበር ናቸው፡፡

ምዕራፍ ሁለት /የተዛማጅ ጽሑፍ ክለሳ/ ይህ ክፍል አምስት ዐበይ ጉዳዮችን ይዟል፡፡ ከነዚህም፡-

- አንደኛው፣ አማርኛ ቋንቋን የሚመለከት ሲሆን፣ስለአማርኛ ቋንቋ ዕድገት፣ስለተናጋሪዎቹ፣አማርኛ መቼ በትምህርት ቤት መሰጠት እንደተጀመረ፣አሁን ያለበትን ሁኔታና ፖለቲካዊ ገጽታዎችን ያቀርባል፡፡
- ሁለተኛው የአመለካከትን ባሕርይ የሚያሳይ ሲሆን ከትርጓሜ ጀምሮ አዎንታዊና አሉታዊ አመለካከቶች በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚያድጉና እንደሚንፀባረቁ ያብራራል፡፡
- ሶስተኛው በተማሪ ላይ አዎንታዊና አሉታዊ ሐሳቦች እንዴት ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ይገልጻል፡፡
- አራተኛው ቋንቋና የቋንቋ ትምህርት አስመልክቶ በተማሪው አመለካከት ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ነገሮችን የሚያቀርብ ሲሆን በርካታ ንዑሳን ክፍሎች አሉት፤ እነሱም ወላጆች፣ኅብረተሰብ፣እኩዮች፣መምህራን፣መማሪያ መጻሕፍት፣ትምህርት ቤቶች፣መማሪያ ክፍሎች፣ ዉጋና ሰዉ ነገሮችና የማስተማር ዘዴዎችና ናቸው፡፡
- አምስተኛው በአማርኛ ቋንቋ ዙሪያ የተደረጉ የአመለካከት ጥናቶችን የሚያሳይ ሲሆን የአንገደርስን /1967/፣ የፀሐዬ/1977/፣ የበርሃኑ /1976 ዓ.ም./፣ የወርቁ /1982 ዓ.ም/ ጥናቶች አጠር ባለመልክ ቀርበዋል፡፡

ምዕራፍ ሶስት /የጥናቱ ዘዴ/ ይህ ክፍል የናሙና መገለጫዎችን፣ ተሳታፊዎችን፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን፣ የመጠይቁ አስረጂነትን፣ የመረጃ

<u>ምዕራፍ አራት/ የጥናቱ ውጤቶችና ማብራሪያዎች</u>/ ይህ ምዕራፍ በርካታ ንዑሳን ክፍሎች ይዟል:: እነሱም፣

- የመላሾች አጠቃላይ ሁኔታ/ ፆታ፣ ዕድሜ፣ ሃይማኖት፣ብሔረሰብ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ የቤተሰብ የገቢ ሁኔታ፣ የተማሪዎች አባቶችና እናቶች የትምህርትና የሥራ ሁኔታ/ ተብራርቷል፣
- የመረጃዎች አቀነባበርና የትንታኔ ስልት ተገልጿል፣
- ከያንዳንዱ ጥያቄ የተገኙ ምላሾች እየተተነተኑ ቀርበዋል፣
- የምላሾች ንጽጽር ተካሂዷል/ስታቲስቲካዊ ስሌቶች ተሠርተው አንዱ ጉዳይ ከሌላው ጉዳይ ጋር እንዲነፃፀር ተደርጓል/፣
- ቃለመጠይቃዊ መልሶች በዝርዝር ቀርበዋል፣
- የመምህራንና የተማሪዎች ምላሾች ተነፃፅረው ቀርበዋል፣
- የምልከታ ሪፖርት ቀርቧል፣
- የምልከታ ውጤትና የተማሪዎች ምላሽ ተነፃፅሯል::

<u>ምዕራፍ አምስት/ ማጠቃለያ ግኝትና አስተያየት/</u> ይህ ክፍል ሶስት ዐበይ ጉዳዮችን ይዟል:: እነሱም፣ማጠቃለያ፣ግኝትና አስተያየት ሲሆኑ በተገቢው መልክ ተብራርተው ቀርበዋል::

የጥናቱ ዋና ክፍል በአስተያየት ከተደመደመ በኋላ ሌሎች ሁለት ክፍሎች አሉ:: የመጀመሪያው ክፍል አጥኚው የተጠቀመባቸውን ዋቢ መጻሕፍት የሚያሳይ ክፍል ሲሆን ተከታዩ ክፍል ልዩ ልዩ አባሪዎችን በቅደም ተከተል የሚያቀርብ ነው:: አባሪዎች ሁሉ በዋናው ጽሑፍ ውስጥ ቦታ ያላቸውና እየተጠቀሱ የገቡ ናቸው::

የዚህ ጽሑፍ ሐሳቦች በሚሰባሰቡበትና በሚቀነባበሩበት ጊዜ ሁለት ዓይነት የዘመን አቆጣጠር ስልቶች ሥራ ላይ ውለዋል:: የአውሮፓውያንና የኢትዮጵያውያን አቆጣጠር:: ታዲያ በጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሰው ዘመን "ዓ.ም." በሚለው ምህፃረ ቃል ከታጀበ የኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር ሲሆን "ዓ.ም." በሚለው ምህፃረ ቃል ያልታጀበ ሁሉ እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር የተወሰደ መሆኑን አንባቢያን ልብ ሊሉ ይገባል:: በተጨማሪም በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ያሉት ጥቅሶች ሁሉ በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ካልተገለፁ በስተቀር አጥኚው ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ የተረጎማቸው ናቸው::

## ምዕራፍ ሁለት ፤

### የተዛማጅ ጽሑፍ ክለሳ

### 2.1 አማርኛ

አማርኛ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ኢትዮሴማዊ ቋንቋዎች አንዱ ሲሆን በሴም ቋንቋነቱ ከዐረብኛ ቀጥሎ ብዙ ተናጋሪዎች ያሉት ቋንቋ ነው:: ቋንቋው ከረጅም ዓመታት በፊት የኢትዮጵያ ኦፊሴላዊ ቋንቋ ሆኖ ማገልገል የጀመረና ዛሬም የአገሪቱ ማዕከላዊ መንግሥት የሥራ ቋንቋ ሆኖ በማገልገል ላይ የሚገኝ ነው:: ይህ ቋንቋ እንዴት እንዳደገ፣ ተናጋሪዎቹ እነማን እንደሆኑ፣ በትምህርት ቤት መሰጠት የተጀመረው መቼ እንደሆነ፣ አሁን ያለበትን ሁኔታና ፖለቲካዊ ገፅታዎቹን አጠር አጠር ባለ መልክ እንመለከታለን::

#### 2.1.1 የአማርኛ ዕድገት

አማርኛ መነገር የተጀመረበትን ጊዜ በትክክለ ወና ገር ባይቻልም፣ሴማዊ ዝርያዎቹ ሁሉ የዛሬ ሶስት ሺህ ዓመታት ገደማ በሰሜን በኩል ወደ ኢትዮጵያ የገቡ መሆኑን ሀብተማርያም ማርቆስ /1972ዓ.ም/ ይገልጻል:: አማ- ርኛ ከአሥራ ሶስተኛው ክፍለ ዘመን በፊት የነበረው ታሪክ ከመሳምት ያሳለፈ ሲሆን፣በአፄ ይኩኖአምላክ ዘመነ መንግሥት /1253/ በስፋት ማገልገል የጀመረና ለሲኖ-መንግሥታዊ ደረጃ የነበረው መሆኑን የሚገልፁ ታሪካዊ መረጃዎች ተገኝተዋል /አምሳሉ አክሊሉ 1976 ዓ.ም./::

በአሥራ አራተኛውና በአሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን በተለይም በአፄ አምደጽዮንና በይስሐቅ ዘመን ቋንቋው ዕድገቱን አፋጥኖ ወደ ጽሑፍ ደረጃ ለሸጋገር ችሏል:: ለዚህ ማስረጃው በተጠቀሱት ዘመናት ስለሁለቱ ነገሥታት በገጣሚ የቀረቡት ጽሑፎችና ቸውፏኝ ገጥሞቹ እነ ጁስ አደማሱ ባዘጋጁት መጽሐፍ /1966ዓ.ም./ በገጽ 118 እና 119 ላይ ይገኛሉ::

በዘመናችን ያለውን አማርኛ ካለፉት ዘመናት ጋር ስናነፃፀር ብዙ ልዩነቶች ይታዩቸዋል:: የበፊት

ሲሆን የዘመኑ አማርኛ ገን ራቅ ብሏል:: ለዚህ እንኳ ምክንያት አማርኛ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት የኩሽ ቋንቋዎች በርካታ ቃላትንና የአገላለጽ ሥርዓቶችን በመውሰዱ መሆኑን ሌስላዉ /1945/ ይገልጻል:: ሌስላዉ ምክንያት አማርኛ የነገሥታትና የትምህርት ቋንቋ በመሆን ያገኘውን አጋጣሚ በመጠቀም ከተለያዩ የውጭ ቋንቋዎች የተለያዩ ቃላትን በተውሶ በማስገባቱና ከራሱ ጋር በማቀላቀሉ ሲሆን ውሰቱን በተመለከተ አበርሃም ደምዝ /1963/ በሰፊት ይገልጻል:: ዘመን አለፍ ዘመን፣ ትውልድ አለፍ ትውልድ ሲተካ ቋንቋ ቀስ በቀስ መልኩን እየቀየረ ይሄዳል:: እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተደምረው አማርኛ ከበፊቱ እንዲቀየርና አድገ ብሎ እንዲገኝ አድርገውታል:: ለአማርኛ ቋንቋ ዕድገት አስተዋጽኦ ያደረጉት ነገሮች በርካታ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

- የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሥልጣን ላይ መውጣት /እንገደርሰን 1971፤
- የከተሞች መስፋፋት /ማክናብ 1989፤ ኩፐር 1976/፣ ይህ ማለት የተለያዩ ብሔረሰቦች በአንድ አካባቢ ተሰባስበው መኖር ሲጀምሩ አማርኛ የጋራ መግባቢያ /Lingua Franca/ ሆኖ ማገልገል በመጀመሩ እያደገ ሄደ::
- የመንግሥትና የሚሽን ትምህርት ቤቶች መስፋፋት፣ ቀደም ብለው የተቋቋሙት ትምህርት ቤቶች አማርኛን እንደ አንዱ የትምህርት ዓይነት ሲሰጡ ቆይተው ወዲያውኑ ከነፃነት በኋላ የአንደኛና የሁለተኛ ክፍሎች የትምህርት ቋንቋ፣ትንሽ ቆይቶ በመላው ኢትዮጵያ የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ አድርገው በመጠቀማቸው ለአማርኛ ዕድገት በጣም ረድተዋል፤ በተለይ የተለያዩ ሚሽነሪዎች በርካታ ትምህርት ቤቶችን በገጠር በማስፋፋታቸው አማርኛ ለመማርና ለመናገር አጋጣሚ ያልነበራቸው ብዙ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ቋንቋውን ለመማርና ለመናገር ችለዋል:: በዚህ ሁኔታ አማርኛ በተወላጅነት ከሚናገሩት ሕዝቦች ውጭ ወደሁኑት ብሔር ብሔረሰቦች ዘለቆ የመግባትና የመስፋፋት ዕድል አግኝቷል: /ቤንደር 1976፤ ደሴ መሉዓለም 1972 ዓ.ም.፤ ማክናብ 1989/:: ከሁሉም በላይ ለረጅም ጊዜ ኦፊሴላዊ ቋንቋ ሆኖ በመገናኛ ብዙሃን፣በማኅበራዊ አገልግሎት፣

በመገኘቱ ለአማርኛ ቋንቋ ዕድገት የረዳ ትልቅ ጉዳይ ነው::

## 2.1.2 የአማርኛ ተናጋሪዎች፣

አማርኛ ከብሔረሰቡ ማደግና መስፋፋት፣ብሎም ወደ ሥልጣን መምጣት ጋር ቀስ በቀስ ወደ ደቡብና ወደሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ሁሉ እየተስፋፋ ሄዶ የአገሪቱ ማኅበራዊ ቋንቋ ሆኗል:: ይህንን አስመልክቶ የቋንቋ ጥናት እንስቲትዩት በ1975 ባወጣው እትም ላይ "የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ማነው?" ለሚለው ጥያቄ "አማራዎች የሚሉ መልስ ብቻ እንደ ማናገኝና ከአማራው ክልል ውጭ በተለያዩ ከተሞች ውስጥ የሚኖሩ ብሔር ብሔረሰቦችና የተማሩት ወገኖች ሁሉ የሚገለገሉበት የኢትዮጵያውያን ቋንቋ እንደሆነ አቅርቧል::

በኢትዮጵያ ውስጥ አማርኛን በአፍ መፍቻነት የሚናገሩት 55.4% ሲሆኑ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚናገሩት 44.6%. መሆናቸውን ማከናብ /1989/ ተገልጻለን::

## 2.1.3 አማርኛ በትምህርት ቤት

አማርኛ በትምህርት ቤት ውስጥ የጎላ እንቅስቃሴ ማድረግ የጀመረው በ1908 የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ከተከፈተ ወዲህ ነው:: በዚህ ትምህርት ቤት አማርኛ እንደአንዱ የትምህርት ዓይነት መሰጠት የ ጀመረ ሲሆን፣ከዚያ በኋላ የተቋቋሙት የመንግሥትም ሆኑ የሚሽን ትምህርት ቤቶች ሁሉ አማርኛን እንደአንዱ የትምህርት ዓይነት ይሰጡ ጀመር /ቤንደር 1976/

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት ከተጀመረ ጀምሮ እስከ ኢጣሊያ ወረራ ድረስ ፈረንሳይኛ የትምህርት ቋንቋ ሆኖ ከቆየ በኋላ፣ከ1941 ጀምሮ እንግሊዝኛ ቦታውን በመውሰዱ ለሰስተኛና ከዚያ በላይ ላሉት ክፍሎች ሁሉ በትምህርት ቋንቋነት ማገልገል ሲጀምር፣አማርኛ ለአንደኛና ለሁለተኛ ክፍሎች የትምህርት ቋንቋ ሆኖ ማገልገል ጀመረ:: ከ1953 ዓ.ም. ጀምሮ ደግሞ አማርኛ የትምህርት ቋንቋነቱ ለኢትዮጵያ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሁሉ ሆነ ::

## 2.1.4 አማርኛ አሁን ያለበት ሁኔታ

አማርኛ በ1987 ዓ.ም. ለሕዝብ ውይይት በቀረበው ረቂቅ ሕገ

በመመረጡ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግሥት የሥራ፡ ቋንቋ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡

አማርኛ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች የሥራ፡ ቋንቋ ከመሆን ጎን በክልል ሶስትና አሥራ አራት ለሚኖር ሕዝብ የዕለት ተዕለት ተግባር ማከናወኛ ዋነኛ ቋንቋ፣ እንዲሁም የመንግሥቶቻቸው የሥራ ቋንቋ ነው፡፡ ደቡብ ሕዝቦች ተብለው በአንድ መስተዳድር ሥር የተጠቃለሉ ብሔር ብሔረሰቦች፣ ብሎም የጋምቤላና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕዝቦች አማርኛን የክልላቸው መንግሥት የሥራ ቋንቋ አድርገው በመጠቀም ላይ ይገኛሉ፡፡

አማርኛ በሁሉም የኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ከአራተኛ ክፍል ጀምሮ እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ እንደአንዱ የትምህርት ዓይነት የሚሰጥ ሲሆን፣ በክልል ሶስትና አሥራ አራት ግን ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ እንደአንዱ የትምህርት ዓይነት ከመሰጠት አልፎ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ የትምህርት ቋንቋ ሆኖ እንዲያገለግል ተወስኗል፡፡ /የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ረቂቅ 1985/ ፡፡

አማርኛ በመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ዘርፍ ከጥንት ጀምሮ ሲያገለግል የቆየና አሁንም ቢሆን ከፍተኛውን ድርሻ ይዞ የሚገኝ ቋንቋ ነው፡፡ በጽሑፍ እንቅስቃሴዎች አኳያም ሲታይ በልዩ ልዩ ልቦለድና ምንባባዊ ጽሑፎች የደረጀ ነው፡፡

አማርኛ በአሁኑ ጊዜ ለበርካታ የውጭ ቃላትና ሐረጎች ተዘኪ ያሉት፣ ከዘመናዊ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር ራሱን ያቀራረበ፣ በአንፃራዊ መልክ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ቋንቋዎች ሁሉ በተሻለ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ፣ ብዙ ተጠቃሚዎች ያሉት ቋንቋ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከፖለቲካዊ ገፅታዎች አኳያ ያሉበትን ችግሮች ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## 2.1.5 <u>ፖለቲካዊ ገፅታዎች</u>

ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ መልኩ በአማርኛ ቋንቋ ላይ ጥላቻ ያላቸው የተወሰኑ ብሔር ብሔረሰቦች አሉ:: የጥላቻው ታሪክ የተነሳው ከአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ነው ይባላል:: አፄ ምኒልክ ወታደራዊ ወረራን ተጠቅመው ግዛታቸውን ወደ ደቡብ ፣ ወደምዕራብና ምሥራቅ ባስፋፉበት ወቅት ፣ በነፍጥ ኃይል ሌሎችን ብሔረሰቦች ካስገበሯቸው ወታደሮች አብዛኛዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ነበሩ:: በዚህ ምክንያት "ነፍጠኞችን" የጠሉት ብሔር ብሔረሰቦች አማርኛ ቋንቋንም ከነፍጥ ጋር አያይዘው ጠሉት ፣ "የወቋኞች ቋንቋ" ብለው ጠሩት:: አንደርበን/1967/ በኢትዮጵያ ፣የጎሣ ቋንቋ ተጠቃሚዎች በአማርኛ ቋንቋ ላይ ዝቅተኛ አመለካከት እንዳላቸው አረጋግጧል:: የዚህ ጥናት አቀራረብም ከገጠመኙ እንደሚያስታውሰው ፣ በኢትዮጵያ ወታደራዊ ደርግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ ፣ በተለይ በ 1969 ዓ.ም. አካባቢ በተወሰኑ ቦታዎች ፣ብሔር ብሔረሰቦች አማርኛን እንደማይፈልጉ የሚገልፁ ጽሑፎች ይበተኑ ነበር ፤ ገለጻዎችም ይደረጉ ነበር:: ይህ ቀስቀሳ ወደትምህርት ቤቶችም ዘልቆ ፣ ተማሪዎች "አማርኛን አንማርም፣ የአማርኛ መምህራን ይውጡ" ብለው መፈክር ያሰሙበትና ግርግር የፈጠሩበት ሁኔታ ነበር::

ዛሬም ቢሆን በአንዳንድ ክልሎች፣ በአማርኛ ቋንቋ ላይ አሉታዊ አመለካከት ካላቸው ብሔር ብሔረሰቦች የወጡ ተማሪዎች ከወላጆቻቸውና ከጓደኞቻቸው ባገኙት ልምድ መሠረት በአማርኛ ቋንቋና በትምህርቱም ላይ የጥላቻ ስሜት እንደሚያንፀባርቁ ለማወቅ ተችሏል::

አዲስ አበባን በተመለከተ ፣ ነዋሪዎቿ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ጥርቅም ቢሆኑ 75% የአፍ መፍቻቸው አማርኛ መሆኑን ማክናብ/ 1989 / ተገልጻለች:: ታዲያ ከዚህ ጥርቅም ኅብረተሰብ የወጡት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋና በትምህርቱ ላይ ምን ዓይነት አመለካከት ይኖራቸው ይሆን? ይህ ጥያቄ በዚህ ጥናት ውስጥ የሚመለስ ይሆናል::

ስለአማርኛ ቋንቋ ይህን ያህል ግንዛቤ ካገኘን ቀጥለን ስለአመለካከት አጠቃላይ ባሕርያት ፣ ስለተማሪው አዎንታዊና አሉታዊ አመለካከት አፈጣጠር ፣እንዲሁም በተማሪ አመለካከት ላይ ተፅዕኖ ስለሚያደርጉት ነገሮች እንመለከታለን::

## 2.2 የአመለካከት አጠቃላይ ባሕርያት

አመለካከት በትምህርት የሚገኝ ለተለያዩ ስሜቶች ወይም ሁኔታዎች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የአስተሳሰብ ሁኔታ ነው:: ሆርስ /1976:407/ "አመለካከት በቀጣይነት የሚቀሰም በተወሰነ የመነሳሳት /stimuli /ደረጃ ላይ የሚታይ የማሰብ፣የማድረግ፣ወይም የውስጣዊ ስሜት /feeling / ሁኔታ ነው" ይላል::
ውሉዲክውስኪ / 1985:46 / "አመለካከት በትምህርት ይቀሰማል፤ በልምድ ሂደት፣በቀጥታ ትምህርት፣በመምህር–ተማሪ ግንኙነት፣በልጅ–ወላጅ ግንኙነት በአሠሪ–ሠራተኛ ግንኙነት፣ ወዘተ. ይዳብራል" ይላል::

እንግዲህ እነዚህን ጠቢቦች በቀላል ቋንቋ ስናጠቃልል፣አመለካከት በአዎንታዊነትም /Positive/ ሆነ በአሉታዊነት /Negative / ከአካባቢ በትምህርት የሚቀሰም፣በልምድ ሂደትና በተለያዩ ግንኙነቶች የሚዳብር፣ የተወሰነ ደረጃ ያለው የማሰብና የማድረግ ውስጣዊ ስሜት ነው::

አመለካከትን ከሁኔታዎች አካሄድ ገምተን "እንዲህ ሊሆን ይችላል" እንላለን እንጂ በዓይን አይታይም:: ሆኖም በንቃት ከተጠራቀመ ገጠመኝ፣ ከቃላዊ ሪፖርት፣ከጥቅል ጠባይና ከተፈጥሯዊ አሠራር ምልክቶች ሊታወቅ ይችላል::

የአመለካከት ፅንስ ሀሳብ የሚመነጨው በግለሰብ ጠባይ ውስጥ ከሚታይ ሥርዓት መሆኑንና የአንዱ ሰው የአመለካከት ጥራት የሚገኘው በዓይን ከሚታይ እንዲሁም ግለሰቡ ለገምገማ ከሚሰጠው ምላሽ መሆኑን የብሪታኒካው ኢንሳይክሎፔዲያ / 1986 / እና ሸሪፍ / 1965/ ይናገራሉ::

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ፍላጎትና አመለካከት አስፈላጊ መሆናቸውን በርካታ ጠበብት ይናገራሉ:: በዚህ መሠረት ታይዳማን /1959/ ፣ ብረምፊት / 1966/፣ አነደኒ / 1983/ ፣ ሰኪን / 1990/ በቋንቋ ትምህርትና ልምምድ ውስጥ ወሳኝ ነገሮች ፍላጎትና አዎንታዊ አመለካከት መሆናቸውንና፣በቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ጥሩ ውጤት ሊያመጡ እንደሚችሉ ተናግረዋል::

እፖሉስኪ / 1969/ በቋንቋ ትምህርት ላይ ዋነኛው ጉዳይ ተማሪው ለቋንቋውና ለቋንቋው ተናጋሪዎች የሚኖረው አመለካከት መሆኑን ከገለፀ በኋላ የተማሪው የግንኙነት አመለካከትና ስለሌሎች ቡድኖችም ያለው አመ-

አመለካከት ከማንነታችን የማይለይና ወሳኝ መሆኑን ውሌይ ኮዋኪ /1985: 47/ እንደሚከተለው ይገልጻል:: " አመለካከት በአስደናቂ ሁኔታ ስሜትን ያንቀሳቅሳል:: የማንኛውም ሰው ሕይወት በአመለካከቱ ዙሪያ ተሆናለች፤ አመለካከት ሁልጊዜ ከኛ ጋር ሆኖ በቋሚነት በጠባያችንና በትምህርታችን ላይ ተፅዕኖ ያደርጋል:: "

አመለካከትና ሌሎች ሥነ ልቦናዊ ሁኔታዎች በትምህርት ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ቀላል እንዳልሆነ ከሙያሉ ምሁራን ጥናታዊ ጽሑፎች ማረጋገጥ ይቻላል:: አመለካከትና መነቃቃት /motivation / ለአስተዋይነትና / intelligence ለጥቅል ዕውቀት / aptitude/ ልዩነት ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ:: ስለዚህ በ ቋንቋ ትምህርት ላይ ሥነ ልቦናዊ ሁኔታዎች የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ቀላል እንዳልሆነ ግንዛቤ ተገኝቷል: /አልፍሬዱ 1972 ፤ ሉትለውዱ 1984 ፤ ፔይን 1992

ክላውዝማየርና ጉድዊን / 1968: 202 / " ... ጥሩ ስሜቶች፣ ዱላና ሽልማቶች፣ምቹ ጥሩ ዕድሜ ወዳለው አዎንታዊ አመለካከት ሲወስዱ፣በአንጻሩ ደግሞ ውድቀትና ቅጣቶች መጥፎ ወደ ሆነው አሉታዊ አመለካከት ይወስዳሉ:: " ይላሉ::

አመለካከት ስሜታዊነትና ተግባቢነት /Sociability / በትምህርት ቤት በትምህርትነት መቀረብ ገና ባይጀምሩም በጣም በርካታ ጥናታዊ ጽሑፎች ተማሪዎች እነ ዚህን ሥነ ልቦናዊ ሁኔታዎች በትምህርት ቤት መማር እንዳለባቸው ይጠቁማሉ:: ስለዚህ በቋንቋ ትምህርት አመራር ላይ የተሳተፈ ማንኛውም ሰው ተማሪዎች ከሚማሩት ነገሮች አመለካከት አንዱ ሆኖ እንዲቀርብ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ማወቅ አለበት /ስታይንባክ 1980 ፤ አሰራይት 1982 ፤ ፔይን 1992/ ::

በትምህርት ቤት ተማሪዎች መማር የሚገባቸው የአመለካከት ዓይነቶች የሚከተሉት መሆናቸውን ክላውዝማየርና ጉድዊን / 1968:202 / ይገልጻሉ::

- ናሙና የሚሆኑ ምሳሌያችን፣
- ቀና ውስጣዊ ስሜት እንዲያድርባቸው የሚያደርገ፣
- መረጃ የመስጠትን ልምድ የሚያጎለብት፣
- ጥሩ ሥልቶችን መጠቀም የሚያስችለ፣
- ትክክለኛውን ልምድ ማቀነባበር የሚያስችለ፣
- ነፃ አመለካከታቸው እንዲጎለፀገ የሚያደፋፍር::

በነዚሁ በነክላውዝማየር / 1968 : 374 / አገላለጽ በትምህርት ቤቶች ከሚገነቡትና በጣም ጠቃሚ ከሆኑት ነገሮች አመለካከትና ዋጋ " Value " ዋነኞቹ

ናቸው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች ተማሪው መስተጋብራዊ ሁኔታዎችንና ሌሎች የሚፈልጋቸውን ነገሮች እንዴት ተነጋግሮ ማግኘት እንዳለበት ያመለክታሉና፡፡

አመለካከት ውስጣዊ ስሜት ሆኖ ለረጅም ጊዜ በሰዎች ጠባይ ላይ ተፅዕኖ በማድረግ ኃይሉን መግለጽ የሚችል ነው፡፡ በተመሳሳይ መልክ አንድ ሰው ለአንድ ነገር መነቃቃት ስለመነቃቃቱ ከአመለካከቱ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ቻክቴይን / 1988 : 139/ "ከፍተኛ ፍላጎት፣ዝግጁነት፣ብቃትና ትምህርት የመቀሰም ብቃት /achievement / በውስጣዊ የመነቃቃት ባሕርይ ይወሰናሉ" ይላል፡፡

እንዶ ኤሳይ /1986/ አገላለጽ ደግሞ ጥሩ የቋንቋ ትምህርት እንዲካሄድ መነቃቃት፣አጠቃላይ ዕውቀት፣ውጤት መሻትና /concern for [illegible] / የክፍል ብቃትና አስፈላጊ ሲሆኑ፣በክፍል ብቃትና ላይ ተፅዕኖ ከሚያደርጉት በርካታ ነጥቦች አንዱ አመለካከት ነው፡፡

ማኅበራዊ ሁኔታ አመለካከትን ይወስናል፤ አመለካከት ወደ መነቃቃት ያመራል፤ የመነቃቃቱ ሁኔታ ትምህርቱ በጥሩ ወይምበመጥፎ ሁኔታ እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡

ስፖልስኪ / 1989/፣ አመለካከት በመማር ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ የሚያደርግ ሳይሆን ተፅዕኖ ሊያመጣ ወደሚችለው መነቃቃት የሚወስድ መሆኑን ይናገራል፡፡ ፒምዝሌር /1962 : 16 / ይህንን ሐሳብ ሲያጠናክር "መነቃቃት ሁለት ዋና ጉዳዮችን ያቀፋል፤ ኃይለኛነትና /intensity / አሳቢነት /kindness /፡፡ አሳቢነት ብዙ ጊዜ ተማሪዎች ለመማር ካላቸው ዋና ዓላማና ግብ ጋር የተያያዘ ነው። ይህ ጉዳይ ደግሞ ከአመለካከት ጋር በጣም የተቀራኘ ነው፡፡ " ይላል፡፡ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሃሳብ በካንንገስዎርዝ / 1984 : 59 / እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ "

> መነቃቃት ለቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ ድርሻ
> አለው በጥሩ ሁኔታ የተነቃቃ ወይም ጥሩ
> አመለካከት ያለው ተማሪ ጥሩ ውጤት ሲኖረው
> በመጥፎ ሁኔታ የተነቃቃ ተማሪ ወይም አመለ
> ካከቱ የተበላሸ ተማሪ ውጤቱ የማይረባ ይሆናል፡፡

ካንንገስዎርዝ ስለመነቃቃት ጠቃሚነት ሲሃኩሩን ሰፋ በማድረግ "... በጥሩ ሁኔታ የተነቃቃ ተማሪ ሆኖ በመጥፎ ሁኔታ እንኳን ቢማር፣በጥሩ ሁኔታ ተምሮ በጥሩ ሁኔታ ካልተነቃቃው ተማሪ የተሻ ውጤት ያመጣል" ይላል፡ / 1984 : 59 /፡፡

አመለካከት ገትርና ቋሚ ሳይሆን እንደሁኔታው ሊሻሻልና ሊቀየር የሚችል መሆኑን ውሌደን ዌንኪ / 1985 / እና ፔይን / 1992 / ይናገራሉ፡፡

ስለዚህ አንድ ተማሪ በቋንቋ ትምህርት ላይ የሚያንፀባርቀው አሉታዊ አመለካከት በልዩ ልዩ የአቀራረብ ስልት ወደ አዎንታዊነት ሊቀየር ይችላል::

ዊልጋ / 1981 / የውጭ ቋንቋ ትምህርትን ከማስተዋወቃችን ወይም ከመጀመራችን በፊት ተማሪዎቹ ስለዚያ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት፣በዚያን ወቅት ቋንቋውን መማር ለምን እንዳስፈለገና ከቋንቋው ትምህርት የሚያገኙት ጥቅም በቅድሚያ መታወቅ እንዳለበት ትናገራለች::

ዊልጋ ለውጭ ቋንቋ ትምህርት ትኩረት ሰጥታ ትናገር እንጂ ፅንሰ ሃሳቡ ለሁሉም ቋንቋዎች ይሠራል:: ጶቤን / 1990 : 13 / ማንኛውም የቋንቋ ትምህርት ከመከናወኑ በፊት ማኅበረሰቡና ተማሪው ስለ ቋንቋው ያላቸው አመለካከት በጥራትና በጥልቀት መጠናት አለበት ትላለች: ከዚህ ጋር በጣም ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ማኬይና ማውንት / 1978 /ፕሬ የቋንቋ ኮርስ ለማዘጋጀት በቅድሚያ ከሚመለከታቸው ሰዎች ጋር መደበኛ ግን ኙነት ማድረግ ተገቢ መሆኑን ይጠቁሙና፣ይህ ካልሆነ ውጤቱ ብላጠ እንደሚሆን ያስምርበታል::

ስለዚህ ከማንኛውም የቋንቋ ትምህርት በፊት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ተማሪዎች፣መምህራን፣ኅብረተሰቡና የትምህርት ባለሙያዎች አመለካከታቸው መጠናት አለበት::

3 <u>የተማሪው አዎንታዊና አሉታዊ አመለካከት አፈጣጠር</u>

በመጀመሪያና በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ በተማሪዎች መሐል የአቀባበል ደረጃ ልዩነቶች ይታያሉ:: ይህን በተመለከተ ስፖልስኪ / 1969 : 271 / የሚከተለውን አስፍሯል::

> የመጀመሪያ ቋንቋን በተመለከተ ማንኛውም ጤነኛ ሰው ቢያንስ እስከ መግባባት ደረጃ ድረስ ችሎታ ይኖረዋል:: የሁለተኛ ቋንቋን በተመለከተ ግን ምንም ከማይችል እስከ ከፍተኛ ችሎታ ድረስ ልዩነቶች ይታያሉ:: በነዚህ የትምህርት አቀባበል ልዩነቶች ተፅዕኖ የሚያደርጉት ነገሮች የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ፣ዕድሜ፣አጠቃላይ ዕውቀትና አመለካከት ናቸው::

በስፖልስኪ አገላለጽ በቋንቋ ትምህርት አቀባበል ላይ ተፅዕኖ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ አመለካከት መሆኑን እንረዳለን:: በተመሳሳይ

መሰኮ ቻክቴይን / 1988 : 123 / ፦ ተማሪዎች ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በማመጠበት ጊዜ የተለያዩ አመለካከቶች ይዘው ይመጣሉ:: ከነዚህ አመለካከቶች ጥቂቶቹ ለጥሩ ውጤት ትምህርቱን የሚያግዙ ሲሆኑ ጥቂቶቹ ደግሞ ትምህርቱን ያዳክማሉ ይላሉ::

ተማሪዎች ስለትምህርቱ፣ስለመጻሕፍቱ ስለክፍሉና ስለክፍል ጓደኞቻቸው፣እንዲሁም ስለራሳቸውና ስለመምህራቸው ያላቸው አመለካከት በትምህርታቸው ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ይኖረዋል:: በተለይ ተማሪዎች መምህራቸውን የማይወዱትና የማያከብሩት ከሆነ ማለትም በመምህራቸው ላይ አሉታዊ አመለካከት ካላቸው እሱ የሚሰጠውን ትምህርት አይከታተሉም። በዚህን ጊዜ መምህሩ በትምህርቱና በተማሪዎች መሐል ገርደሸ ሆኖ ይቀማሉማለት ነው: / ውሎዲክውስኪ 1985 ፤ ጋምበርት 1972 ፤ ኾመር 1983 / ::

እነዚህ ምሁራን እንደሚነግሩን ተማሪዎች መጽሐፉን፣ክፍሉን፣የክፍል ጓደኞቻቸውንና መምህራቸውን ከጠሉ ለቋንቋው ትምህርት አሉታዊ አመለካከት እንደሚኖራቸውና ከወደዷቸው ግን አዎንታዊ አመለካከት እንደሚኖራቸው ነው::

በሌላም በኩል ቻክቴይን / 1988 : 123 / የሚከተለውን ጽፏል::

> ተማሪዎች ስለቋንቋው፣ስለቋንቋው ተናጋሪዎችና
> ስለባሕላቸው አዎንታዊ፣አሉታዊ፣ ወይም
> ደብለቅ አመለካከት ሊኖራቸው ይችላል:: ለቋ
> ንቋውና ለቋንቋው ተናጋሪዎች ከፍተኛ ግምት
> የሚሰጡ ከሆነ የመማር ፍላጎታቸውም ከፍተኛ
> ይሆናል:: በተጨማሪም ቋንቋውን ማወቅ ለወ
> ደፊቱ ትርፋማ መሆኑን ካመኑ ጊዜያቸውን ሰውተው
> ተግባቦታዊ /communicative /ችሎ
> ታቸውን ያዳብራሉ፤ ወደቋንቋው ተናጋሪ ኅብረ
> ተሰብ ለመሄድ የሚማሩም ከሆነ አመለካከታቸው
> የበለጠ ቀናና ከፍያለ ይሆናል::

በቋንቋ ላይ አሉታዊ አመለካከት ያለው ተማሪ ስሜቱን በተለያዩ መንገዶች ይገልጻል:: ጓቤን / 1990 / እንደምትነግረን ተማሪው መምህሩን በትኩረት አያዳምጥም፤ ይረብሻል፤ይቁነጠነጣል፤ሌላ ሥራ ይሠራል፤ከክፍል ጥሎ ይወጣል ወዘተ. ታዲያ የዚህ ዓይነቱ ግለሰባዊም ሆነ ቡድናዊ የቋንቋ ትምህርት ጥላቻ የሚፈጠረው በተማሪዎች ፍላጎትና በትምህርቱ አካሄድ መካከል አለመጣጣም ሲፈጠር ነው:: ለምሳሌ ተማሪዎቹ ቋንቋውን ለቀጽበታዊ መገባቢያነት ብቻ የሚፈልጉት ሆኖ ሳለ መምህሩ በሥነ ጽሑፍና በመዋቅራዊ ደንብ ላይ የሚያተኩር ከሆነ ተማሪዎቹ የመማር ፍላጎታቸው ሊቀዛቀዝና

በትምህርቱ ላይ አሉታዊ አመለካከት ሊያሳድሩ ይችላሉ።

እንደ ጁጌንና ኦስሸቲይን / 1986 / አገላለጽ በቋንቋ ላይ አሉታዊ የሆኑን አመለካከት የሚፈጠረው በታሪካዊ፣በፖለቲካዊና በብሔር ተገንነት ስሜት ወይም በማኅበራዊ ገጽታዎች ሳቢያ ሊሆን ይችላል። በየትኛውም መልክ ቢሆን አሉታዊ አመለካከት ጉዳት እንጂ ጠቃሚ ስለማይሆን የቋንቋ ተማሪ ሁሉ በታለመው /target / ቋንቋ ላይ አዎንታዊ አመለካከት ሊኖረው ይገባል። ጁጌንና ኦስሸቲይን : /1986 : 14 / የሚከተለውን አስፍረዋል።

> በቋንቋ ላይ አዎንታዊ አመለካከት ካለ ቋንቋውና ቋንቋው ለሚወክለው ባሕል አድናቆት እንዲኖር ያደርጋል፤ ደግሞም ቋንቋውን ለመማር ገሳዊ ከፍተኛ መነቃቃት እንዲነሳሳ ያደርጋል። ከሁሉም በላይ ተማሪው ለቋንቋው ትምህርት በጣም የሚጉጉ ይሆናል። በቋንቋ ላይ የሚታይ ጉጉትና ገሳዊ አዎንታዊ አመለካከት በቋንቋው ትምህርት ከፍተኛ ውጤት እንዲገኝ ያደርጋል።

ይህንን ሐሳብ ስፖልስኪ / 1989: 151 / ሲያጠናክር "ተማሪው ለታለመው ቋንቋ ተናጋሪዎች አዎንታዊ አመለካከት ካለው ለቋንቋውም ትምህርት አዎንታዊ ውጤት ይኖረዋል" ይላል።

በሌላም በኩል ተማሪዎች በቋንቋው ትምህርት የሚያገኙት ውጤት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል። ጥሩ ውጤት አዎንታዊ ተፅዕኖ ሲኖረው መጥፎ ውጤት አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል። ይህንን በተመለከተ፡ የተለያዩ ምሁራን ባቀረቡት ሐሳብ መሠረት፡-

በቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውጤት ያመጣ ትጉህ ተማሪ ቀና አመለካከቱ ከፍ ይላል። ይህ ከፍ ያለው አመለካከት ደግሞ ለላ ከፍተኛ ውጤት እንዲመዘገብ ምክንያት ይሆናል። በአንጻሩ ደግሞ በቋንቋው ትምህርት ተደጋጋሚ ውጤቱ ደካማ የሆነ ተማሪ አሉታዊ አመለካከት ሊያዳብር ይችላል። ይህ አሉታዊ አመለካከት ደግሞ አስምርጡን ቀልፍ ሌሎች ደካማ ውጤቶች እንዲከተሉ ያደርጋል። ስለዚህ መምህራን ተማሪዎቻቸው ጥሩ ውጤት እንዲያገኙ እንዲቀሰቀሱ /motivation / የየራሳቸውን ዘዴ መጠቀም ይኖርባቸዋል። ይህ ማለት ግን ተማሪዎቹ ሁሉ ጥሩ ውጤት እንዲያመጡ ብለው ከደረጃ በታች የሆነ በጣም ቀላል ፈተና ይሰጥ ማለት አይደለም፤ በጣም ቀላል ፈተና መሆኑ ራሱ እንዳይቀሰቀሱና አሉታዊ አመለካከት እንዲያዳብሩ ሊያደርግ ይችላል፡ /ሄርመር 1983፣ ስተርን 1983፣ ሊትልውድ 1984/። የተማሪዎችን ውጤት አስመልክቶ፡ሄርመር/1983:6/ "ጥሩ ውጤት ማግኘት

አለማገኘት በተማሪው አኳ ቢሆንም መምህሩ በሂደቱና በአፈጻጸሙ ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል ” ይላል።

የተማሪው ቀደምት ልምዶችም በትምህርቱ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያደርጉ በተ ሃርወር / 1983 : 4 / እንደሚከተለው አቅርበዋል።

> ... ምናልባት ተማሪው ቀደም ሲል ይህንን ቋንቋ ተምሮ ያቋረጠ ከሆነና አሁን እንደገና እንዲማር ከተደረገ የበፊት ገጠመኙ መንፀባረቅ ይጀምራል። በፊት ሲማር ከብዶት እንደሆነ አሁን ትምህርቱን ገና ሳይጀምር “ እኔ ይከብደኛል፣አልችልም” በማለት ከወዲሁ አሉታዊ አመለካከት ይዞ ትምህርቱን ይጀምራል። በአንጻሩ ደርሞ የሚወደውና ጥሩ ውጤት ያስመዘገበበት ከሆነ አሁንም በአዎንታዊ አመለካከት ሊነሳሳ ይችላል።

ቻስቴይን / 1988 : 139 / “ በክፍል ውስጥ ንግግርን ለመማርና ከሌሎች ጋር ለመግባባት ተማሪዎች አዎንታዊ የግል ጠባብና የመተባበር አመለካከት ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም የሌሎችን ጠሳብ ለማዳመጥና የራሳቸውንም ጠሳብና ስሜት ለመግለጽ ፍቃደኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል ” ይላል።

## 2.4. ቋንቋና የቋንቋን ትምህርት አስመልክቶ በተማሪው አመለካከት ላይ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ነገሮች

### 2.4.1 ወላጆች፣ ኅብረተሰቡና እኩዮች /peers /

በአንዱ ሰው የሕይወት አቅጣጫ ላይ ድርሻ ያላቸው ነገሮች በርካታ ናቸው። ት/ቤት፣ቤተሰብ፣ጓደኞች፣የአካባቢ ነዋሪዎችና፣ የእምነት ሁኔታም አስተዋጽኦ አላቸው። ይህን በተመለከተ ኩምበስ / 1968 : 17 / “ ... በተጨማሪነት ቤተሰብ፣ ጓደኞች ፣ ቤተክርስቲያንና የአካባቢ ኃይሎች በየራሳቸው መንገዱ የተማሪውን ሕይወት ወይም ማንነት ይቀርጻሉ... ” ይላል።

ከቋንቋ ትምህርት አኳያም ሲታይ የተማሪው ወላጆች፣ ኅብረተሰቡና እኩዮች ተማሪው በቋንቋ ትምህርት ላይ ሊኖረው የሚችለውን አመለካከት በአንዱ ወይም በሌላ መልክ ተፅዕኖ ሊያደርጉበት

ትምህርት ከሌሎች የሚያገኘው መገለጫ፣ የቋንቋ ትምህርት ፍላጎቱንና አመለካከቱን ከሚወስኑት ነገሮች አንዱ መሆኑን ሳምበርትን ጠቅሶ ያቀርባል:: ፒኔስ /1976: 174 /ደግሞ የሚከተለውን ጽፏል::

> ሕጻናት ገና በጨቅላነታቸው ከወላጆቻቸው የሚያገኙት
> የአስተዳደግ ሁኔታ ማለትም ቁጣ፣ጥላቻ፣ የሚደረግና
> የማይደረግ፣ የሚያስጠላና የሚማርክ፣ስለሰዎች፣ስለ
> እንስሳት፣ስለዕፅዋት፣ወዘተ. የሚያገኙት ትምህርት፣
> ተረቶችና ቀልዶች ሁሉ በልጁ የወደፊት አመለካከት
> ላይ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል::

የቤተሰብ አመለካከት በልጁ አመለካከት ላይ ትልቅ ድርሻ እንዳለው ስፖልስኪ /1969/ ካርለን ጠቅሶ ያቀርባል:: ይኸው ፀሐፊ በ1960 የተደረገውን የጋርዴነርን ጥናት መሠረት በማድረግ በሞንትሪያል የእንግሊዝና ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች በፈረንሳይኛ ቋንቋ ላይ ያሏቸው አመለካከት የወላጆቻቸው አመለካከት ነፀብራቅ እንደሆነ ይገልጻል:: ከዚህ ጋር በጣም ተመሣሣይ በሆነ መልኩ ፒልና በይዱ /1956: 10: "የወላጆች የአመለካከትና የባሕርይ ለውጥ ብዙ ጊዜ በልጁ ለምዱና ባሕርይ ላይ ለውጥ ያመጣል" ይላሉ::

ዱጋል / 1983 : 16 / ወላጆች በልጁ ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን ሲገልጽ "ወላጆች የልጃቸውን የቋንቋ ትምህርት የሚከታተሉና የሚያደንቁ ከሆነ የልጁም አመለካከት ቀናና ችሎታውም ከፍ ያለ ይሆናል" ይላል:: ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ ስታርን /1983 : 309 / "ወላጆችና ማኅበረሰቡም በልጁ ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ልጁ ለቋንቋ ትምህርት የሚኖረውን ስሜትና አመለካከት በአዎንታዊነት ወይም በአሉታዊነት እንዲንፀባረቅ ያደርጋል" ይላል::

ከኅብረተሰቡ የተወረሱ ባሕላዊ እምነቶች፣በሁለት አቅጣጫ በአመለከካከታችን ዕዱገት ላይ ተፅዕኖ እንደሚያደርጉ ስፖልስኪ / 1989 / ጋርዴነርን ጠቅሶ ያቀርባል:: እነሱም ስለቋንቋው ቤተሰቦች ባለን አመለካከትና ስለቋንቋው የመማር ሁኔታ ላይ ባለን አመለካከት ነው:: ማኅበራዊ ሁኔታ፣ለቋንቋ መማር ሁኔታዎች መመቻቸት አለመመቻቸት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባይኖረውም በስውር ተፅዕኖ ያደርጋል::

ሂርመር / 1983 : 4 / ወላጆች፣እኩዮችና ማኅበረሰቡም በልጁ አመለካከት ላይ የሚኖራቸውን ድርሻ እንደሚከተለው ያቀርባል::

> የተማሪ አመለካከት በአካባቢው ባሉት ሁኔታዎች
> ተፅዕኖ ሥር ይወድቃል:: ለምሳሌ የተማሪው

ወላጆች የታላሚውን ቋንቋ ባሕል የሚቃወሙና የሚጠሉ ከሆነ የልጁን አመለካከት ወደ አሉታዊ ተፅዕኖ ይወስደዋል፡፡ በአንጻሩ ወላጆች በ ቋንቋው ላይ ያላቸው ቀና አመለካከት በልጁ ላይ አዎንታዊ አመለካከት ያሳድራል፡፡ በሌላም በኩል የተማሪው እኩዮች አመለካከት አዎንታዊ ከሆነ የሱም እንደዚያው ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ገለሰቦች ስለ ታላሚው ቋንቋ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊነት ወይም አሉታዊነት በልጁ አመለካከት ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡

በተለይም የእኩዮች አመለካከት በልጁ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዳለው ስፖልስኪ / 1969፡ 274 / ሲገልጽ " ለቋንቋ ትምህርት የተማሪው እኩዮች አመለካከት ወሳኝ ሚና ይኖረዋል " ይላል፡፡

እንግዲህ ከተለያዩ ምሁራን አገላለጽ እንደተረዳነው ተማሪው ስለ ሚማረው ቋንቋና ስለቋንቋውም ትምህርት የሚኖረው አመለካከት በወላጆች፣ በኅብረተሰቡና በእኩዮች አመለካከት ተፅዕኖ ሥር ይወድቃል፡፡ እነዚህ ወገኖች ልጁ ለሚማረው ቋንቋና ለቋንቋው ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት ካላቸው የልጁም አመለካከት አዎንታዊ ይሆናል፤ አመለካከታቸው አሉታዊ ከሆነ የልጁም እንደዚያው ይሆናል ማለት ነው፡፡

2.4.2 <u>መምህራን</u>

በርካታ መምህራን ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዲወዱና አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ፡፡ ስለሆነም በተለያየ መልክ ይቀ ሰቅሷሉ፣ይመክራሉ፣ለማሳመን ይጥራሉ፡፡ ዉሉደክ ዋከ/ 1985 / እን ደሚለው እነዚህ ባዶ ቃላት ወይም ነገገር ብቻቸውን በተማሪዎች ላይ አመለካከት አያመጡም፡፡ ተማሪዎች ራሳቸው በትምህርቱ እንቅስቃሴ ተሳ ትፈው በመምህሩ አቀራረብና በትምህርቱም መሳብ መቻል ይኖርባቸዋል፡፡

መምህር ተማሪው በቋንቋ ትምህርት ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከት እንዲያሳድር ለማድረግ " ትልቅ ወሳኝ አካል ነው " ቢባል የተጋነነ አይሆንም፡፡ ስፖልስኪ / 1969 ፡ 273 / የመምህራን አመለካከት ለተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ወሳኝ መሆኑን የጠቀሰ ሲሆን

የስፖሊስኪን ሐሣብ የሚያጠናክር ሐሳብ አቅርባለች። አንደገና ዓንሤሉ
/ 1964 ፡ 17/ " በቂ ዕውቀት ያለውና በደንብ የሚያስተምር ዝነኛ መም
ህር በተማሪዎቹ ተመስጠና ተኪትፍ እንዲሁም ባሕርይ ላይ ጥሩ ተፅዕኖ ያደርጋል"
ይላል። ሀርመር / 1983 / እና ውሉደክዎከኪ / 1985 / መምህሩ ተማሪዎ
ችን በአቀራረቡ የሚስብና የሚማርክ ፣ ስብዕናቸውን የሚጠብቅና የሚንከባከባቸው
ከሆነ ተማሪዎች እንደሚወዱትና እንደሚያከብሩት ብሎም በትምህርቱ ላይ አዎንታዊ
አመለካከትን በማሳደር ከልብ እንደሚማሩ ይገልጻሉ። በሌላ በኩል መምህር ነጭናጫና
ተኪዳቢ ፣ እንዲሁም ተደባዳቢ ከሆነ ተማሪዎቹ ትምህርቱን እንዲጠሉና አሉታዊ አመ
ለካከት እንዲያድርባቸው እንደሚያደርግ ያስረዳሉ።

ከላይ በተከታታይ ሐሳባቸውን የሰጡት ምሁራን ሁሉ አንዱ መምህር በተማሪ
ዎች አመለካከት ላይ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ያመለክታሉ። ስለዚህ መምህር ሙያ
ውን አፍቃሪና ከልብ የሚሠራ ፣ ጠቀኛና ተማሪዎቹን የሚወዱ ጥሩ አርአያ መሆን
የሚችል ሰው መሆን አለበት። ይህ ከሆነ በተማሪዎች ላይ አዎንታዊ አመለካከትን
ሊያሳድር ይችላል። ይህንን አስመልክቶ ሃርመር / 1983 / ለተማሪዎች አዎን
ታዊ አመለካከት ሲባል አንዱ የቋንቋ መምህር ማድረግ የሌለበትንና ማድረግ የሚና
ርበትን እንደሚከተለው ያቀርባል።

- መምህር ሲሳደብ ፣ ሲቆጣ ፣ ሥራውን እንደነገሩ ሲሠራ መታየት
  የለበትም፤
- ሳይዘጋጁ ክፍል መግባት የለበትም፤
- ወሻዋይ መሆን የለበትም ፣ / ለምሳሌ አርፋጆችን አንዳንዴ
  ይቀበላል አንዳንዴ ያባርራል ወዘተ.../
- በቀጥታ መደራደር የለበትም፤ / መምህር ክስታራ ካልሆነ በሚል
  አሮጌ ፈሊጥ አካልና ሥነ ልቦናን የሚጎዳ ቅጣት አለመስጠት/
- በኃይለ ቃል መናገር ወይም ማንባረቅ የለበትም፤
- ትምህርቱን አሰልቺ ማድረግ የለበትም፤ / በዱንገጦሽ ፣ ምቹ ዘዴ
  ባለመምረጥ፤ ወዘተ.../
- አድሏዊ መሆን የለበትም፤ / ለአንዱ ተማሪ ያደረገውን ለሁሉም
  ማድረግ አለበት/

በአንጻሩ የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርበታል

- ሕጎችን ማክበርና ስብዕናውን/ personality / መጠበቅ አለበት።
  / የማያረፍድ ፣ የማይሰክር ፣ የማይባልግ ወዘተ.../
- ትምህርቱ ማራኪ እንዲሆን በጣም መጣር አለበት፤
- ተማሪዎችን በእኩል ዓይን የሚመለከት ፣ ችግራቸውን የሚፈታና የሚያ ማከራቸው የቅር ጓደኛ መሆን አለበት፤
- በታለሚው ቋንቋ በደንብ የሚናገርና አርአያ መሆን የሚችል መሆን አለበት፤
- ተማሪዎች በታለሚው ቋንቋ መናገር እንዲችሉ የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅሞ ማስተማር የሚችል ዘዴኛ መሆን አለበት።

ስቴንባክ / 1980 / በዚህ ሐሳብ ይስማማል።

በተጨማሪም ሌቪንና ሄል / 1990 / እንደሚያቀርቡት አንድ የቋንቋ መምህር፡-

- የሚሠራውንና የሚያሠራውን በየጊዜው መቀያየር ይኖርበታል፤
- ተማሪዎቹ እየተደሰቱ የሚማረበትን መንገድ መፈለግ ይኖርበታል፤
- ቅደሚያ ዕቅድ ሊኖረው ይገባል፤
- ተማሪዎችን ማማከር ይኖርበታል፤
- ተማሪዎቹ ያለገባቸውን እንዲጠይቁ በቂ ጊዜና ዕድል የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል፤
- የተለያዩ መርጃ መሣሪያዎችን መጠቀም ይኖርበታል። መምህሩ ተማሪዎቹን የሚወደና የሚያከብራቸው መሆን ይገባዋል። ሄይከራፍት /1978/ መምህሩ በተማሪዎች ስብዕና ካለዉ ትምህርቱ በቻውን እንደሚሠራ ማሸን ሊቀጠር እንደሚችል ይናገራል።

ቻክቴን / 1988/ ከመምህሩ ቀጣይ ተግባራት አንዱ ተማሪዎች በመጥፎ ስሜት የሚያጠቃልሉት ሐሳብ በትምህርት አቀባበላቸው ላይ ጉዳት እንዳያመጣ ጥረት ማድረግና ተማሪዎች ከመምህራቸውም ሆነ ከክፍል ጓደኞቻቸው የሚጠብቁት ገንቢና አዎንታዊ አስተያየት በመምህራን ዘንድ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ይገልጻል።

መምህራን በተማሪዎቻቸው ፊት ውያቸውን የሚያማርሩና ጥላቻን የሚያንፀባርቁ መሆን የለባቸውም። ምክንያቱም ተማሪዎችም መምህሩን ተከትለው ትምህርቱን ሊጠሉት

ከላይ በዝርዝር እንዳየነው በቋንቋ ትምህርት ላይ ከማንም በላይ በተማሪዎች ላይ ተፅዕኖ ማድረግ የሚችለው መምህሩ ስለሆነ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል። ክፉንና ደጉን በሚገባ እየመረመረ የተማሪዎችን አመለካከት አሉታዊ ሊያደርጉ ከሚችሉ ተግባራት መራቅና አመለካከታቸውን አዎንታዊ ሊያደርጉ የሚችሉ ተግባራትን መፈጸም ይኖርበታል።

## 4.3 <u>መማሪያ መጻሕፍት</u>

የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት የተማሪን አመለካከት በመቀየር በኩል ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። በመሆኑም መጻሕፍቱ በሚዘጋጁበት ጊዜና ከመዘጋጀታቸውም በፊት የተማሪዎችን አመለካከት ጠንቅቆ ማወቅ ተገቢ ይሆናል። ይህንን በማስመልከት ዉርሲያ / 1991 : 443 / “ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ከማዘጋጀታችን በፊት ተማሪዎቹ ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው አመለካከት አዎንታዊነት ወይም አሉታዊነት መታወቅ አለበት” ትላለች። ይህ ቺው ሴት ስለመማሪያ መጻሕፍት አመለካከትን የማስቀየር ኃይል ስትገልጽ “ መማሪያ መጻሕፍት የተጠቃሚያቻቸውን ስሜት የመቀስቀስ ኃይል አላቸው። ስለዚህ ጥሩ መጻሕፍት በአዎንታዊ መልክ ሲቀሰቅሱ መጥፎዎቹ ደግሞ በአሉታዊነት ይቀሰቅሳሉ ትላለች / ገጽ 32/። መማሪያ መጻሕፍት በአባሪዎች ፣ በቃላት ዝርዝርና በሥዕላ ሥዕል ከታደሉ የተማሪዎችን ስሜት ወደ አዎንታዊ አመለካከት እንደሚስቡና እንደሚማርኩ ዉርሲያ / 1991 / ትናገራለች። ካንንገ ስያርዝ / 1984 : 55/ አንዱ መማሪያ መጽሐፍ የቃላት ዝርዝርና ኢንዴክስ መያዝ እንደሚገባው ይናገርና “ እነዚህም መምህሩና ተማሪዎች የተፈለገውን ነገር ቶሎ በለው ማግኘት እንዲችሉ ይረዷቸዋል” ይላል። ስለዚህ አንዱ መማሪያ መጽሐፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ የቃላት ዝርዝር ፣ ኢንዴክስ ፣ ሥዕላ ሥዕሎችንና አባሪዎችን አሟልቶ መገኘት አለበት።

ሹጌን / 1990 : 14/ “ ባለሙያዎች የሚያዘጋጁት መማሪያ መጽሐፍ የተማሪዎችን ስሜት የሚስብና የሚማርክ ፣ የመማር ዝንባሌያቸውን የሚቀሰቅስና በፍላጎታቸው ላይ የተመሠረተ መሆኑን እርግጠኛ መሆን አለባቸው” ትላለች። ካንንገስያርዝ / 1984 : 5/ ይህንን ሐሳብ ሲያጠናክር “ መማሪያ መጻሕፍት ተማሪውን በቀጥታ ወደ ትምህርቱ ዓለም የሚያ

ደርሱና ከተማሪው ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ መሆን አለባቸው። " ይላል። ይህ ፀሐፊ ስለመጻሕፍት ማራኪ የመሆን ሁኔታ ሲናገር "መማረክ የሚችል መጽሐፍ ተማሪው መማር የሚፈልገውን ነገር ያቀፈ ወይም በሚገባ ተማሪውን ሊያሳትፈው የሚችል መሆን ይኖርበታል፡ " ይላል፡ /1984:56/።

መማሪያ መጻሕፍት ከውጫዊ መልካቸውና ከቅርጻቸው ጀምረው እስከ ውስጣዊ የአጻጻፍ ስልትና ሥዕላ ሥዕላዊ ቅንብሮች ድረስ ጥራ ቅርጽ የያዙና ተማሪዎችን መሳብ የሚችሉ መሆን አለባቸው። ይህን አስመልክቶ ሸልደን / 1987 / መማሪያ መጽሐፍ አጠቃላይ ሁኔታው የሚስብ መሆን እንዳለበትና አንዱ ደራሲ ፣ መማሪያ መጽሐፍ ውጤታማ እንዲሆን ቅርጹ ፣ ያአጻጻፍ ስልቱና ሥዕላዊ ቅቦቹ ሁሉ አስፈላጊ መሆናቸውን ማወቅ ተገቢው መሆኑን ይገልጻል። በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ የመማሪያ መጻሕፍት ተጠቃሚያች በቀለማት ያሸበረቁና የሚያነቃቃ መጽሐፍ እንደሚፈልጉ ፀሐፊው ይጠቅስና ደራሲያን መጽሐፍ በሚያዘጋጁበት ጊዜ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው ያብራራል። ነገር ግን በብዙ መንገዶች ከላይ የተጠቀሱት መሠረታዊ ጉዳዮች አስፈላጊውን ትኩረት እንደማያገኙ የመጽሐፍ ዋነኛ ባለቤት የሆኑት ተማሪዎችም እንደማይታወሱ ያስረዳል። በመሠረቱ ከተጠቃሚያች ፍላጎት ውጭ የሚዘጋጁ መጽሐፍ ፋይዳ ሊኖረው አይችልም። እንዲያውም ተማሪዎች በመጽሐፍም ሆነ በትምህርቱ ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲያሳድሩ ያደርጋል። ስለዚህ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ መሠረታዊ የሆኑ መስፈርቶችን ማሟላት ይኖርበታል።

በሸልደን / 1987 / አገላለጽ አንዱ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት:-

- በቂ የቋንቋ ዕውቀቶችን የያዘና ተማሪዎችን በደንብ የሚመራ፣
- ለተማሪው ነፃነት ሰጥቶ የሚያሠራ ፣
- ከተማሪዎች ፍላጎትና ዝንባሌ አኳያ የተዘጋጀ ፣
- ከተማሪዎች የአጥርና የረጅም ጊዜ ዓላማ ጋር ተጣጥሞ የሚሄድ ፣
- የቋንቋ ዘርፎችን በሚገባ አመጣጥኖ የሚይዝ፣
- ከጊዜ ጋር የተመጣጠነ ፣
- የተማሪዎችን ገላጊ ስሜት የሚጠብቅና የሚማርክ ፣

- ለክፍል ውስጥ የትምህርት ሂደት የተመቻቸ፣
- ተማሪዎችን ለውይይትና ለችግር ፈቺነት የሚጋብዝ።

አንዱ የቋንቋ ተማሪ መማሪያ መጽሐፉን በግሉ ማግኘትና እንደ ልቡ መጠቀም መቻል አለበት። ካለመማሪያ መጽሐፍ የቋንቋ ትምህርት ተፈላጊውን ግብ ሊመታ አይችልምና። ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ለሁሉም ተማሪዎች በግል መዳረስ ይኖርባቸዋል፡፡

የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ለሁሉም ተማሪ ቢዳረስ መልካም ውጤት እንደሚኖረው ካይሉዶስ / 1989 : 155 / ሲጽፍ "የመጻሕፍትና የሌሎች ትምህርታዊ ቁሳቁሶች ችግር ካለ የትምህርቱ ተቀባይነትና ውጤት ዝቅ ይላል። እያንዳንዱ ተማሪ በግሉ መጽሐፍ ካገኘ ግን የትምህርቱ ተቀባይነትና ውጤቱም ከፍ ይላል ..." ይላል።

ስለዚህ የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት በተማሪዎች አመለካከት ላይ ተፅዕኖ የማድረግ ኃይል ያላቸው መሆናቸው ታውቆ በዝግጅት ላይ ትኩረት ሊሰጣቸውና ለያንዳንዱ ተማሪ በግል መዳረስ መቻል ይኖርባቸዋል።

## 2.4.4 ት/ቤቶች ፣ መማሪያ ክፍሎች ፣ ድጋፍ ሰጪ ነገሮችና ዘዴዎች፣

በተማሪው ስብዕና ቀረጻ ላይ ድርሻ ካላቸው ነገሮች ት/ቤት ዋነኛና ከፍተኛ ድርሻ ያለው መሆን ይኖርበታል። ይህን በተመለከተ ኪምበስ/ 1968 : 17/ "... ት/ቤት ተማሪዎች ከየትም ሊያገኙ የማይችሉትን ነገሮች ማቅረብ ይጠበቅበታል ..." ይላል።

ት/ቤት ገና ሲመሠረት በታውቶ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡ ሄሪክና ሌሎች / 1956 : 239/ "በተቻለ መጠን ት/ቤት በመኖሪያ ቤቶች አካባቢ እንጂ በንግድና በኢንዱስትሪ አካባቢ መሠራት የለበትም፤ ምክንያቱም ሁካታና ግርግር ከትምህርት ጋር አይሄድምና..." ይላሉ።

እንግዲህ ከትምህርት ዓይነቶች አንዱ ቋንቋ እንደመሆኑ መጠን ተማሪው የቋንቋውን ትምህርት ለመማር የሚሄድበት ት/ቤት ያልተመቻቸና በተለያዩ ሁኔታዎች ተማሪውን የሚያስጠላ ከሆነ ተማሪው በት/ቤቱና በትምህርቱም ላይ አሉታዊ አመለካከት ሊያሳድር ይችላል።

ቸው፣በርና መስኮቶቹ የወላለቁና በብርዱ የሚያስመቁ፣ወዘተ. ከሆኑ ተማሪው ይጠላቸዋል ማለት ነው::

የትምህርት መሣሪያዎችና የማስተማር ዘዴዎችም የተማሪውን ስሜት ከኮረኮረው አዎንታዊ አመለካከት ሊያሳድሩ፣አሊያም ተማሪውን አስጠልተው አሉታዊ አመለካከት ሊፈጥሩ ይችላሉ:: ዳንኤል / 1964:39/ "ተማሪዎችን በትምህርት ቤትና በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚያጋጥሟቸው ነገሮች በባሕርያቸው ዕድገት ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል::..." ይላል:: ሃርመር /1983:5 / ስለመማሪያ ክፍሎችና ስለማስተማር ዘዴዎች ባንዱነት የሚከተለውን አቅርቧል::

መማሪያ ክፍሉ ወንበር የሌለው፣ብርዳም፣በተማሪ ብዛት የተጧበበና የሚወብቅ፣ የሠሌዳው ምቹ አለመሆንና የጽሑፉ አለመነበብ፣ወዘተ. ተማሪው ለትምህርቱ ያለውን አመለካከት አሉታዊ ሊያደርጉት ይችላሉ::

በሌላም በኩል የማስተማር ስልቱ ተማሪዎችን የሚያሳትፍና የማይማርክ ከሆነ ለትምህርቱ የመቀስቀስ ስሜታቸውን ይገላል:: በአንጻሩ የማስተማር ዘዴው የሚሰብና የሚማርክ ከሆነ ተማሪዎቹ ለቋንቋው ትምህርት ይነቃቃሉ፤ አዎንታዊ አመለካከትንም ያዳብራሉ::

በተጨማሪም "የማስተማር ዘዴ የተለያየና የሚቀያየር ከሆነ ተማሪዎችን ይስባል፤ ይማርካል:: ነገር ግን አንዱ ዓይነት ከሆነ አሰልቺና ተማሪዎችም ትምህርቱን እንዲጠሉ የሚያደርግ ይሆናል" ሃርመር / 1983 : 220 / ::

ኢሳይ /1986 : 5 / "በቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ አለመቻቸት ካለ ተሳታፊነትና ተገባቢነት ይቀንሳሉ" ይላል:: የሚፈለገው ትልቁ ነገር ተማሪዎች በትምህርት ላይ አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸውና በደስታ እንዲማሩ አስ ከሆነ ደረስ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች፣የማስተማር ዘዴውና የማስተሳሰሪያ ቋንቋውም ጥምር በተማሪዎቹ ችሎታና ፍላጎት ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል:: ይህንን በተመለከተ በውንትሬ / 1974 : 52 / "... ተማሪዎች እንዲማሩ የተፈለገው የትምህርት ዓይነት፣የማስተማሪያ ቋንቋውና ትምህርቱ የሚቀርብባቸው አጋዥ መሣሪያዎች ሁሉ በተማሪዎች ፍላጎት፣ችሎታና ዝግጁነት ላይ የተመሠረቱ መሆን ይኖርባቸዋል" ይላል::

የማስተማር ዘዴን በተመለከተ ሃርመር / 1983 : 5 / "ተማሪዎች

ዘዴው የማይስብና አሰልቺ ከሆነ ተማሪዎቹ ለመማር አይነቃቁም:: ነገር ገን ዘዴው ተለዋዋጭና ማራኪ ከሆነ ተማሪዎቹ ለመማር ይነቃቃሉ" ይላል:: እንደ ኪንንገስዎርዝ / 1984 / አገላለጽ የቋንቋ ማስተማሪያ ቁሳቁሶች:-

- ለዩ ለዩ የሆኑ በጥሪ ሁኔታ የሚያገለግሉ፣
- ወስህብነት ያላቸውና ስሜትን የሚነኩ፣
- ወደ ገሐ ተኪቶችና ወደ ትምህርት ውስጥ ሂደት የሚያደርሱ ተግባራትን ያቀፈ፣
- በቃት ያላቸዉ ወይም ችግር ፈቺ ጉዳዮች ያሉባቸውን ተግባራት የያዙ መሆን አለባቸው::

እንዴ የቋንቋ መምህር ጥሪ አጋዥ የሚሆኑትንና የትምህርቱን ዓላማ ከግቡ ሊያደርሱ የሚችሉትን ቁሳቁሶች መጠቀም ይጠበቅበታል:: ታዲያ በ ዋናነት የሚያገለግሉትንና በአጋዥነት የሚያገለግሉትን ለይቶ ማወቅ ተገቢው ይሆናል: / ኪንንገስዎርዝ 1984 : 50 /::

እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱትን ሐሳቦች ስናጠቃለል ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ላይ አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸውና ተደስተው እንዲማሩ ከ ተፈለገ ትምህርት ቤቱ መጫወቻ ሜዳዎችና በገና ቤት ያለው መሆን አለበት:: በመማሪያ ክፍሎችም ወንበሮች የተማሪዎች ወንበሮችና መስኮቶች በርዱ የማያስገቡ፣ ሠሌዳው ያልተበሳሳና በቀለም ያማረ መሆን አለበት:: በተጨማሪም ለቋንቋ ትምህርት የሚቀርቡት ዉጋፍ ሰጪ ነገሮች ዓላማውን ከግብ ሊያደርሱና ተማ ሪዎችን ሊቀሰቅሱ የሚችሉ መሆኑ ይኖርባቸዋል:: የማስተማር ዘዴውም በ የጊዜው የሚቀያየር፣ ተማሪዎችን የሚያሳትፍና የሚስብ መሆን አለበት::

ከዚህ ቀጥለን በአማርኛ ቋንቋ ዙሪያ የተሠሩ ቀደምት ሥራዎችን እንመለከታለን::

## 2.5 አማርኛንና የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት አስመልክቶ የተደረጉ የአመለካከት ጥናቶች፣

2.5.1 እንደርሰን እንደርስ በ1967 በኡፕሳላ / .. ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ተቋም ያደረገው ጥናት "

" Multilingualism and Attitude on Explorative Descriptive Study Among Secondary School Students in Ethiopia

በኢትዮጵያና በታንዛኒያ ያሉት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በእንግሊዝኛና በአገሪቱ ብሔራዊ ቋንቋ ላይ ያላቸውን አመለካከት ለመለካት ነው።

በአንደርሰን ጥናት የተጠኑት ሰዎች የሁለቱም አገሮች የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ሲሆኑ ከኢትዮጵያ አምስት መቶ ሃምሣ ዘጠኝ ተማሪዎች ተካፋይ ሆነዋል። ተማሪዎቹ የተመረጡት ከስድስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆን፤ ሦስቱ በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ፤ ሦስቱ ደግሞ ከአዲስ አበባ ውጭ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ነበሩ።

አጥኚው መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተጠቀመበት ዘዴ የጽሑፍ መጠይቆችን በመበተን ሲሆን የሚከተሉትን ውጤቶች መዝግቧል።

- በሁለቱም አገሮች በትምህርት ቤት ደረጃ ከብሔራዊ ቋንቋው ጋር እንግሊዝኛ ጠቃሚ ቦታ ያለው መሆኑን፤
- በሁለቱም አገሮች የጎሣ ቋንቋ ተናጋሪዎች ለብሔራዊ ቋንቋው ዝቅተኛ አመለካከት ያላቸው መሆኑን፤
- በሁለቱም አገሮች በትምህርት ቋንቋነት ከብሔራዊ ቋንቋ ይልቅ እንግሊዝኛ ተመራጭነት ያለው መሆኑን፤
- በኢትዮጵያ የከፍል ደረጃ በጨመረ ቁጥር ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አሉታዊ አመለካከት እየጨመረ የሚሄድ መሆኑን፤

በመጨረሻም አንደርሰን የሚከተሉትን አስተያየቶች ሰጥቷል።

- እንግሊዝኛ የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቋንቋ ስለሆነና፤ ተማሪዎችም ከፍተኛ አዎንታዊ አመለካከት ስላላቸው መንግሥት ለቋንቋው ልዩ ትኩረት ሊያደርግ ይገባል።
- አሁን ያለው ብሔራዊ ቋንቋ የሚቀጥል ከሆነ ቋንቋው ተቀባይነትን እንዲያገኝ አስፈላጊው ጥረት ሁሉ መደረግ ይኖርበታል። በተለይ ቋንቋቸው ከአማርኛ ውጭ የሆነ የጎሣ ቋንቋ ተናጋሪዎችን ማሳመን ተገቢ ነው።

2.5.2 ፀሐዬ ተፈራ በ1977 በጆርጅ ታውን ዩኒቨርሲቲ በሥነ ልሳን ትምህርት ለፒ.ኤች.ዲ. ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናት "A Sociolinguistic Survey of Language Use and Attitudes Towards Language in Ethiopia: Implications for Languages Policy in Education."

የቀረበ ሲሆን የጥናቱ ዋነኛ ዓላማ፣ ኢትዮጵያውያን ለትምህርትና ለቢሮ ሥራ ዎች እንዲሁም ከቢሮ ውጭ ላሉት ተግባራት በሚያገለግሉ ቋንቋዎች ላይ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅና ውጤቱን በወቅቱ ካለው እንዲሁም ወደፊት ሊኖር ከሚገባው የትምህርት ፖሊሲ ጋር ለማዛመድ ነው።

በጽሑፉ የተጠኑት ሁለት መቶ አሥራ አንድ ሰዎች ሲሆኑ በወቅቱ በነበረው የትምህርት ሥርዓት ውስጥ በማገልገል ላይ የነበሩ ቢሮክራቶች ፣ የዩኒቨርሲቲ መምህራንና ተማሪዎች ፣ እንዲሁም የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም መምህራን ናቸው። ከተማሪዎቹ ዘጠና ሰባቱ በአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች በመማር ላይ የነበሩ ናቸው። የጥናቱ ተካፋዮች ከጾታ ስርጭት አኳያ ሲታዩ 91%. ወንዶችና 9%. ሴቶች ሲሆኑ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አኳያ ደግሞ በአራት ቡድን የተከፈሉ ናቸው።እነሱም፡-

- በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ = 41.7%
- በትግርኛ ቋንቋ " " = 33.4%
- በኦሮምኛ ቋንቋ " " = 11.4%
- በሌሎች ቋንቋ " " = 13.5% ናቸው።

ፀሐፊ መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀመበት ዘዴ የጽሑፍ መጠይቆችን በመበተን ሲሆን የሚከተሉትን ውጤቶች መዝገቧል።

- የአፍ መፍቻ ቋንቋ የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን የብዙዎች ፍላጎት መሆኑን፣
- አብዛኛዎቹ መላሾች የአፍ መፍቻ ቋንቋ የሁለተኛ ደረጃና የዩኒቨርሲቲ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን አለመደገፋቸውን፣
- አብዛኛዎቹ መላሾች እንግሊዝኛ የሁለተኛ ደረጃና የዩኒቨርሲቲ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን መደገፋቸውን፣
- አብዛኛዎቹ መላሾች አማርኛ አፊሴላዊ ቋንቋ እንዲሆንና ኦሮምኛና ትግርኛም ሁለተኛና ሦስተኛ አፊሴላዊ ቋንቋ እንዲሆኑ መደገፋቸውን፣
- የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጡ የሚወደድ ዓይነት አለመሆኑን፣

ፀሐፊ ከነዚህ የጥናቱ ውጤቶች በመነሳት የሚከተሉትን አስተያየቶች ሠን

- አማርኛን በአፍ መፍቻነትና በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ የተለያዩ ወገኖች እንዳሉ እየታወቀ፣ አንድ ዓይነት መጻሕፍትና መርጃ መሣሪያዎችን እየተጠቀሙ ማስተማር ጥሩ አይደለም። ስለዚህ አማርኛ አፍ መፍቻቸው የሆኑትንና ሌሎችን በተለያዩ መሣሪያዎችና ዘዴዎች ማስተማር ተገቢ ሲሆን በሌላም በኩል ቋንቋውን ሳይሆን ስለቋንቋው ሰዋስው ማስተማሩ አይጠቅምም ብቻ ሣይሆን፣ ተማሪዎቹ ትምህርቱን እንዲጠሉት ያደርጋል። ስለሆነም በዚህ ላይ ትኩረት ማድረግና ሁለቱ ወገኖች በተለያየና በዘመናዊ መልክ እንዲማሩ ቢደረግ፣
- ተማሪዎች ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል ድረስ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ቢማሩና፣ በሁለተኛና ሦስተኛ ክፍል ላይ አማርኛን እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ቢማሩ፣
- አምስተኛና ስድስተኛ ክፍል ላይ አማርኛ እንደ ረዳት የማስተማሪያ ቋንቋ ቢያገለግል፣
- የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከሰባተኛ እስከ አሥረኛ ክፍል ድረስ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ቢሰጥ፣
- አማርኛ ለሰባተኛና ለስምንተኛ ክፍሎች የትምህርት ቋንቋ ቢሆንና ከዘጠነኛ እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ብቻ ቢሰጥ፣
- እንግሊዝኛ ከዘጠነኛ ክፍል እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ የትምህርት ቋንቋ ቢሆን።

2.5.3 ብርሃኑ ገብረማርያም በ1976 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናት "ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያሏቸው አመለካከት በስድስት የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች" የሚል ሲሆን ዋነኛ ዓላማው፣

- በወረ ደረጃ ። ተማሪዎች ትምህርቱን አይወዱም፣ መምህራንም ገዱ የሏቸውም ፣ ስለዚህ በተለይ የአማርኛ ቋንቋ መምህር መሆን አያስደስትም ። የሚለውን ጠሳብ በጥናት ለማረጋገጥ፣
- ተማሪዎች በትምህርቱ ላይ ያላቸውን አመለካከት ፣ መምህራን በዝግጅትና በአቀራረብ ረገድ የሚታይባቸውን ድክመትና ጥንካሬ ለማወቅና ትክክለኛውን የማስተማር አቅጣጫ ለመወሰን፣
- መምህራንን የሚመለምሉና የሚያሠለጥኑ ተቋሞች ፣ የሥርዓተ ትምህርት አዘጋጆችና የትምህርት ከፍተኛ ባለሙያዎች፣ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ላይ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅና አስፈላጊውን ዕቅድ አውጥተው እንዲሠሩ ለማሳሰብ፣
- ለቋንቋ የተሳሳተ ትርጉም የሚሠጡ ሰዎች ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ጠሳብ ለማቅረብ ነው።

የብርሃኑ ጥናት ተሳታፊዎች አምስት መቶ ሰላሳ አምስት ተማሪዎችና አርባ ሰምንት መምህራን ሲሆኑ ከስድስት ትምህርት ቤቶች የተመረጡ ናቸው።

- ኮሰሬ አጠቃላይ
- እንጦጦ አጠቃላይ
- ዳግማዊ ምኒሊክ
- መድኃኒዓለም አጠቃላይ
- ንፋስ ስልክ አጠቃላይ
- የካቲት አሥራ ሁለት ናቸው።

ብርሃኑ መረጃዎችን የሰበሰበው በሁለት ዘዴዎች ተጠቅሞ ነው። አንደኛ የጽሑፍ መጠይቆችን ለተማሪዎችና ለመምህራን በማቅረብ ፣ ሁለተኛ የክፍል ትምህርት ምልከታ በማድረግ ነው።

የብርሃኑ የጥናት ውጤቶች የሚከተሉት ናቸው:_

- አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይልቅ የእንግሊዝኛን ቋንቋ ትምህርት የሚወዱ መሆናቸውን፣
- ከሴቶች ይልቅ ወንዶች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተሻለ አመለካከት ያላቸው መሆኑን፣
- ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ጋር ሲታያይ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ መሆኑን፣
- ተማሪዎች አማርኛ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን አለመ

– የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከፍተኛ የሥነ ልቦና ችግር እንዳለባቸውና በሙያው ውስጥ የገቡበትን ቀን እድሜ ልካቸውን እየረገሙት የሚኖሩ መሆናቸውን::

ብርሃኑ የሚከተሉትን አስተያየቶች ሰጥቷል፤

- የሚመለከታቸው ክፍሎች የመምህርነት ሙያ ክቡር ከሆኑት የአገር ግንባታ ሥራዎች አንዱ እንደሆነ ሕብረተሰቡ እንዲያውቅ ማድረግ አለበት:: መምህራን ከኢኮኖሚና ከሥነ ልቦናዊ ጉስቁልናቸው እንዲላቀቁ መንግሥት አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ይኖርበታል:: መምህራንም ክቡር ግዳጃቸውን በሚገባ እንዲወጡት በጥንቃቄ መመልመል፤ በጥራት ማሠልጠንና በብቃት ማዘጋጀት፤ በሥራ ላይ ከተመደቡም በኋላ በሙያቸው እያደጉ እየበለፀጉ እንዲሄዱ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ያሻል / ገጽ 126/::
- በአገራችን አንድ ቋንቋ መናገር የሚችል ሰው "ቋንቋውን ያውቀዋልና መማር አያስፈልገውም" የሚል ግምት በብዙ ሰዎች ዘንድ አለ:: ከዚህ የተነሳ ... አማርኛን በመማር እንዳችም አዲስ ነገር ሊገኝ እንደማይችል ተደርጎ ሲነገር እንሰማለን:: ይህ ስህተት ነው:: አንድ ሰው የሚያውቀውን ቋንቋ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ በተለያዩ የጥልቀት ደረጃ ሊማረው ይችላል:: ስለዚህ ይህ የተሳሳተ አመለካከት መወገዱ ይኖርበታል::

2.5.4 ወርቁ በሻዳ በ1982 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናት "የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የማስተማሪያ ቋንቋ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ቢለወጥ በተማሪዎችና በመምህራን ዘንድ ያለውን አመለካከት ለማወቅ በአምስት የአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተደረገ ጥናት" የሚል ሲሆን የጥናቱ ዓላማ፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የማስተማሪያ ቋንቋ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ቢለወጥ ተማሪዎችና መምህራን ምን ዓይነት አመለካከት ሊኖራቸው እንደሚችል ለማወቅ ነው::

በጥናቱ የታቀፉት ስድስት መቶ ሃያ አንድ ተማሪዎችና ስልሳ አራት መምህራን ሲሆኑ የተመረጡት ከአምስት የአዲስ አበባ ከፍተኛ

ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነው:: ትምህርት ቤቶቹም:=

- ዳግማዊ ምኒልክ
- ነፋስ ስልክ አጠቃላይ
- አዲስ ከተማ አጠቃላይ
- ኮልፌ አጠቃላይና
- ቀጨኔ ደብረ ሰላም ናቸው::

ወርቁ መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀመበት ዘዴ የጽሑፍ መጠይቆችን ለመምህራንና ተማሪዎች በመበተን ሲሆን የሚከተሉትን ውጤቶች መዝግቧል፤

- አማርኛ ቋንቋ የሁለተኛ ደረጃ ይፋ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን የተሠነዘረ ሐሳብ በአብዛኛው ተማሪዎችና መምህራን ዘንድ ተቀባይነት አለማግኘቱን፤
- በአሁኑ ጊዜ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የማስተማሪያ ቋንቋ "እንግሊዝኛ ነው" ቢባልም እየተሠራበት ያለው ቋንቋ ግማሽ በግማሽ አማርኛ ሆኖ መገኘቱን፤
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቶችን ለመከታተል የማያስችል መሆኑን፤
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቶች በእንግሊዝኛ ቋንቋ መሰጠታቸው መጠነኛ ጉዳት ማስከተሉን፤

ወርቁ በጥናቱ መጨረሻ ላይ የሚከተሉትን አስተያየቶች አቅርቧል፤

አማርኛ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን ያልተደገፈባቸው ምክንያቶች በርካታ ቢሆኑም ጥቂቶቹ፤

- አማርኛ ስሳልዳበረ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ፅንሰ ሐሳቦችን መግለጽ አይችልም፤
- አማርኛ አለም ዓቀፋዊ ባሕርይ ስለሌለው ሩቅ አያስኬድም ወዘተ... የሚሉ ናቸው፤ ዋናው ቁም ነገር፤ የሚሰጠውን ትምህርት መረዳት፤ማወቅ እንጂ፤ ቋንቋውን ዓለም ይጠቀምበታል፤አይጠቀምበትም የሚለው አይደለም:: ስለዚህ የዚህ ዓይነቱን አመለካከት በትምህርት መስጥ ስለሚቻል ተገቢው ትኩረት ይሰጠው፤
- የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ትምህርቶችን በእንግሊዝኛ ቋንቋ መከታተል ስለማይችሉ የሁለተኛ ደረጃን የትምህርት ቋንቋ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ለመወጥ የመንግሥት ውሣኔ ያስፈልጋል፤

- አማርኛ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን ከተወሰነ፤ በየደረጃው በአማርኛ የተዘጋጁ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ማቅረብ፣ ተርጓሚዎችን ማስፋፋት፣መምህራንን ማሠልጠን፣ሴሚናሮችን ማዘጋጀት፣ ሕዝቡንም ማሳተፍና፣ከሁሉም በላይ፣በበላይነት የሚቆጣጠር ተጠሪ አካል ማቋቋም ያስፈልጋል።

እነዚህ አጥኚዎች የተለያዩ ዓላማዎችን ይዘው በመነሳታቸው የተለያዩ ውጤቶችን መዝገበዋል፤ ይሁን እንጂ በሁሉም የጥናት ውጤቶች ላይ አማርኛ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን አለመፈለጉ ተገልጿል፤ ምክንያቱ ምን ይሆን? ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ከዚህ ጥናት የተገኘውን ውጤት ከምዕራፍ አራት ማግኘት ይቻላል።

ከዚህ ቀጥለን አጥኚው መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተጠቀመበትን የጥናት ዘዴ እንመለከታለን።

# ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ዘዴ

### 3.1 ናሙናዎችና መገለጫዎች

#### 3.1.1 ተማሪዎች

በጥናቱ ናሙናነት እንዲታቀፉ የተመረጡትበአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ የአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ፣ የዚህ ክፍል ተማሪዎች የተመረጡበት ምክንያት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ማዕከላዊ ደረጃ ላይ የሚገኙና አንፃራዊ በሆነ መልኩ በዕድሜና በትምህርት በኩል ተማሪዎች በመሆናቸው ነው:: የሌሎቹ ክፍል ተማሪዎች የዚህን ክፍል ተማሪዎች ያህል ምቹ አይደሉም:: ለምሣሌ የአሥራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ለብሔራዊ ፈተና ስለሚዘጋጁና አጥኚው መረጃ በሚሰበስብበት ወቅት በትምህርት ቤቶች ሊገኙ ስለማይችሉ፣ በጥናቱ ሊታቀፉ አይችሉም:: የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ገና ከመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጡና በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በቂ ልምድ የሌላቸው በመሆናቸው በጥናቱ አልታቀፉም:: የአሥረኛ ክፍል ተማሪዎች በመሐል ያሉና መጠነና ልምድ ያላቸው ቢሆኑም የአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች በሰስተም ደረጃዎች /9,10,11/ ውስጥ ያለፉ፣ ከአሥረኛ ክፍል ተማሪዎች ይበልጥ ልምድ ያካበቱና በዕድሜም የበሰሉ በመሆናቸው ሊመረጡ በቅተዋል::

#### 3.1.2 መምህራን

በጥናቱ እንዲሣተፉ በናሙናነት የተመረጡት መምህራን በየትምህርት ቤቶቹ የሚገኙ የአሥራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው:: የአሥራ አንደኛ ክፍል መምህራን የተመረጡበት ምክንያት ከላይ እንደተገለፀው በናሙናነት የተመረጡት የአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ስለሆኑና መልሶቻቸውን ከአስ ተማሪዎቻቸው አስተያየት ጋር ማነፃፀር አስፈላጊ በመሆኑ ነው::

3.1.3 ትምህርት ቤቶች

በጥናቱ ውስጥ በናሙናነት የታቀፉት ከየዞኑ የተመረጡ ስድስት የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ ሌሎች የግል፣ የኮሚዩኒቲና የቴክኒክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በጥናቱ አልታቀፉም:: እነዚህ ትምህርት ቤቶች ያልታቀፉበት ምክንያት እንደየትምህርት ቤቶቹ ዓይነት ይለያያል::

1. በአዲስ አበባ የሚገኙ የግል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሐብታሞችና የዲፕሎማት ልጆች ብቻ የሚማሩባቸው በመሆናቸውና የቋንቋ ትምህርት ትኩረታቸውም ሲታይ ቀድሞውኑ ወደ እንግሊዝና አዘንብሉ ስለሚታይ፣ለብዙሃን የአዲስ አበባ ተማሪዎች ናሙና ሊሆኑ አይችሉም::

2. በአዲስ አበባ የሚገኙ የኮሚዩኒቲ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ገና ከጅምሩ ለየዜጎቻቸው ልጆች መማሪያ እንዲሆኑ የተቋቋሙ ስለሆኑ፣ጥቂት የሐብታም ኢትዮጵያዊያን ልጆች ቢደባለቁባቸውም፣ልዩ ትኩረታቸው ለየሐገርቻቸው ባህልና ቋንቋ ስለሆነ ለአማርኛ ቋንቋ እምብዛም ቦታ አይሰጡም:: ስለሆነም ጥሩ ናሙና ሊሆኑ አይችሉም::

3. በአዲስ አበባ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶች ልዩ ትኩረትና አላማቸው ለቴክኒክና ለሙያ ዕውቀት ስለሆነ ለአማርኛም ሆነ ለሌሎች የቀለም ትምህርቶች ግድ የላቸውም:: በመሆኑም እነዚህም ናሙና ሊሆኑ አይችሉም::

ስለዚህ ከላይ እንደተገለፀው የአዲስ አበባ ብዙሃን ተማሪዎች የሚማሩባቸው ትምህርት ቤቶች የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመሆናቸው ለጥናቱ ናሙና ሆነው ተመርጠዋል::

እነዚህ ትምህርት ቤቶች ከየዞኑ የተመረጡት በዕጣ ሲሆን ዝርዝራቸውን ከሚከተለው ሠንጠረዥ መመልከት ይቻላል::

ሠንጠረዥ አንድ

ከየዞኑ የተመረጡ ትምህርት ቤቶች

| ተ.ቁ. | የትምህርት ቤቱ ስም | ዞን |
|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 1 |
| 2 | ኤስ.ኦ.ኤስ. ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 2 |
| 3 | ወንድራድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 3 |
| 4 | ኢትዮጵያ ትቅደም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 4 |
| 5 | ጥቁር አንበሳ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 5 |
| 6 | አቃቂ አጠቃላይ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 6 |

## 3.2 የጥናቱ ተሳታፊዎች

### 3.2.1 ተማሪዎች

ከላይ በተጠቀሱት ስድስት ትምህርት ቤቶች አራት ሺህ ሁለት መቶ ሃያ አንድ የአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች አሉ:: ከእነዚህ ውስጥ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ስድስት ተማሪዎች ወንዶች ሲሆኑ ሁለት ሺህ ሃያ አምስት ተማሪዎች ሴቶች ናቸው። የናሙና ተማሪዎችን አመራረጥ በተመለከተ ፣ ከየትምህርት ቤቱ አንድ የሳይንስና አንድ የአርት ክፍል በነሲብ ከተመረጠ በኋላ፣ከየክፍሉ አርባ ተማሪዎች በድምሩ ሰማንያ ተማሪዎች እንደዚሁ በነሲብ ተመርጠው መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርገዋል:: በዚህ መሠረት መጠይቁ በስድስቱም ትምህርት ቤቶች ለአራት መቶ ሰማንያ ተማሪዎች ከተበተነ በኋላ በትክክል ያልተሞሉ ስልሳ ወረቀቶች ተወግደው የአራት መቶ ሃያ ተማሪዎች ምላሽ በጥናቱ ታቀፏል:: ተሳታፊ ተማሪዎች ከጾታ ስርጭት አኳያ ሲታዩ፣ሁለት መቶ ሃምሳ ሁለቱ/60%/ወንዶችና አንድ መቶ ስልሳ ስምንት/40%/ሴቶች ናቸው:: ለዝርዝሩ ሠንጠረዥ ሁለትን ይመልከቱ::

ሠንጠረዥ ሁለት

በትምህርት ቤቶቹ የሚገኙ ተማሪዎችና ለናሙና የተመረጡ ተማሪዎች

| ተ.ቁ. | ትምህርት ቤት | በትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች | | | ለናሙና የተመረጡ ተማሪዎች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ድምር | ወ | ሴ | ድምር |
| 1 | ከፍተኛ አራት ትምህርት ቤት | 548 | 462 | 1010 | 35 | 35 | 70 |
| 2 | ኢስ.ኦ.ኢስ ትምህርት ቤት | 216 | 174 | 390 | 44 | 26 | 70 |
| 3 | ወንደራድ ትምህርት ቤት | 307 | 487 | 794 | 37 | 33 | 70 |
| 4 | ኢትዮጵያ ትቅደም ትምህርት ቤት | 300 | 360 | 660 | 42 | 28 | 70 |
| 5 | ጥቁር አንበሳ ትምህርት ቤት | 445 | 310 | 755 | 44 | 26 | 70 |
| 6 | አቃቂ ትምህርት ቤት | 380 | 232 | 612 | 50 | 20 | 70 |
| | ድምር | 2196 | 2025 | 4221 | 252 | 168 | 420 |

3.2.2 መምህራን

ቢመረጡት ትምህርት ቤቶች አርባ አራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚገኙ ቢሆን በሳባ አራቱ ወንዶች፣ አሥሩ ቢቶች ናቸው:: ከነዚህ ውስጥ ከየትም አሥራ ሁለት የአሥራ አንደኛ ክፍል መምህራን ለቃለ መጠይቅ ተመርጠዋል:: ከየትም የሚያስተምሩ ለናሙና የተመረጡትን ክፍሎች የሚያስተምሩ ህርት ቤቱ የተመረጡት መምህራን፣ ለናሙና የተመረጡትን ክፍሎች የሚያስተምሩ ህርት ቤቱ የተመረጡት መምህራን፣ ለናሙና የተመረጡትን ክፍሎች ተጠሪዎች ናቸው:: ለዝርዝሩ ሠንጠረዥ መምህራንና የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተጠሪዎች ናቸው:: ለዝርዝሩ ሠንጠረዥ ሦስትን ይመልከቱ:: -

ሠንጠረዥ ሦስት

በትምህርት ቤቶቹ የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና በቃለ መጠይቅ ላይ የተሳተፉ ናሙና የአሥራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን

| ተ.ቁ | ትምህርት ቤት | የአማርኛ መምህራን | | | የትምህርት ደረጃ | | በቃለ መጠይቅ የተሳተፉ የአሥራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ድምር | ጎንደሬ | ጎንደሌም | ወ | ሴ | ድም |
| 1 | ከፍተኛ አራት | 12 | 2 | 14 | 9 | 5 | 1 | 1 | 2 |
| 2 | ኢስ.ኦ.ኢስ | 3 | 3 | 6 | 4 | 2 | 2 | - | 2 |
| 3 | ወንደራድ | 7 | 3 | 10 | 6 | 4 | 2 | - | 2 |
| 4 | ኢትዮጵያ ትቅደም | 5 | 1 | 6 | 4 | 2 | 2 | - | 2 |
| 5 | ጥቁር አንበሳ | 4 | - | 4 | 2 | 2 | 2 | - | 2 |
| | | | | | | | 1 | 1 | 2 |

## 3.3 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

እንደ ጥናት መለያየት ሁሉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ይለያያሉ:: ይህ ጥናት የተማሪዎችን ዝንባሌ ለማወቅ ዓላማ አድርጎ የተነሣ በመሆኑ ለዝንባሌ ጥናት ምቹ የሆኑ ዘዴዎችን መምረጥ ግድ ይሆንበታል::

ታርገና ያሰ / 1989:134/፣ኪቻን /1967:76/፣ስፖሊስኪ /1989/149/ "የተማሪዎችን አመለካከት ለማወቅ ግልጽ የሆነው መንገድ እነሱኑ መጠየቅ ነው" ይላሉ:: ከጥያቄ በተጨማሪ የተማሪዎችን አመለካከት ለማወቅ የምልከታን ሂደት መጠቀም እንደሚቻል ታርገና ያሰ /1989:37/ ይገልጿሉ:: የአንድን ሰው ዝንባሌ ለማወቅ ለሰውየው ለራሱ ከሚቀርብለት ጥያቄ በተጨማሪ ሁኔታዎችን በአይን ተመልክቶ መረጃ ማግኘት እንደሚቻል ከላይ የቀረበውን ሐሳብ በመጠናከር የብሪታኒካ ኢንሳይክሎፒዲያ / 1986:687/ ሲገልጽ "አንድ ሰው ዝንባሌው የሚታወቀው ሊታይ ከሚችለው ሁኔታና ለግምገማ ከሚሰጠው ምላሽ ነው" ይላል::

በዚህ መሠረት አጥኚው የተማሪዎችን አመለካከት ለማወቅ ሶስት ዘዴዎችን ተጠቅሟል::

1. ለተማሪዎች በተለያየ መልክ የተዘጋጀ የጽሑፍ መጠይቅ በማቅረብ ነፃ ሐሳባቸውን እንዲሰጡ በማድረግ::
2. ለመምህራን ቃለ መጠይቅ በማቅረብ ስለተማሪዎቻቸው የሚያውቁትንና ያዩትን እንዲናገሩ በማድረግ::
3. በትምህርቱ ሂደት ላይ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል ለማወቅ የክፍል ትምህርት ምልከታ በማድረግ::

### 3.3.1 የጽሑፍ መጠይቆች ሁኔታ

ኋኒንና አለጠቶይን / 1986:17/ "የአመለካከት ጥያቄዎች ዝግ/close / መሆን ሲኖርባቸው በጣም ጥቂቶቹ ብቻ ክፍት ይሆኑና ለሌሎች መጠይቆች ድጋፍ ሰጪ በመሆን ለአጥኚው ያገለግላሉ" ይላሉ:: በዚህ መሠረት የጽሑፍ መጠይቆቹ ለ ቋንቋ የአመለካከት መለኪያ ምቹ እንዲሆኑ አማራጭ መልሶቹ ዝግ ሆነው አምስት ነጥብ ደረጃ ባላቸው የሊከርት አፀፋፍ ስልት እንዲቀመጡ ተደርጓል:: በተጨማሪም ሐሳቡን የሚያዳብሩና ለ [illegible] ክፍት / open / ጥያቄዎችም

ታቀፈዋል:: / አባሪ "ሀ" ከገጽ 1 - 10 ይመለከቱ/

እነዚህ ዝግ ጥያቄዎች የሆኑ አምስት ነጥቦች ደረጃ ያሏቸው የሊከርት አፀፋፍ ስልቶች ከአዎንታዊና ከአሉታዊ ጠሳቦች አኳያ አማራጮቹ የተለያዩ ነጥቦችን እንዲሸከሙ ተደርጓል:: ለዚህ አባባል የሚከተለውን መግለጫ እንመልከት::

1. ስምምነትን የሚጠይቀው ዐረፍተ ነገር አዎንታዊ ከሆነ የነጥብ አሰጣጡ እንደሚከተለው ይሆናል::

- በጣም እስማማለሁ = አምስት ነጥብ
- እስማማለሁ = አራት ነጥብ
- መወሰን ያስቸግረኛል = ሶስት ነጥብ
- አልስማማም = ሁለት ነጥብ
- ፍጹም አልስማማም = አንድ ነጥብ

2. ስምምነትን የሚጠይቀው ዐረፍተ ነገር አሉታዊ ከሆነ የነጥብ አሰጣጡ እንደሚከተለው ይሆናል::

- በጣም እስማማለሁ = አንድ ነጥብ
- እስማማለሁ = ሁለት ነጥብ
- መወሰን ያስቸግረኛል = ሶስት ነጥብ
- አልስማማም = አራት ነጥብ
- ፍጹም አልስማማም = አምስት ነጥብ

በሁለቱም በኩል ከፍተኛው ነጥብ አዎንታዊነትን፣ዝቅተኛው ነጥብ አሉታዊነትን ያመለክታል:: ሶስት ለሁለቱም ጠሳቦች ማዕከላዊ ነጥብ ሆኖ ወደ አምስት እየወጣ በሄደ ቁጥር አዎንታዊ ጠሳቡ ከፍተኛ መሆኑን ሲያመለክት ወደ አንዱ እየወረደ በሄደ ቁጥር ደግሞ አሉታዊ ጠሳቡ ጠንካራ መሆኑን ያመለክታል:: /ፔይን 1992:457/፣ መደጠኑ ኃይለጊዮርጊስ 1986:24/

የዚህ ጥናት አቀራቢ መጠይቁ በሚዘጋጅበት ጊዜ አዎንታዊና አሉታዊ የሆኑት ዓረፍተ ነገሮች ተደባልቀው ተራ በተራ እንዲገኙ አድርጓል ይህም የሆነበት ምክንያት አንደኛው ወገን በዝቶ ወይም ተከታታይ ሆኖ በመላሾቹ ሥነ_ልቦና ላይ ተፅዕኖ በማድረግ መረጃዎችን እንዳያዛባ ነው። የጥያቄዎቹም አቀማመጥ ተጠየቃዊ ቅደም ተከተል ስለሌለው የአንዱ መልስ በሌላው ላይ ምንም ዓይነት ተፅዕኖ የለውም።

መጠይቁ አምስት የተለያዩ ተለዋጮችን / Variable / አቀፏል። እነሱም:_ ተለዋጭ 1. የተማሪው የገለ አጠሳካከት፣

ተሳውጥ 2. የወሳጆች፣የህብረተሰብና የእኩዮች አመለካከት፣

ተሳውጥ 3. የአማርኛ ቋንቋ መምህር ጠባይ፣ ችሎታና አመለካከት፣

ተሳውጥ 4. የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ሁኔታ፣

ተሳውጥ 5. ት/ቤቶች ፣ መማሪያ ክፍሎች ፣ ድጋፍ ሰጪ ነገሮችና የማስተማር ዘዴዎች ናቸው።

3.3.2 የቃለ መጠይቆች ሁኔታ

ለመምህራን በቀረበው ቃለመጠይቅ ውስጥ የቀረቡት ጥያቄዎች ስድስት ናቸው። / አባሪ " ለ " ን ይመልከቱ/። በምልለሱ ወቅት መምህራን የሚሰጡትን አስተያየት ሁሉ እንዳለ በጽሑፍ ለማስቀረት አስቸጋሪ ስለሚሆን የምልለሱ ሂደት በካሤት እንዲቀረፅ ከተደረገ በኋላ ወደ ጽሑፍ ተለውጦ ቀርቧል።

3.3.3 የትምህርት ህደት ምልከታ ሁኔታ

የክፍል ትምህርት ምልከታን በተመለከተ አጥኚው በየት/ቤቶቹ ካሉት አሥራ አንደኛ ክፍሎች አንዱ የአርትና አንዱ የሳይንስ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን በሚማሩበት ጊዜ ተመልክቷል።

ይህ የክፍል ምልከታ ያስፈለገበት ምክንያት በትምህርቱ ሂደት ላይ የተማሪዎች ተሳትፎና የመምህሩ ጥረት ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅና በተጨማሪም ተማሪዎች ትምህርቱን ወደውና ፈቅደው ከልብ መቀበል አለመቀበላቸውን፣ መምህሩም በደንብ ማቀረብ አለማቀረቡን ለማረጋገጥ ነው። በሌላ በኩል የክፍሉ አጠቃላይ ሁኔታ ለመማር ምቹ መሆን አለመሆኑን ፣ በተማሪዎቹ ከሚቀርቡት መረጃ በተጨማሪ በአይን አይቶ ለማረጋገጥ ነው።

3.4. የመጠይቁ ስርጭት

የመጠይቁን ሥርጭትና አሞላል በተመለከተ አጥኚው ጥናቱ የሚመለከታቸው ትምህርት ቤቶች ሁሉ አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርጉ ከዩኒቨርስቲው ደብዳቤ አስጽፎ ወደየትምህርት ቤቶቹ በመንቀሳቀስ ከዲሬክተሮቹ ከዩኒት መሪዎቹ ጋር ተገቢውን ምክክር አድርጓል፤ቅድመ ሁኔታዎችን ሁሉ አመቻችቷል። መጠይቁ ከመቀሳቀሱ በፊት ከየትምህርት ቤቱ መጠይቁን እንዲሞሉ ለተመረጡ ተማሪዎች አጠቃላይ የመጠይቁን አሞላል በተመለከተና ለየት ባለ መልክ ለሚሞሉት

ተማሪዎቹ መጠይቁን የሞሉት እዚያው በት/ቤት አዳራሽ ውስጥ ተሰብስበው ነው። ይህ እንዲሆን የተደረገው፦

1. ተማሪዎቹ መጠይቁን ወደየቤታቸው ይዘው ከሄዱ ሊቀደዱ ወይም ሊጠፋባቸው ይችላል ከሚል ፍራቻ የተነሣ፤
2. መጠይቁን ከክፍል ውጭ ይዘው ከሄዱ ብዙዎቹ ተማሪዎች ተነጋገረው ተመሳሳይ መልስ ብቻ ይዘው ይመጣሉ ከሚል ፍራቻ የተነሳ፤
3. መጠይቁን ይዘው ከሄዱ አንዳንዱ ገለጽ ያልሆነላቸውን ጠሳብ አጥኚውን መጠጸቅ ስለማይችሉ ወደ ቱሳሰተ ግምታዊ መልስ ይሄዳሉ ከሚል ፍረቻ የተነሣ ነው።

ይህ አጥኚው የተጠቀመበት በገንቢር ቀርቦ መጠይቁን የማስሞላት ስልት ብክነትን ከመቆጣጠረም በላይ መረጃ ሰብሳቢው እዚያው ሆኖ የሚነሡ ጥያቄዎችን እየመለሰ በማስሞላቱ ከጥቂቶች በስተቀር አብዛኛዎቹ መጠይቁን በትክክል ሞልተዋል ።

## 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴዎች

ከተማሪዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ሁለት አብይ ክፍሎች አሏቸው፡፡ አንደኛው ፤ ስለተማሪው ማንነትና ስለቤተሰቡ ሁኔታ የሚገለፀው ዳራዊ መረጃ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ፤ ተማሪው በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያለውን አመለካከት የሚያመለክተ መረጃ ነው።

መረጃዎቹ ከተማሪዎች እንደተሰበሰቡ መለያ ቁጥር ተሰጥቷቸውና በየትምህርት ቤቶቹ ተለይተው " ታሊ " ተደርገዋል። በዚህ አሠራር የእያንዳንዱ ጥያቄ አማራጭ መልሶች በምን ያህል ሰዎች እንደተመረጡ ታውቆ ተመዝግቧል፤ የመቶኛና የአማካይ ነጥብ ስሌተም ተሠርቷል። ቀጥሎ እያንዳንዱ ተማሪ በያንዳንዱ ተለዋጭ ላይ ያገኘው ነጥብ ተለይቶ ከታወቀና ከተመዘገበ በኋላ፤ ለልዩ ልዩ ስታቲስቲካዊ ንፅፅር ወደ ኮምፒዩተር ተላከ። የዚህ ከንውን ዓላማ በትምህርት ቤቶች፤ በወንዶችና በሴቶች ፤ በሳይንስና በአርትስ፤ ተማሪዎች እንዲሁም በአማሮችና በሌሎች መካከል ስታቲስቲካዊ ፋይዳ ያለው የምላሽ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማነፃፀር ሲሆን፤ በተጨማሪነት ከሁለት እስከ አምስት ባሉት ተለዋጮች የተመዘገቡት ውጤቶች ከተለዋጭ አንዱ ውጤት ጋር ሊቀናጁ መቻል አለመቻላቸውን ለማወቅ ነው። ተለዋጭ አንዱ ከጥናቱ ርዕስ ጋር የተያያዘ ዋነኛ

ስለዚህ የእያንዳንዳቸው ውጤት ከተሰጣጭ አንድ ውጤት ጋር ምን ያህል ተጣምሮ እንዳለው መታየት ይኖርበታል።

በሌላ በኩል በያንዳንዱ ተሰጣጭ ላይ የተገኙት መረጃዎች በመጠይቁ ላይ በሰፈሩት ተራ ቁጥርና ቅደም ተከተል መሠረት እንደየባሕሪያቸው ሁኔታ በመቶኛና በአማካይ ነጥብ እየተጠቃለሉ ተተንትነዋል፤ በሠንጠረዦች ተቀነባብረው ቀርበዋል።

በመጨረሻም በቃለ መጠይቅ አማካይነት ከመምህራን የተሰበሰቡት መረጃዎች ከተማሪዎች ከተሰበሰቡት መረጃዎች ጋር እየተጣቀሱ ተብራርተዋል።

የአጥኚው የምልከታ ውጤቶችም ከዝረዘሩ በኋላ ከተማሪዎች ምላሾች ጋር እየተነፃፀሩ ተገልፀዋል።

3.6 ሠንጠረዦቹ መግለጫዎች፤

በሠንጠረዥ ሆነው ሊገለፁ የሚገባቸው ጉዳዮች ሁሉ በሠንጠረዥ ተዘርዝረው ቀርበዋል። በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥ አሥራ ሦስት ሠንጠረዦች የሚገኙ ሲሆን ከአንድ እስከ ሦስት ያሉት ሠንጠረዦች በምዕራፍ ሁለት ውስጥ የሚገኙና በናሙናነት ስለተመረጡት ትምህርት ቤቶች፣ ተማሪዎችና መምህራን የሚገልፁ ናቸው። ቀሪዎቹ አሥር ሠንጠረዦች በምዕራፍ አራት ውስጥ የሚገኙ ናቸው። ከነዚህም ሁለቱ ስለተማሪዎችና ስለቤተሰባቸው ዳራዊ መግለጫ የሚያቀርቡ ናቸው። ከሠንጠረዥ ሰባት እስከ አሥር ያሉት ደግሞ መላሾች ለምርጫቸው የሰጧቸውን ምክንያቶች የሚያቀርቡ ናቸው። ከሠንጠረዥ አሥራ አንድ እስከ አሥራ ሁለት ያሉትም የተማሪዎችን አስተያየት የሚያቀርቡ ሲሆን ሠንጠረዥ አሥራ ሦስት የተሰጣጮችን የርስበርስ ተጣማሪነት ያሳያል።

# ምዕራፍ አራት

## ውጤቶችና ማብራሪያዎች

### 4.1 የመላሾች አጠቃላይ ሁኔታ

ናሙና የሆኑት የመጠይቁ መላሾች ከስድስት ትምህርት ቤቶች የተመረጡና አራት መቶ ሃያ ተማሪዎች መሆናቸው በምዕራፍ ሦስት ተገልጿል። እነዚህን ተማሪዎች በፆታ ፣ በዕድሜ ፣ በሃይማኖት ፣ በብሔረሰብና በአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ እንዲሁም በቤተሰብ ገቢ፣በአባትና በእናት የትምህርት ደረጃና የሥራ ሁኔታ እኪያ እንመለከታለን።

#### 4.1.1 ፆታ

በናሙናነት የተመረጡት ተማሪዎች ሁለት መቶ ሃምሣ ሁለት /60 %/ ወንዶች ሲሆኑ አንድ መቶ ስልሣ ስምንት / 40%. / ሴቶች ናቸው። ይሁን እንጂ በየትምህርት ቤቱ የተገኘውን መረጃ ስንመለከት ቁጥሩ የተለያየ ሆኖ ይገኛል። ለዝርዝሩ ሠንጠረዥ አራትን ይመለከቱ።

#### 4.1.2 ዕድሜ

የናሙና ተማሪዎች ዕድሜ በአሥራ አምስትና በሃያ ዓመት መጠል ሲሆን በሁለት ተመደቧል። ከአሥራ አምስት እስከ አሥራ ሰባት ያሉትን በአንዱ ወገን፣ከአሥራ ስምንት እስከ ሃያ ያሉትን ደግሞ በሌላ ወገን። በዚህ መሠረት ከአሥራ አምስት እስከ አሥራ ሰባት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙት ሁለት መቶ ሰባ አንድ /64.5%/ ሲሆን ከአሥራ ስምንት እስከ ሃያ ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙት አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ /35.5%/ ናቸው። የዚህም ዝርዝር ሁኔታ በሠንጠረዥ አራት ላይ ይገኛል።

## 4.1.3 ብሔረሰብና የአፍ መፍቻ ቋንቋ

ከጠቀሰሰጡ የጥናቱ ናሙናዎች ሁለት መቶ ሃምሣ /59.5%/ የአማራ ብሔረሰብ ተወላጆች ሲሆኑ ስልሣ /14.3%/ የኦሮሞ ብሔረሰብ ተወላጆች፣ አርባ አምስት /10.7%/ የትግሬ ብሔረሰብ ተወላጆች፣ ቀሪዎቹ ሃያ ሁለት /5.2%/ ሌሎች ብሔረሰቦች ናቸው::

የአፍ መፍቻ ቋንቋን በተመለከተ ሶስት መቶ ሰማኒያ ሁለት /91%/ በአማርኛ አፋቸውን የፈቱ ሲሆኑ አሥራ ሰባት /4%/ በኦሮምኛ፣ አሥራ አምስት /3.6%/ በትግርኛ፣ ስድስት /1.4%/ በጉራጌኛ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ናቸው::

በመረጃዎቹ መሠረት አንድ መቶ ሰባ /40.5%/ ተማሪዎች አማራ ያልሆኑ ብሔረሰቦች ቢሆኑም ከነሱ ሠላሳ ስምንት /9%/ በስተቀር ሌሎቹ ሁሉ በአማርኛ አፋቸውን የፈቱ ናቸው:: ከጥናቱ ዓላማ አኳያ ብሔረሰቦችን "አማራ" እና "ሌሎች"፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋንም "አማርኛ" እና "ሌሎች" በማለት እያንዳንዳቸውን በሁለት ከፍለን ከትምህርት ቤቶች አኳያ ለመለየት ሞክረናል:: ሁኔታውን ከሠንጠረዥ አራት ይመልከቱ::

ሠንጠረዥ አራት

የተማሪዎች ጾታ፣ ዕድሜ፣ ብሔረሰብና የአፍ መፍቻ ቋንቋ

| ትምህርት ቤት | ጾታ | | ዕድሜ | | ብሔረሰብ | | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ከ15-17 | ከ18-20 | አማራ | ሌላ | አማርኛ | ሌላ |
| ከፍተኛ 4 | 35 | 35 | 46 | 24 | 29 | 41 | 58 | 12 |
| ሥ.ላ.ሥ | 44 | 26 | 49 | 21 | 39 | 31 | 64 | 6 |
| ወንድይራድ | 37 | 33 | 42 | 28 | 49 | 21 | 63 | 7 |
| ኪ/ተ ተቀዳሚ | 42 | 28 | 41 | 29 | 54 | 16 | 67 | 3 |
| ተፈር አንበሳ | 44 | 26 | 57 | 13 | 35 | 35 | 66 | 4 |
| አያቴ | 50 | 20 | 36 | 34 | 44 | 26 | 64 | 6 |
| ድምር | 252 | 168 | 271 | 149 | 250 | 170 | 382 | 38 |

## 4.1.4 የቤተሰብ የገቢ ሁኔታ

በጥቅሉ ከታየ፣ አብዛኛዎቹ ቤተሰቦች ወርሃዊ ገቢያቸው ከአምስት መቶ ብር በታች ነው:: በተለይ የአያቴ ትምህርት ቤት ወላጆች ገቢያ ቸው በጣም ዝቅተኛ ሲሆን የከፍተኛ 4 ትምህርት ቤት ወላጆችም ከአያቴ

በዚም አይበልጡም። ከአምስት መቶ ብር በታች ገቢ ያላቸው የአቃቂ ት/ቤት ወላጆች ትምህርት ቤት ወላጆች ሃምሳ ስምንት /82%/ ሲሆኑ የከፍተኛ አራት ት/ቤት ወላጆች አርባ ሦስት /61.4%/ ናቸው። በሌላ በኩል ከሁለት ሺህ ብር በላይ ገቢ ያለው አንድም ወላጅ በከፍተኛ አራት ትምህርት ቤት የማይገኝ ሲሆን በአቃቂ ግን ስድስት አሉ። ስለዚህ የሁለቱ ትምህርት ቤት ወላጆች ገቢ ያቸው በጣም ዝቅ ያለ ነው። ከሁለቱ ቀጥሎ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ወላጆች የታዩት በኢትዮጵያ ትቅደም ትምህርት ቤት ሲሆን የወንድራድና የኢስ.ኦ.ኢስ. ትምህርት ቤት ወላጆችም ትንሽ ሻል ያሉ እንጂ ከዝቅተኛ የገቢ ደረጃ የሚወጡ አይደሉም።

የጥቁር አንበሳ ትምህርት ቤት ወላጆች ግን አብዛኞቻቸው ከፍተኛ ገቢ ያላቸውና በተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው። ለዝርዝሩ ሠንጠረዥ አምስትን እንመልከት፡—

ሠንጠረዥ አምስት

የቤተሰብ ወርሃዊ ገቢ

| የገቢ መጠን | ትምህርት ቤቶች | | | | | | ድምር | መቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከፍተኛ 4 | ኢስ ኦ.ኢስ | ወንድራድ | ኢትዮጵያ ትቅደም | ጥቁር አንበሳ | አቃቂ | | |
| 200 እና በታች | 23 | 8 | 10 | 14 | 3 | 36 | 94 | 22.4% |
| ከ201— 500 | 20 | 21 | 25 | 25 | 5 | 22 | 118 | 28.1% |
| ከ501 — 800 | 14 | 22 | 18 | 15 | 6 | 4 | 79 | 18.8% |
| ከ801 — 1200 | 6 | 8 | 9 | 6 | 17 | 2 | 48 | 11.4% |
| ከ1201—1600 | 5 | 2 | 4 | 1 | 4 | — | 16 | 3.8% |
| ከ1601—2000 | 2 | 1 | — | 2 | 4 | — | 9 | 2.1% |
| ከ2001—2500 | — | 2 | — | 4 | 10 | 1 | 17 | 4.0% |
| ከ2500 በላይ | — | 6 | 4 | 3 | 21 | 5 | 39 | 9.3% |
| ድምር፡— | 70 | 70 | 70 | 70 | 70 | 70 | 420 | 100% |

ከኢስ.ኦ.ኢስና ከጥቁር አንበሳ ት/ቤት ወላጆች በስተቀር የቀሪዎቹ ትምህርት ወላጆች ከግማሽ በላይ ወርሃዊ ገቢያቸው ከአምስት መቶ ብር በታች ነው።

## 4.1.5 የአባቶችና የእናቶች የትምህርት ደረጃና የሥራ ሁኔታ

አብዛኛዎቹ የተማሪ ወላጆች የትምህርት ደረጃቸው ከአሥራ ሁለተኛ ክፍል በታች ነው:: ከላይ ስለቤተሰብ የገቢ መጠን መግለጫ ላይ አቃቂ ከሁሉም ዝቅተኛ መሆኑንና ጥቁር አንበሣ ከፍ ያለ መሆኑ ተገልጾ ነበር:: ይህ ሁኔታ በትምህርት ደረጃም እንዳለ ተንፀባርቋል:: የአቃቂ ት/ቤት ወላጆች 41% ያልተማሩና በመሠረተ ትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆን በዲግሪና በዲፕሎማ ደረጃ ላይ ያሉት 11.4% ብቻ ናቸው:: በአንፃሩ የጥቁር አንበሣ ት/ቤት ወላጆች 66.4% በዲግሪና በዲፕሎም ደረጃ ያሉ ሲሆኑ ፣ ያልተማሩና መሠረተ ትምህርት ደረጃ ላይ ያሉት 2.9% ብቻ ናቸው:: ከአቃቂ ቀጥሎ በዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኙት ወላጆች የኢትዮጵያ ትቀደም ትምህርት ቤት ወላጆች ናቸው:: በቀሪዎቹ ሦስት ትምህርት ቤቶች የሚገኙት ወላጆችም ከላይ እንደተጠቀሰው በአብዛኛው ከአሥራ ሁለተኛ ክፍል በታች ደረጃ ያሉ ናቸው:: ይበልጥ ግልፅ እንዲሆን ሠንጠረዥ ስድስት " ሀ " ን ይመልከቱ::

የሥራ ሁኔታን በተመለከተ 35% ወላጆች የመንግሥትና የሌሎች ድርጅቶች ተቀጣሪ ሲሆኑ 20.5% ወላጆች ደግሞ በንግድና በግል ሥራ የሚተዳደሩ ናቸው:: ከእናቶች ደግሞ 17.6% ሥራ የሌላቸውና የቤት እመቤቶች ናቸው:: ቀሪዎቹ 26.9% ደግሞ ጡረተኞች ፣ ሥራ አጥና ሥራቸው ያልተገለፀ ናቸው:: በከፍተኛ 4 ትምህርት ቤት ካሉት ወላጆች እናቶች 54.3% የቤት እመቤቶች ሲሆኑ በታቃራኒው በጥቁር አንበሣ ትምህርት ቤት ካሉት ወላጆች እናቶች 8.9% ብቻ የቤት እመቤት ናቸው:: ለዝርዝሩ ሠንጠረዥ ስድስት " ለ " ን ይመልከቱ::

<u>ሠንጠረዥ ስድስት</u>

የአባቶችና የእናቶች የትምህርት ደረጃና የሥራ ሁኔታ

| " ሀ " | ከፍተኛ 4 | | አስጎአስ | | ወንደራዴ | | ኢትዮጵያ ተቀደም | | ጥቁር አንበሳ | | አቃቂ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የትምህርት ደረጃ | አ | አ | አ | አ | አ | አ | አ | አ | አ | አ | አ | አ | ድምር | መቶኛ |
| ያልተማረና መሠረተ ትምህርት | 8 | 23 | = | 18 | 9 | 19 | 18 | 30 | 2 | 2 | 22 | 36 | 137 | 22.3% |
| ከ1 – 12 | 43 | 40 | 40 | 36 | 36 | 36 | 30 | 22 | 17 | 26 | 36 | 30 | 392 | 46.7% |
| ዲፕሎማ | 12 | 6 | 14 | 12 | 16 | 12 | 11 | 18 | 15 | 33 | 4 | 2 | 155 | 18.5% |
| ዲግሪ | 7 | 1 | 16 | 4 | 9 | 3 | 11 | – | 36 | 9 | 8 | 2 | 106 | 12.6% |
| " ለ " የሥራ ሁኔታ | | | | | | | | | | | | | | |
| በንግድና በሌላ የግል ሥራ | 24 | 6 | 12 | 6 | 25 | 4 | 30 | 7 | 22 | 22 | 8 | 6 | 172 | 20.5% |
| በመንግሥትና በሌሎች ድርጅቶች | 20 | 12 | 35 | 16 | 28 | 19 | 25 | 19 | 40 | 32 | 30 | 18 | 294 | 35% |
| ሥራ አጥና ጡረተኛ | 12 | – | 4 | – | 9 | – | 4 | – | – | – | 22 | 6 | 57 | 6.8% |
| ሥራቸው ያልተገለፀ | 14 | 14 | 19 | 26 | 8 | 12 | 11 | 21 | 8 | 10 | 10 | 16 | 169 | 20.1% |
| የቤት እመቤት | – | 38 | – | 22 | – | 35 | – | 23 | – | 6 | – | 24 | 148 | 17.6% |

4.2 <u>የመረጃዎች ስሌታዊ አሠራር</u>

መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ አወንታዊና አሉታዊ ዐረፍተ ነገሮች ከያዙት ነጥቦች አኳያ አያንዳንዱ መላሽ ያገኘው ነጥብ ተለይቶ ተመዝግቧል። በያንዳንዱ ጥያቄ ላይ የተገኙት ነጥቦች ተደምረው ከአምስት የተገኘው አማካይ ነጥብ ተሰልቷል:: ስለ አማካይ ነጥብ አሠራር እንደምሣሌ እንመልከት:_

" አማርኛን መማር እወዳለሁ " ለዚህ ዐረፍተ ነገር የሚከተለው ምላሽ ተሰጠ እንበል::

በጣም እስማማለሁ = 25 መላሾች      አለስማማም = 6 መላሾች

እስማማለሁ ....= 7 "      ፍጹም አለስማማም = 2 "

መወሰን ያስቸገረኛል=10 "

በምዕራፍ ሦስት እንደተገለፀው ይህ ዐረፍተ ነገር አዎንታዊ በመሆኑ "በጣም እስማማለሁ" / 5 /፣ እስማማለሁ / 4/፣ መወሰን ያስቸግረኛል /3/፣ አልስማማም /2/፣ ፍጹም አልስማማም/1/ ነጥብ ይዘዋል። ስለዚህ የስሌቱ አካሄድ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

አማካይ ለማግኘት የስምምነቱን ነጥብ በድግግሙ ብዛት ማባዛትና መደመር ከዚያ ለመላሾች ቁጥር ማካፈል። / በዚህ ምሳሌ የመላሾች ቁጥር ሃምሳ ነው/ ስለዚህ:_

$$\text{አማካይ} = \frac{(5\times25) + (4\times7) + (3\times10) + (2\times6) + (1\times2)}{50}$$

$$= \frac{125 + 28 + 20 + 12 + 2}{50}$$

$$= \frac{197}{50} = 3.94$$

በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ ከአማካይ ነጥቡ ጎን የመላሾች ብዛት በመቶኛ ተሰልቶ ቀርቧል። ከላይ የወሰድነውን ምሳሌ በመቶኛ ስሌት እንደሚከተለው መሥራት ይቻላል። የመቶኛ ስሌት የመላሽ ብዛት ሲካፈል ለጠቅላላ የመላሽ ቁጥር ሲባዛ በመቶ ይሆናል። ስለዚህ "በጣም እስማማለሁ" ያሉት ሃያ አምስት መላሾች በመቶኛ ሲሰላ $\frac{25}{50} \times 100 = 50\%$ ። በዚህ ቀመር መሠረት ስንሠራ "እስማማለሁ" የሚለው 7/14%/፣ መወሰን ያስቸግረኛል" የሚለው 10/20% /፣ "አልስማማም" የሚለው 6/12%./፣ "ፍጹም አልስማማም" የሚለው 2/4%/ ይሆናል ማለት ነው፡፡

አማካይ ነጥብና የመቶኛ ስሌት በሚሠራበት ጊዜ ወደ አሥረኛ ቀርበት ተጠግቷል።

4.3. <u>ከእያንዳንዱ ጥያቄ የተገኘ ምላሽ</u>

4.3.1 <u>የተማሪዎች</u> ገላጭ <u>አመለካከት</u>

ይህ የመጀመሪያና ዋነኛ ተለውጠ ሲሆን ስድስት አዎንታዊና ስድስት አሉታዊ ሐሳቦችን በድምሩ አሥራ ሁለት ዝግ ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ ይህ ክፍል እያንዳንዱ መላሽ ለ "1.11" እና ለ "1.12" ለሰጠው መልስ ምክንያት እንዲሰጥ ይጠይቃል። በዚህ ክፍል ውስጥ የታቀፈ ሌላው ዋነኛ ጥያቄ በቀጥ

ትምህርት ክፍል ሊቀርቡ የሚችሉትን ዐቢይ ትምህርቶችን ይዘረዝርና ተማሪዎች በፍላጎታቸው መሠረት በቅደም ተከተል እንዲመረጡ ይጋብዛል። ሌላው በዚህ ክፍል የታቀፈው ጥያቄ በቁጥር "14" ላይ የተቀመጠ ሲሆን ከሌሎች የትምህርት ዘርፎች ጋር ሲነፃፀር ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጡትን ቦታ ለማወቅ የታሰበ ነው።

ከዚህ ቀጥለን በዚህ ተሳወጠ ሥር ለቀረቡት አሥራ አራት ጥያቄዎች ለያንዳንዳቸው የተሰጠውን መልስ በዝርዝር እንመለከታለን።

1.1. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ገፍቼ ጋዜጠኛና ደራሲ መሆን እፈልጋለሁ።

| አማራጭ መልሶች | የመላሽ ብዛት | የተገኘ ነጥብ | መቶኛ |
|---|---|---|---|
| ሀ. በጣም እስማማለሁ | 133 | 665 | 31.7% |
| ለ. እስማማለሁ | 69 | 276 | 16.4% |
| ሐ. መወሰን ያስቸግረኛል | 106 | 318 | 25.2% |
| መ. አልስማማም | 63 | 126 | 15.0% |
| ሠ. ፍጹም አልስማማም | 49 | 49 | 11.7% |
| ድምር፡– | 420 | 1434 | 100% |

አማካይ = 3.41

1.2. ግዴ ሆኖብኝ እንኳ አማርኛን መማር አልፈልግም።

| አማራጭ መልሶች | የመላሽ ብዛት | የተገኘ ነጥብ | መቶኛ |
|---|---|---|---|
| ሀ. በጣም እስማማለሁ | 32 | 32 | 7.6% |
| ለ. እስማማለሁ | 22 | 44 | 5.2% |
| ሐ. መወሰን ያስቸግረኛል | 20 | 0 | 4.8% |
| መ. አልስማማም | 122 | 488 | 29.0% |
| ሠ. ፍጹም አልስማማም | 224 | 1120 | 53.3% |
| ድምር፡– | 420 | 1744 | 100% |

አማካይ ነጥብ 4.15

1.1 ለአፃንታዊ ጠሣቦች ሁሉ የስሌት አሠራር ምሣሌ እንዲሆንና

1.2 ደግሞ ለአሉታዊ ጠሣቦች ሁሉ የስሌት አሠራር ምሣሌ እንዲሆን በዝርዝር ያስቀመጥን ስለሆነ ሌሎቹን ባጭሩ በመቶኛና በአማካይ ነጥብ እየገለጽን እናልፋለን። ደግሞም በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ አጠቃላይ ሁኔታውን የሚያቀርብ ኮገሪ ስላለ በያንዳንዱ ጥያቄ ላይ ስለአሠራር ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ መግባት አያስፈልገም።

1.3 " አብዛኞቹ የምማራቸው የአማርኛ ትምህርት ዘርፎች ከፍላጎቴ ጋር ይጣጣማሉ።

በዚህ ጠሣብ ላይ 31.4% በጣም እስማማለሁ " ፤ 33.3% " እስማማለሁ " ፤ 12.1% መጠነኛ ያስቸግረኛል " ፤ 13.8% " አልስማማም " ፤ 9.3% ደግሞ " ፍጹም አልስማማም " በማለት መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡም 3.64 ነው።

1.4 የአማርኛ ትምህርት ስለሚቀለኝ እንቀዋለሁ።

በዚህ ዐረፍተ ነገር ላይ 5.2% በጣም እስማማለሁ " ፤ 6.2% " እስማማለሁ " ፤ 8.1% መጠነኛ ያስቸግረኛል " 32.6% " አለስማማም " ፤ 47.9% " ፍጹም አለስማማም " የሚል መልስ ሰጥተዋል። አማካይ ነጥቡም 4.12 ነው።

1.5 የአማርኛን ባህል ወግና ሥርዓት እወዳለሁ።

ለዚህ ጠሣብ " በጣም እስማማለሁ " ያሉት 55.7% ፤ " እስማማለሁ " ያሉት 18.1% ፤ " መጠነኛ ያስቸግረኛል " ያሉት 11.4% ፤ " አለስማማም " ያሉት 7.4% ፤ " ፍፁም አለስማማም " ያሉትም 7.4 ናቸው። አማካይ ነጥቡ ደግሞ 4.07 ነው።

1.6 አማርኛ ቋንቋ ያስጠላኛል።

በዚህ ላይ 4.3% " በጣም እስማማለሁ " ፤ 1.2% " እስማማለሁ " ፤ 3.6% " መጠነኛ ያስቸግረኛል " 22.4% " አለስማማም " ፤ 68.6% " ፍጹም አለስማማም " በማለት መልስ ዋለ።

አማካይ ነጥቡ 4.50 ነው።

1.7 የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ብሔረሰቦችን አከብራለሁ።

ለዚህ ጠሣብ 43.3% " በጣም እስማማለሁ " 22.6% " እስማማለሁ " ፤ 16.7% " መጠነኛ ያስቸግረኛል " ፤ 7.9% " አልስ

ማማም " ፣ 9.5% " ፍጹም አለስማማም " የሚል መልስ ተሰጥቷል።

አማካይ ነጥብ 3.82 ነው።

1. 8 ብዙ ጊዜ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤቱ ዝቅተኛ ነው።

በዚህ ጠሣብ ላይ " በጣም እስማማለሁ " ያሉት 12.1%፣ " እስማማለሁ " ያሉት 14% ፣ " መወሰን ያስቸግረኛል " ያሉት 14.3% ፣ " አለስማማም " ያሉት 27.1% ፣ " ፍጹም አለስማማም " ያሉት 32.4% ናቸው። አማካይ ነጥቡ 3.54 ነው።

1. 9 ሲነበና ሲጻፍ ከሌሎች ቋንቋዎች ይልቅ በደንብ የሚገባኝ በአማርኛ ቋንቋ ሲሆን ነው።

ለዚህ ጠሣብ 65.2% " በጣም እስማማለሁ " ፣ 15.2% " እስማማለሁ " 7.1% " መወሰን ያስቸግረኛል " ፣ 8.1% " አልስማማም " ፣ 4.3% . ፍጹም አለስማማም " ብለ ዋል። አማካይ ነጥቡ 4.29 ነው።

1.10 ከአማርኛ ይበለጥ የምወደው ቋንቋ አለኝ።

በዚህ ጠሣብ ላይ 27.9% " በጣም እስማማለሳሁ " 17.6% " እስማማለሁ " ፣ 14% " መወሰን ያስቸግረኛል " 12.6% " አለስማማም " ፣ 27.9% . " ፍጹም አለስማማም " ብለ ዋል። አማካይ ነጥቡ 2.95 ነው።

1.11 አማርኛ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ ቢሆን ደስ ይለኛል።

ለዚህ ጠሣብ የተሰጠው ምላሽ 23.8 " በጣም እስማማለሁ " ፣ 8.3% " እስማማለሁ " ፣ 14.5% " መወሰን ያስቸግረኛል " ፣ 20% " አለስማማም " ፣ 33.3% ፍጹም አለስማማም " የሚል ነው።

አማካይ ነጥቡ 2.69 ነው።

1.12 አማርኛ የኢትዮጵያ አፊሴላዊ ቋንቋ መሆን የለበትም።

በዚህ ዐረፍተ ነገር ላይ 13.1% . " በጣም እስማማለሁ " 3.3% " እስማማለሁ " ፣ 9.8% ፣ መወሰን ያስቸግረኛል፣ 12.6% አለስማማም " ፣ 61.2% " ፍጹም አለስማማም " በማለት መልስ ዋል።

በዚህ ተሳትሞ ሳይ ከፍተኛ አዎንታዊ ነጥብ የተመዘገበው " አማርኛ ቋንቋ ያስጠላኛል " በሚለው አሉታዊ ዐረፍተ ነገር ላይ ሲሆን 91%. ተማሪ-ዎች ሐሣቡን ተቃውመውታል። አማካይ ነጥቡም 4.50 ነው።

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ የነበረው መድሐኔ ሀብተጊዮርጊስ /1986:22/ የአዲስ አበባ ተማሪዎች አማርኛን እንደሚጠሉ አድርጉ ያቀረበውና በተወሰኑ ሰዎችም እየተደገፈ የሚነገረው ሐሣብ ፍጹም ውሸት ነው። ማንም ሰው ቋንቋውን አይጠላም። ጊዋራ / 1983 / የአንድ አካባቢ ቋንቋ ከተናጋሪዎቹ ሕሊውና ጋር የተያያዘ ዋነኛ ጉዳይ መሆኑን ይጠቅሳል። እንደ ጊዋራ አባባል የራሱን ቋንቋ የሚጠላ ሕሊውናውን የሚጠላ ማለት ነው። ስለዚህ የአዲስ አበባ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋቸው እስከሆነ ድረስ / ከጥቂቶች በስተቀር / ሊጠሉት አይችሉም። ከጥናቱ የተገኘው መረጃም ይህንኑ ያረጋግጣል።

ሌላው ከፍተኛ ነጥብ የተመዘገበው " ሲነበና ሲዳምጥ ከሌሎች ቋንቋዎች ይልቅ በደንብ የሚገባኝ በአማርኛ ቋንቋ ሲሆን ነው " በሚለው ሐሣብ ላይ ሲሆን 80.4% መላሾች ተቀብለውታል። አማካይ ነጥቡም 4.29 ነው። ከዚህ ሐሣብ ጋር ተጣምሮ ሊታይ የሚችለው ወደ አሉታዊነት ያዘነበለ ምላሽ የተገኘበት " አማርኛ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቋንቋ ቢሆን ደስ ይለኛል " የሚለው ሐሣብ ነው። በመሠረቱ አንድ ሰው ለመማር የቋንቋ ምርጫ ቢሰጠው መምረጥ ያለበት ለማንበብም ሆነ ለማዳመጥ ይበልጥ የሚቀለውንና የሚገባውን መሆን አለበት ነገር ግን በዚህ ጥናት ከተማሪዎቹ የተገኘው ምላሽ በተቃራኒው ነው። አብዛኛዎቹ ተማሪዎች " ይበልጥ የሚገባን አማርኛ ነው " እያሉ አማርኛ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን አልደገፉም። አማርኛ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን አለመደገፉ በዚህ ጥናት ብቻ የታየ ሳይሆን ቀደም ብለው በተደረጉት በአንደርሰን አንደርሰ ጥናት / 1967/ ፣ በፀጠየ ተፈራ ጥናት / 1977/ ፣ በብርሃኑ ገብረማርያም ጥናት / 1976 ዓ.ም. / ፣ በወርቁ በሺዳ ጥናት / 1982 ዓ.ም./ ሁሉ ላይ ነው። ተማሪዎቹ በዚህ ጥናት ላይ አማርኛ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን ሳለመደገፋቸው የሰጡትን ምክንያቶች ወረድ ብለን እናገኛለን።

ሁለት ከፍተኛ የተቃውሞ መልስ የተሰጣቸው አሉታዊ ሐሣቦች " ገዱ ሆኖ ብቻ እንጂ አማርኛን መማር አያስፈልግም " የሚለውና " የአማርኛ ትምህርት ስለ ... ሐሣብ የተቃወሙት 82.3%

ሲሆኑ ሁለተኛውን ሐሣብ የተቃወሙት 80.5% ናቸው። አማካይ ነጥባቸውም እንደቀደም ተከተላቸው 4.15 እና 4.12 ናቸው። እነዚህ መረጃዎች ተማሪዎች አማርኛን እንደሚንቁና መማር እንደማይፈልጉ በብርሃኑ ገብረማርያም ጥናት / 1976 ዓ.ም. / የቀረበውንና በአንዳንድ ሰዎችም የሚነገረውን ሐሣብ ውድቅ ያደርጉታል።

በሥነ–ጽሑፍ ክለሳ ክፍል እንደተመለከትነው የአንድን ማኅበረሰብ ባህል፣ ወግና ሥርዓት የሚወድ ሰው ቋንቋቸውንም ይወዳል። በዚህ መሠረት " የአማርኛን ባህል፣ ወግና ሥርዓት እወዳለሁ " የሚለው ሐሣብ 73.8% ስለተደገፈና አማካይ ነጥቡም 4.07 ስለሆነ አማርኛ ቋንቋ በተማሪዎች ዘንድ የሚወደድ እንጂ የሚጠላ እንዳልሆነ " 1.6 " ላይ የቀረበውን መረጃ በተዘዋዋሪ መንገድ አረጋገጠታል።

ሌላው 73.8% ተቃውሞ የተሰነዘረበት አሉታዊ ሐሣብ " አማርኛ የኢትዮጵያ ኦፊሴላዊ ቋንቋ መሆን የለበትም " የሚለው ነው። የተገኘው አማካይ ነጥብ 4.05 ሲሆን በርካታዎቹ መላሾች አማርኛ የኢትዮጵያ ኦፊሴላዊ ቋንቋ እንዲሆን ደገፈዋል። ፀሐየ ተፈራ / 1977 / ባደረገውም ጥናት አማርኛ የኢትዮጵያ ኦፊሴላዊ ቋንቋ እንዲሆን ተደግፏል።

በ " 1.11 " ላይ እንደቀረበው፣ በአማርኛ ትምህርት ገፍተው ጋዜጠኛና ደራሲ መሆን የሚፈልጉት ተማሪዎች 48%. ሲሆኑ የማይፈልጉት 26.7% ናቸው። " ጋዜጠኛና ደራሲ መሆን እንፈልጋለን " ያሉት ተማሪዎች አማርኛንና የአማርኛን ትምህርት እንደማይጠሉ እንገምታለን። በሌላ በኩል " ጋዜጠኛና ደራሲ መሆን አንፈልግም " ያሉት ተማሪዎች ሁሉ አማርኛንና ትምህርቱን ይጠላሉ ማለት አይደለም። ነገር ግን ከቋንቋው ትምህርት ጋር የተያያዘውን ሙያ ምን ያህሉ ተማሪዎች እንደሚያስቡትና ከዓላማቸው አኳያ ለትምህርቱ ሊሰጡ የሚችሉትን ትኩረት ለመገመት ይረዳል።

በ " 1.3 " ላይ እንደተገለፀው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች /64.7%/ የሚማሯቸው የአማርኛ ትምህርት ዘርፎች ከፍላጎታቸው ጋር ይጣጣማሉ። ፍላጎትን የጠበቀ ትምህርት ይወደዳል። ስለዚህ የአማርኛ ትምህርት የብዙዎቹን ፍላጎት ከጠበቀ በብዙዎቹ ተማሪዎች ይወደዳል ማለት ነው። በርግጥ 22.5% ተማሪዎች ከፍላጎታቸው ጋር እንደማይጣጣም ገልፀዋል። ቀሪዎቹ መወሰን አልቻሉም።

በ " 1.7 " ላይ እንደቀረበው 65.9% ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ እንደ ተናጋሪ ብሔረሰቦችን ያከብራሉ። ብሔረሰቡን ያከበረ የብሔረሰቡን ቋንቋ እንደ

ሚያከብር በዝግጁ ጽሑፍ ከለሳ ክፍል አይተናል:: ስለዚህ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ያከብራሉ ማለት ነው:: ጥቂት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ብሔረሰቦችንና አማረኛ ቋንቋን አያከብሩም /17.4 %/፣ ቀሪዎቹ ደግሞ አቋም ያልወሰዱ ናቸው::

በ " 1.8 " መረጃ መሠረት ብዙ ጊዜ የአማርኛ ትምህርት ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆነው 26.1 % ሲሆኑ 59.5 % ውጤታቸው ጥሩ ነው:: በዝግጁ ጽሑፍ ከለሳ ክፍል እንደተገለፀው በአንዱ ቋንቋ ጥሩ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት ጥሩ አመለካከት ይኖራቸዋል:: በዚህ መሠረት በርካታዎቹ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ጥሩ አመለካከት አላቸው ማለት ነው::

በ " 1.10 " ላይ 45.5 % ተማሪዎች ከአማርኛ ይበልጥ የሚወዱት ቋንቋ እንዳላቸው ገልፀዋል:: " ከአማርኛ ይበልጥ የምንወደው ቋንቋ የለም" ያሉት 40.5 % ናቸው:: አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አማርኛ የአፍ መፍቻቸው ስለሆነና ስለሚያውቁት የማያውቁትን እንግሊዝኛ ለማወቅ የበለጠ ፍላጎት አላቸው:: ይህን የበለጠ ፍላጎት ይዘው ነው " ከአማርኛ ይበልጥ የምንወደው ቋንቋ አለን" ያሉት:: በመሠረቱ ማንም ሰው ከአፍ መፍቻው ቋንቋው በላይ የሚወደው ቋንቋ እንደሌለ በዝግጁ ጽሑፍ ከለሳ ክፍል አይተናል::

መላሾቹ ለ" 1.11" እና ለ " 1.12" መልሶቻቸው የሰጡት ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል::

ሀ. 1.11 " አማርኛ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ ቢሆን ደስ ይለኛል" የሚለውን ሐሳብ የደገፉት መላሾች ያቀረቧቸው ምክንያቶች በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርበዋል::

ሠንጠረዥ ሰባት

የድጋፍ ምክንያቶች

| ተ.ቁ | ምክንያቶች | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|---|
| 1 | በአማርኛ ቋንቋ ብንማር ትምህርት በቀላሉ ሊገባን ስለሚችል | 56 | 13.3 |
| 2 | እንግሊዝኛ ቋንቋ በጣም ስለሚከብደንና ገለጻው ስለማይገባን | 15 | 3.6 |
| 3 | በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንደለቢችን ጠይቀን መረዳት ስለማንችል | 10 | 2.4 |
| 4 | ያደጉ አገሮች ሁሉ በራሲቸው ቋንቋ ስለሚማሩ | 8 | 1.9 |
| 5 | ለአማርኛ ቋንቋ እድገት ጠቃሚ ስለሚሆን | 6 | 1.4 |
| 6 | የአገራችን ብሔራዊ ቋንቋ ሆኖ በማገልገል ላይ በመሆኑ | 5 | 1.2 |
| 7 | በብዙ የክልል ከተሞች ሁሉ የመገባቢያ ቋንቋ በመሆኑ | 5 | 1.2 |
| 8 | ለጥናት ስለማያስቸግር | 3 | 0.7 |
| 9 | ከአማርኛ ውጭ ሌሎች ቋንቋዎችን ስለማንችል | 3 | 0.7 |
| 10 | የአማርኛ ቋንቋ ዕውቀታችን ስለሚሰፋ | 3 | 0.7 |
| 11 | በብዙ ሰዎች የሚነገርና ያደገ ቋንቋ በመሆኑ | 2 | 0.5 |
| 12 | እንደልብ መጠየቅና መመለስ ስለምንችል | 1 | 0.2 |

በሠንጠረዡ ላይ በርካታ ምክንያቶች የተዘረዘሩ ቢሆንም ከምክንያት አቀራቢ ዎች በብዙ ሰዎች የቀረቡትና አሳማኝ የሚመስሉት ከተራ ቁጥር 1 - 3 የተጠቀሱት ና ቸው::

አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚገለጽ ጠሣብ በደንብ እንደማ ይገባቸውና የተማሪዎቹ የእንግሊዝኛ ችሎታ ትምህርት ሊቀስመበት የማያስችላቸው መሆኑን ወርቁ በቧኣ /1982 ዓ.ም./ ገልጿል:: ስለዚህ ዛሬም ቢሆን ፡፡ የ ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ እንግሊዝኛ ነው። ይባል እንጂ ከተማሪዎቹ አለ መረዳትና ከአንዳንዱ መምህራንም ቋንቋውን በደንብ አለመቻል የተነሳ ገለጻው ግማሽ በግማሽ በአማርኛ ቋንቋ እየተካሄደ ነው /ወርቁ በቧኣ 1982 ዓ.ም/ ::

ለ. 1.11 ። አማርኛ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ ቢሆን ደስ ይለናል

የቀረቡቸው ምክንያቶች

## ሠንጠረዥ ስምንት

የተጠቀሱ ምክንያቶች

| ተ.ቁ | ምክንያቶች | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|---|
| 1 | አማርኛ ዓለም አቀፋዊ ቋንቋ ስላልሆነ | 50 | 11.9 |
| 2 | አማርኛን ስለምንችል የማንችለውን እንግሊዝኛ ብናዳብር ይሻላል | 21 | 5 |
| 3 | እንግሊዝኛ ዓለም አቀፋዊ ቋንቋ ስለሆነ በሱ መማር አለብን | 15 | 3.6 |
| 4 | እንግሊዝኛን ማወቅ የበለጠ ስለሚጠቅም ትምህርት በእንግሊዝኛ መቀጠል አለበት | 13 | 3.1 |
| 5 | እንግሊዝኛን በሁለተኛ ደረጃ ተምረንበት ካላጎለበትን ዩንቨርስቲ ስንገባ እንቸገራለን | 8 | 1.9 |
| 6 | የሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝቶች በአማርኛ መጠሪያ - ቃላት ስለሌላቸው | 8 | 1.9 |
| 7 | አማርኛ በደንብ ስላልዳበረ እንግሊዝኛን ሊተካ አይችልም | 5 | 1.2 |
| 8 | የእንግሊዝኛ ችሎታችን ይመነምንና ጥራቱ ይወ ታል | 5 | 1.2 |
| 9 | መጻሕፍቱን ወደ አማርኛ ለመተርጎም ስለሚያስቸግር | 4 | 1 |
| 10 | እንግሊዝኛን በሁለተኛ ደረጃ ካልተማርንበት ውጭ ሀገር ብንሄድ ከሌሎች ጋር ለመግባባት አንችልም | 3 | 0.7 |
| 11 | በአማርኛ ቋንቋ መማር አይጥምም | 2 | 0.5 |
| 12 | የሒሳብና የሳይንስ ትምህርቶች በአማርኛ ሊቀርቡ ስለማይችሉ | 2 | 0.5 |

የትምህርት ዓላማ የማያውቁትን ማሳወቅ እስከሆነ ድረስ ማሳወቅ የሚቻለው ተማሪው በሚገባው ቋንቋ ሲነገረው ነው:: የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ረቂቅ /1985:61 ዓ.ም./ የትምህርት ቋንቋን በዕውቀት ማስተላለፊያና መቀበያ መሣሪያነቱ መምህሩና ተማሪው በማሰብ፣በማዳመጥ፣በመናገር፣በማንበብና በመጻፍ ሳይቸገሩ በሥርዓቱ ሊጠቀሙበት ይገባል ይላል:: ታዲያ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሳይቸገሩ የሚጠቀሙበትና በደንብ የሚገባ ... አማርኛ ስለመሆኑ ጥርጥር የለም::

ተማሪዎቹ ራሳቸው በ "1.9" ላይ በቀረበላቸው ጥያቄ መሠረት ሲያነቡና ሲያዳ ምጡ ከሌሎች ቋንቋዎች ይበልጥ በአማርኛ ሲሆን እንደሚገባቸው ተናግረዋል:: በ አንጻሩ በሠንጠረዥ ስምንት ላይ ከ1 - 5 ዋነኛ ሆነው የተጠቀሱትና አማርኛ የ ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ እንዳይሆን የቀረቡት ምክንያቶች እንደሚከተለው ሊብራሩ ይችላሉ::

- አንደኛው ምክንያት "አማርኛ አለም አቀፋዊ ቋንቋ ስላልሆነ" ይላሉ:: በመሆኑ "ዓለም አቀፋዊ የትምህርት ቋንቋ" ተብለው የተመደቡ ቋን ቋዎች አሉወይ? ዛሬ የበለፀጉ በርካታ አገሮች የየራሳቸውን ቋንቋ የትምህርት ቋንቋ አድርገው የሚጠቀሙበት ቋንቋቸው አለም አቀፋዊ ቋንቋ ስለሆነ ነው? የነዚህ ጥያቄዎች መልስ ግልጽ ስለሆነ አጥ ጌው ለመመለስ አይሞከርም ግን ፣ቢጥሬ የተጠቀሰው ምክንያት አሳማኝ አለመሆኑ መታወቅ ይኖርበታል::
- ሁለተኛው ምክንያት "አማርኛን ስለምንችል የማንችለውን እንግሊዝኛ ብናዳብር ይሻላል" ይላል:: ለመሆኑ በሁለተኛ ደረጃ የሚሰጡት ትምህርቶች ሁሉ አላማቸው የእንግሊዝኛን ችሎታ ለማዳበር ነው? ደግሞስ፣ የእንግሊዝኛ ችሎታን ለማዳበር ሲባል የሌሎች ትምህርቶች ሁሉ ዕውቀት ሳይገባን ይቅር? ይህም ምክንያት ሳይንሳዊነት እንደሌለው ልብ ልን ለው ይገባል::
- ሶስተኛው ምክንያት "እንግሊዝኛ ዓለምአቀፋዊ ቋንቋ ስለሆነ በሱ መማር አለብን" የሚል ሲሆን አራተኛና አምስተኛ ምክንያቶችም የ ተያያዙ ሆነው "እንግሊዝኛ ማወቅ ይጠቅማል፤ በሁለተኛ ደረጃ ውስጥ ሆነን ካላወቅን ዩኒቨርስቲ ስንገባ እንቸገራለን" የሚሉ ናቸው:: እንግሊዝኛ ቋንቋን ማወቅ ጠቃሚ መሆኑን ማንም አይክደም:: ነገር ግን "ዓለም አቀፋዊ ነውና የግድ የትምህርት ቋንቋ መሆን አለበት" የሚለው ሐሳብ አያሳምንም:: ከሩቅ የሚታለመው የዩኒቨርስቲ ትምህ ርትም ቢሆን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያልገባው ሰው መች እዚያ ይደርስና:: ስለዚህ አማርኛ የትምህርት ቋንቋ እንዳይሆን የቀረቡት ምክንያቶች ሁሉ ተቀባይነት የላቸውም::

ሐ. 1.12 " የአማርኛ የኢትዮጵያ ኦፊሴላዊ ቋንቋ መሆን የለበትም " የሚለውን ሐሳብ የተቃወሙት መላሾች ያቀረቧቸው ምክንያቶች በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርበዋል::

ሠንጠረዥ ዘጠኝ

የተቃውሞ ምክንያቶች

| ተ.ቁ | ምክንያቶች | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|---|
| 1 | አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚግባባበት ቋንቋ በመሆኑ | 130 | 31 |
| 2 | አማርኛ ከጥንት ጀምሮ የተለመደ ማዕከላዊ ቋንቋ በመሆኑ | 30 | 7.1 |
| 3 | አማርኛ በርካታ ተናጋሪዎች ስላሉበት | 15 | 3.6 |
| 4 | አማርኛ ለሁሉም ገለጽና ቀላል ቋንቋ በመሆኑ | 10 | 2.4 |
| 5 | በርካታ ብሔር ብሔረሰቦች አማርኛን መናገር ስለሚችሉ | 10 | 2.4 |
| 6 | አማርኛ ኦፊሴላዊ መሆን የሚችል ያደገ ቋንቋ በመሆኑ | 8 | 1.9 |
| 7 | ለበርካታ ሰዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ በመሆኑ | 7 | 1.7 |
| 8 | ከአማርኛ የተሻለ ሌላ ቋንቋ ስለሌለ | 4 | 1 |
| 9 | ሌላ ቋንቋ ለመምረጥ ጊዜ ስለሚፈጅ | 2 | 0.5 |

መ. 1.12 " አማርኛ የኢትዮጵያ ኦፊሴላዊ ቋንቋ መሆን የለበትም " የሚለውን ሐሳብ የደገፉ መላሾች ያቀረቧቸው ምክንያቶች በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርበዋል::

ሠንጠረዥ አሥር

የድጋፍ ምክንያቶች

| ተ.ቁ | ምክንያቶች | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|---|
| 1 | ሁሉም ብሔረሰቦች በራሳቸው ቋንቋ መጠቀም ስላለባቸው | 5 | 1.2 |
| 2 | አማርኛን የማይችሉ ሌሎች ብሔረሰቦች እንዳይጎዱ | 4 | 1 |
| 3 | ከአማርኛ የበለጠ ተናጋሪ ያለው ቋንቋ ስላለ | 3 | 0.7 |
| 4 | የአንድ ብሔረሰብ ቋንቋ ብቻ ማደግ ስለሌለበት | 2 | 0.5 |
| 5 | አማርኛን መናገር የማይችሉ ብዙ ሰዎች ስላሉ | 2 | 0.5 |
| 6 | አማርኛ ከሌሎች ቋንቋዎች የበለጠ ስላልሆነ | 1 | 0.2 |
| 7 | ካደጉ አገሮች ጋር ለመግባባት አማርኛ ስለማይጠቅም | 1 | 0.2 |

በሠንጠረዥ ዘጠኝና አሥር የቀረቡትን ምክንያቶች እንደሚከተለው ለማብራራት እንሞክራለን::

በሠንጠረዥ ዘጠኝ የተጠቀሱት ምክንያቶች የሚያመለክቱት ሐሳብ «አማርኛ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠቀምበትና ከጥንት ጀምሮ ኦፊሴላዊ ቋንቋ ሆኖ ሲያገለግል የቆየ፣ ከሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችም በርካታ ተናጋሪዎችን ያፈራ ነው:: ስለሆነም ከሱ የተሻለ ኦፊሴላዊ ሆኖ የሚያገለግል ቋንቋ የለም::» የሚል ነው። ቤንደር /1976/ እና ማክናብ /1989/ ይህንን ሐሳብ ይደግፋሉ::

በሠንጠረዥ አሥር ላይ አማርኛ ኦፊሴላዊ ቋንቋ እንዳይሆን የቀረቡት የመጀመሪያ ሁለቱ ምክንያቶች «ሁሉም ብሔረሰቦች በራሳቸው ቋንቋ መጠቀም ስላለባቸውና አማርኛን የማይችሉት ብሔረሰቦች እንዳይጎዱ» የሚሉ ናቸው:: እንደ እውነቱ ከሆነ እነዚህ ሐሳቦች ተቀባይነት የላቸውም:: ምክንያቱም ምንም ቢሆን የሁሉም ብሔረሰብ ቋንቋዎች የአገሪቱ ኦፊሴላዊ ቋንቋ መሆን አይችሉም:: የግድ አንዱ ወይም ጥቂቶች ብቻ መመረጣቸው አይቀርም:: ደግሞም የአንዱ ቋንቋ ኦፊሴላዊ ቋንቋ ሆኖ መመረጥ ሌሎች ብሔረሰቦች በራሳቸው ቋንቋ እንዳይጠቀሙ አያግድም:: በሌላም በኩል ቋንቋቸው ኦፊሴላዊ ሆኖ ያልተመረጠ ብሔረሰቦች የሚጎዱበት ነገር የለም:: ብሔረሰቦች ሁሉ በየክልላቸው የራሳቸውን ቋንቋ እንደልብ ይጠቀሙበታል:: ይልቅስ ለጋራ መግባቢያ ኦፊሴላዊ ሆኖ የተመረጠውን ቋንቋ ቢማሩትና ቢያውቁት ተጠቃሚ እንጂ አለተጉዱም::

ስለዚህ አማርኛ ኦፊሴላዊ ቋንቋ እንዳይሆን የቀረቡት ምክንያቶች አያሳምኑም የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ረቂቅ /1985:669.ም/ «አማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ብሔር ብሔረሰቦችን በጋራ ስለሚያገባብ ... ሃገራዊ ግንኙነት እንዲመረጥ አብቅቶታል» ይላል:: ስለዚህ በሠንጠረዥ ዘጠኝ ላይ የቀረቡት ምክንያቶች ይበልጥ አሳማኝ ናቸው::

ለ.ለ «1.11» እና ለ «1.12 ጥያቄዎች መልስ ያልሰጡት በርካታ ናቸው::
በዚህ መሠረት በ «1.11» ሐሳብ ላይ የስምምነት ምክንያት የሰጡት 27.8%. ሲሆኑ የተቃውሞ ምክንያት የሰጡት 32.5%. ናቸው:: ቀሪዎቹ 39.7%. ምክንያት አልሰጡም::

በ «1.12» ሐሳብ ላይም እንደዚሁ ለተቃውሟቸው ምክንያት የሰጡት 51.6%. ሲሆን ለድጋፋቸው ምክንያት የሰጡት 3.8%. ብቻ ናቸው:: ቀሪዎቹ 45.6%. ለመልሳቸው ምክንያት አልሰጡም::

በዚህ ተሳውጦ ላይ ከአሥራ ሁለቱ ዝግ ጥያቄዎች በተጨማሪ የተማሪዎችን
ፍላጎትና ምርጫ የሚዳስሱ ሁለት ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ጥያቄዎቹ መለሶቻቸው
የሚከተሉት ናቸው::

1.13 ቀጥሎ የተዘረዘረትን ዐበይ የአማርኛ ትምህርት ርዕሶች ደስ ብሏችሁ
ከምትማሯት ጀምራችሁ በፍላጎታችሁ ቀደም ተከተል መሠረት ከርዕሶቹ
ፊት ለፊት ባለው ሳጥን ውስጥ ቁጥር ስጡት

ተማሪዎቹ ለቀረቡላቸው አሥራ ሁለት ዐበይ የትምህርት ርዕሶች ምርጫቸውን
ቁጥር በመስጠት ካለመለከተ በኋላ እያንዳንዱ ርዕስ በምርጫ ያገኘውን ደረጃ ለማ
ወቀ ደሳለኝ ማሉ ቺካ /1995/ የተገለገለበትን፡ስልት፡ በመጠቀም በአንደኛ ደረጃ
ለተመረጠው አሥራ ሁለት ነጥብ፤በሁለተኛ ደረጃ ለተመረጠው አሥራ አንድ ነጥብ፤ በ
ሶስተኛ ደረጃ ለተመረጠው አሥራ ነጥብ፤በአሥራ ሁለተኛ ደረጃ ለተመረጠው አንድ
ነጥብ ተመደበ:: ከዚያም የደገገሙን ቁጥር በተመደበለት ቁጥር በማባዛት እያን
ዳንዱ ርዕስ ያገኘው ነጥብ ታውቆ ደረጃ ወጥቶለታል:: በዚህ መሠረት "ሰበለዱ
ሲነበብ ማዳመጥ" አንደኛ፤የቀነ ትምህርት ሁለተኛ፤የምቢሉያዊ አነጋገር ትምህርት
ሶስተኛ፤ ደረጃ አገንተው የተመረጡ ሲሆን የሰዋሰው ትምህርትና ሰበለዱ ያልሆኑ
ጽሑፎችን መጻፍ መጨረሻ ሆነው ተመርጠዋል:: /ለዝርዝሩ አባሪ "ጠ" ን ይመለ
ከቱ/

1.14 አሁን የምትማሯቸውን ትምህርቶች በጣም ከምትወዱት ጀምራችሁ በቀደም
ተከተል ጻፉ::

የአሥራ አንደኛ ክፍል የሣይንስም ሆኑ የአርት ተማሪዎች ስድስት ትምህር
ቶችን ይማራሉ:: አማርኛ፤እንግሊዝኛ፤ሒሳብና ባዮሎጂ ለሁለቱም ወገኖች የጋራ እወን
የሣይንስ ተማሪዎች ፊዚክስና ኬሚስትሪን፤የአርት ተማሪዎች ጂኦግራፊና ታሪክን ይጨ
ምራሉ:: በዚህ መሠረት በየትምህርት ቤቶቹ ያሉት ተማሪዎች የሚማሯቸውን ስድስት
የትምህርት ዓይነቶች ደረጃ የሰጧቸው ሲሆን ከላይ በ "1.13" ላይ እንደተጠቀ
ሰው የሁለቱንም ምላሽ አሰባሰብ ደረጃ ለማውጣት በአንደኛ ደረጃ ለተመረጠው ስድስት
ነጥብ ፤ በሁለተኛ ደረጃ ለተመረጠው አምስት ነጥብ፤ ... በስድስተኛ ደረጃ ለተ
መረጠው አንድ ነጥብ በመስጠት በደገገሙ ቁጥር ከተባዛ በኋላ የእያንዳንዱ ትምህ
ርት ደረጃ ታውቋል:: በዚህ መሠረት አማርኛ በሳይንስ ተማሪዎች ዘንድ ከስድስቱ
አራተኛ ደረጃ ሲያገኝ በአርት ተማሪዎች ዘንድ ከስድስቱ አንደኛ ደረጃን አገኝቷል
የሁለቱንም ተማሪዎች ውጤት አጠቃለን ስንመለከት ደግሞ አማርኛ ከስድስት የትምህርት
ይህ ደረጃ የአማርኛ ትምህርት

የሚወደዱ እንጂ የሚጠሉ አለመሆኑን ያሳያል። ለዝርዝሩ አባሪ "መ" ን ይመልከቱ።/ ደረጃ የሚወጣው በአማካይ ነጥብ እንጂ በነጥቦች ድምር አይደለም። ምክንያቱም ታሪክ ፣ ጂኦግራፊ ፣ ፊዚክስና ኬሚስትሪ ደረጃ የተሰጣቸው ከሁለት መቶ አሥር መላሾች ብቻ ሲሆን ቀሪዎቹ አራቱ ከአራት መቶ ሃያ ተማሪዎች ደረጃ ተሰጥቷቸዋልና /

በተሳውጠ አንዱ ላይ የተገኘው አማካይ ነጥብ 3.73 ሲሆን ለዝርዝሩ አባሪ "ሠ" ን ይመልከቱ.

4.3.2 <u>የወላጆች ፣ የኅብረተሰብና የእኩዮች አመለካከት፣</u>

በዚህ ተሳውጠ ሥር የቀረቡት ጥያቄዎች ሦስት የተለያዩ ወገኖችን ይመለከታሉ። የመጀመሪያዎቹ አራቱ ሐሳቦች የወላጆችን አመለካከት የሚጠይቁ ፣ በመሐል ያሉት አራት ጥያቄዎች ስለአካባቢው ኅብረተሰብ አመለካከት የሚጠይቁ ሲሆኑ የመጨረሻዎቹ አራቱ ደግሞ ስለ ተማሪው እኩዮች አመለካከት የሚጠይቁ ናቸው። ጠቅላላ ጥያቄዎቹ አሥራ ሁለት ሲሆኑ ስድስቱ በአዎንታዊ ፣ ስድስቱ ደግሞ በአሉታዊ ሐሣብ መልክ የተቀመጡ ናቸው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ የተሰጠው መልስ እንደሚከተለው ቀርቧል።

2.1 ወላጆቼ የአማራን ብሔረሰብ ይወዳሉ።

በዚህ ሐሣብ ላይ 43.3% "በጣም እስማማለሁ" ፣ 22.4% "እስማማለሁ" ፣ 23.8% "መወሰን ያስቸግረኛል" 5.2% "አልስማማም" ፣ 5.2 "ፈጽሞ አልስማማም" ብለዋል። አማካይ ነጥቡ 3.93 ነው።

በመረጃው መሠረት የተማሪ ወላጆች 65.7% የአማራን ብሔረሰብ ይወዳሉ። ብሔረሰቡን የወደደ ቋንቋውን ስለማይጠላ አማርኛ ቋንቋ ይወዳዳል ማለት ነው። በርግጥ ከመረጃው እንደሚታየው 10.4% የተማሪ ወላጆች የአማራን ብሔረሰብ ስለማይወዱ አማርኛ ቋንቋንም ሊጠሉት ይችላሉ። በሌላም በኩል ስለወላጆቻቸው አመለካከት መወሰን ያልቻሉ 23.8% ተማሪዎች ታይተዋል።

2.2 ወላጆቼ የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት መርጬ ለከፍተኛ ትምህርት እንድገፋበት አይፈቅዱም።

ለዚህ ሐሣብ 7.4% "በጣም እስማማለሁ" ፣ 7.1% "እስማማለሁ" ፣ 31.4% "መወሰን ያስገረኛል" ፣

20.2% " አለስማማም " ፣ 3.8% " ፍጹም አለስማማም " በማለት መልሰዋል:: አማካይ ነጥቡም 3.66 ነው::

በዚህ መረጃ መሠረት ተማሪዎች አማርኛን መርጠው ቢማሩ የማይከለከሉት ወላጆች 54% ሲሆኑ የማይፈቅዱት 14.5% ብቻ ናቸው:: በርካታ ተማሪዎች ደግሞ የወላጆቻቸውን አቋም ለመወሰን ተቸግረዋል::

2.3 ወላጆቹ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸን ዝንባሌ ያበረታታሉ::

በዚህ ሐሳብ ላይ 25.7% " በጣም እስማማለሁ " ፣ 23.3% " እስማማለሁ " ፣ 30% " መወሰን ያስቸግረኛል " ፣ 11.7% " አልስማማም " 9.3% " ፍጹም አለስማማም " ብለዋል:: አማካይ ነጥቡም 3.45 ነው::

በጥቅሉ የሐሳቡ ደጋፊዎች 49% ሲሆኑ ተቃዋሚዎች 21% ናቸው:: በዚህም ላይ በርካታ ተማሪዎች / 30% / የወላጆቻቸውን አቋም መወሰን አልቻሉም::

2.4 ወላጆቹ በቤት ውስጥ በአማርኛ እንድናገር አይፈልጉም::

ለዚህ ሐሣብ 9.5%. " በጣም እስማማለሁ " ፣ 6% " እስማማለሁ " ፣ 8.3% " መወሰን ያስቸግረኛል " ፣ 21% " አለስማማም " ፣ 55.2% ፍጹም አለስማማም ብለዋል:: አማካይ ነጥቡም 4.06 ነው::

የቀረበውን አሉታዊ ሐሣብ የተቃወሙት 76.2% ስለሆኑ አማርኛ በቤት ውስጥ በስፋት ይነገራል ማለቱ ነው:: በቤታቸው አማርኛን እንዳይናገሩ የሚከለከሉትና ምናልባትም የወላጆቻቸውን ቋንቋ ብቻ እንዲናገሩ የሚገደዱት 15.5% ብቻ ናቸው:: ቀሪዎቹ ጥቂት ተማሪዎች ለመወሰን የተቸገሩ ናቸው::

2.5 የሰፈሬ ሰዎች " አማርኛ በዙሃን ኢትዮጵያዊያንን ስለሚያገናኝ መማር ጥሩ ነው " እያሉ እንድማር ያበረታቱኛል::

በዚህ ሐሣብ ላይ 27.9% " በጣም እስማማለሁ " ፣ 21.2%. " እስማማለሁ " ፣ 25% " መወሰን ያስቸግረኛል " ፣ 13.1% " አለስማማም " ፣ 12.9% " ፍጹም አለስማማም " በማለት መልሰዋል:: አማካይ ነጥቡም 3.38 ነው::

በመረጃው መሠረት ይህ ሐሣብ 49.1% የተደገፈ ሲሆን 26% ተነ

ቀፏል:: 25 %. ተማሪዎች መወሰን አልቻሉም:: ስለዚህ ተማሪዎች አማርኛን እንዲማሩ በርካታው የአካባቢ ሕብረተሰብ ይደገፋል ማለት ነው::

2.6 የሰፈሬ ሰዎች « ከተማሪ አይቀር እንግሊዝኛ እንጂ አማርኛ ወንዝ አያሻግርም » እያሉ በትምህርቱ እንዳልገፋ ተስፋ ያስቆርጡኛል::

ለዚህ ሃሳብ 11 %. « በጣም እስማማለሁ » ፣ 11 %. « እስማማለሁ » ፣16.4 %. « መወሰን ያስቸግረኛል » ፣ 23.6 % « አልስማማም » 38.1 %. « ፍጹም አልስማማም » ብለዋል:: አማካይ ነጥቡ 3.67 ነው::

ይህንን አሉታዊ ሃሳብ 61.7 %. ተማሪዎች ሲቃወሙት 22 % ተማሪዎች ደግፈውታል:: ቀሪት መወሰን ያልቻሉ ተማሪዎች ቢኖሩም አብዛኛው ህብረተሰብ ተማሪዎች እንግሊዝኛን ወደው እንዲማሩና አማርኛን እንዲጠሉ አያደርግም ማለት ነው::

2.7 ብዙ ጉረቤቶቼ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ገፍቼ ጋዜጠኛና ደራሲ እንድሆን ይመክሩኛል::

በዚህ ሃሳብ ላይ 21.7 % « በጣም እስማማለሁ » ፣13.3 %. « እስማማለሁ » ፣23.3 « መወሰን ያስቸግረኛል » ፣ 19 %. « አልስማማም » 22.6 %. « ፍጹም አልስማማም » በማለት መልስ ዋል:: አማካይ ነጥቡ 2.92 ነው::

በመረጃው መሠረት 41.6 %. የአካባቢ ህብረተሰብ ተማሪዎች ጋዜጠኛና ደራሲ እንዲሆኑ አይመክሩም:: 35 %. የአካባቢ ህብረተሰብ ገን ተማሪዎች ጋዜጠኛና ደራሲ እንዲሆኑ ይመክራሉ:: በዚህ ጉዳይ ላይ መወሰን ያልቻሉ በርካታ ተማሪዎች ቢኖሩም ተማሪዎች ጋዜጠኛና ደራሲ እንዲሆኑ ከመምከር አኳያ አሉታዊ ጎኑ ጎልቶ ተንፀባርቋል::

2.8 የአከ[illegible]ሰዎች « አማርኛ የጨዋኞች ቋንቋነው » እያሉ ይጠሉታል::

በዚህ ሃሳብ ላይ 7.1 % « በጣም እስማማለሁ » ፣4 %. « እስማማለሁ » ፣ 11 %. « መወሰን ያስቸግረኛል » ፣16.2 %. « አልስማማም » 61.7 « ፍጹም አልስማማም » በማለት መልስ ዋል:: አማካይ ነጥቡ 4.21 ነው::

ከመረጃው ገለጽ ሆና እንደሚታየው 77.9 %. ተማሪዎች ሃሳቡን ሲቃወሙት 11.1 %. ብቻ ተቀብለውታል:: ስለዚህ አብዛኛው ህብረተሰብ አማርኛን የጨዋኞች ቋንቋ አድርገው በማሰብ አይጠሉም

2.9 ጉደኛ ቹ የአማርኛን ባህል ያደንቃሉ::

ለዚህ ሃሳብ 37.9 %. "በጣም እስማማለሁ" ፣20 %. "እስ ማማለሁ" ፣ 26.2 %. መወሰን ያስቸግረኛል" ፣ 7.1 %. "አለስማማም" 8.8 %." ፍጹም አለስማማም" ብለዋል:: አማካይ ነጥቡ 3.71 ነው::

የዚህ ሃሳብ ደጋፊዎች 57.9%.ሲሆኑ ተቃዋሚዎች 15.9 %.ና ቸው:: መወሰን ያልቻሉ በርካታ ተማሪዎች ቢኖሩም የብዙ ተማሪዎች ጉደኞች የአማ ርኛን ባሕል ስለሚያደንቁ በቀደምት ጽሑፋዊ መረጃዎች መሠረት አማርኛ ቋን ቋንም ያደንቃሉ ማለት ነው::

2.10 ጉደኛ ቹ አማርኛ ቋንቋን ይጠላሉ::

በዚህ ሃሳብ ላይ 5 %. "በጣም እስማማለሁ" ፣ 2.9 %. "እስ ማማለሁ" ፣14.8 "መወሰን ያስቸግረኛል" ፣24 %. "አለስማማም"፣ 53.3 %. "ፍጹም አለስማማም" በማለት መልሰዋል:: አማካይ ነጥቡም 4.19 ነው::

በመረጃው መሠረት ሃሳቡ 77.3 %. ተቀባይነት አሳገኘም:: ሃሳ ቡን የደገፉት 7.9 %.ብቻ ሲሆኑ ቀሪዎቹ መወሰን ያልቻሉ ና ቸው:: ስለ ዚህ የብዙሃን ተማሪ እኩዮችና ጉደኞች አማርኛ ቋንቋን አይጠሉም:: ተጠ የቀ ያዊ አካሄዱ በ "1.6" ላይ በተገለፀው መሠረት ይሆናል::

2.11 ጉደኛ ቹ ከሌሎች ቋንቋዎች ይበልጥ አማርኛን በስፋት ይጠቀማሉ::

ለዚህ ሃሳብ 65.2 %. "በጣም እስማማለሁ" ፣ 20%. "እስ ማማለሁ" ፣ 5.5 %." መወሰን ያስቸግረኛል" ፣ 3.6 %. አለስማማም" ፣ 5.7 %. "ፍጹም አለስማማም" ብለዋል:: አማካይ ነጥቡም 4.35 ነው::

ከመረጃዎቹ በገለጸ እንደሚታየው 85.2 %. ተማሪዎች በ ሃሳቡ ላይ ሲስማሙ 9.3 %. ብቻ አል ተስማሙም:: መወሰን ያልቻሉትም በጣም ጥቂ ቶች ና ቸው:: ስለዚህ ብዙሃኑ የተማሪ ጉደኞችና እኩዩች ከሌሎች ቋንቋ ዎች ይበልጥ አማርኛን በስፋት ይጠቀሙበታል::

2.12 ጉደኛ ቹ "የአማርኛ ትምህርት ቀላል ነው" እያሉ ይገቃሉ::

በዚህ ሃሳብ ላይ 19%. "በጣም እስማማለሁ"፣14.8 %. "እስማማለሁ" ፣15.2 %. "መወሰን ያስቸግረኛል" ፣ 23.3%. "አለስማማም" ፣ 27.6 %. " ፍጹም አለስማማም" በማለት መልሰዋል::

አማካይ ነጥቡም 3.26 ነው::

መረጃዎቹ እንደሚጠቁሙት 50.9 %. መሳሾች ሃሣቡን አለተቀበሉትም:: ሃሣቡን የደገፉት 33.8 %. ሲሆኑ ቀሪዎቹ መወሰን ያልቻሉ ናቸው:: ስለዚህ አማርኛ ቋንቋ በብዙ የተማሪ ጊደኖችና እኩዮች ዘንድ አይናቅም::

በዚህ ተሳውጦ ላይ ከቀረቡት አሥራ ሁለት ጥያቄዎች ከአንዱ በስተቀር ሌሎቹ ሁሉ አዎንታዊ ሆነው ተመለስዋል:: ስለዚህ የተማሪ ወላጆች ህብረተሰቡና እኩዮች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አዎንታዊ አመለካከት አላቸው ማለት ነው::

"የዚህ" ተሳውጦ (ሁለት) አማካይ ነጥብ 3.73 ሲሆን ለዝርዝሩ አባሪ "ረ" ይመልከቱ::

---

## 4.3.3 የአማርኛ ቋንቋ መምህር ጠባይ፣ችሎታና አመለካከት

በዚህ ተሳውጦ ሥራ የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች ስለ መምህራን ጠባይ፣ችሎታና አመለካከት የሚያውቁትን ሃሣብ እንዲሰጡ የሚያደርጉ ናቸው:: ጥያቄዎቹ ስድስት አዎንታዊ፣ስድስት አሉታዊ፣በድምሩ አሥራ ሁለት ናቸው:: ጥያቄዎቹንና መልሶቻቸውን እንደሚከተለው እናቀርባለን::

3.1 መምህሩ ተማሪዎች አማርኛንና የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት እንዲወዱ ጥረት ያደርጋል::

በዚህ ሃሣብ ላይ 52.9 %. "በጣም እስማማለሁ" ፣ 23.6 %. "እስማማለሁ" ፣ 6.2 %. "መወሰን ያስቸግረናል" ፣ 6 %. "አለስማማም" ፣ 11.4 %. "ፍጹም አለስማማም" በማለት መልሰዋል:: አማካይ ነጥቡም 4.00 ነው:: ስለዚህ 76.5 %. ተማሪዎች ሃሣቡን ስለደገፉ መምህራን ተማሪዎችን አማርኛንና የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት እንዲወዱ ጥረት ያደርጋሉ ማለት ነው::

3.2 መምህሩ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በቂ ዕውቀት የለውም::

ለዚህ ሃሣብ "በጣም እስማማለሁ" 7.6 %. ፣ "እስማማለሁ" 8.1 %. ፣ "መወሰን ያስቸግረናል" 13.8 %, ፣ "ፍጹም አለስማማም" 52.1 %. መልስ የሰጠ ሲሆን አማካይ ነጥቡም 3.99 ነው::

በመረጃው መሠረት 70.4% ተማሪዎች ሐሣቡን ስለተ

ቋንቋ መምህራን ለክፍሉ ደረጃ የሚበቃ ዕውቀት እንዳላቸው እንገነዘባለን።

3.3 መምህሩ የተማሪዎችን ጉጉትና የሚቀሰቅስ ማራኪ አቀራረብ አለው።

ለዚህ ሐሳብ 32.4% " በጣም እስማማለሁ "፣ 24.5% " እስማማለሁ "፣ 14% " መወሰን ያስቸግረኛል "፣ 9.5% " አልስማማም "፣ 19.5% " ፍጹም አልስማማም " ብለዋል። አማካይ ነጥቡም 3.41 ነው።

በመረጃው መሠረት 56.9% ተማሪዎች የመምህሩ አቀራረብ ማራኪ መሆኑን የደገፉ ሲሆን 29% ተቃውመውታል። ሌሎቹ መወሰን ያልቻሉ ናቸው። ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት አቀራረብ ሙሉ በሙሉ የተደገፈ ባይሆንም አዎንታዊ ምላሹ ከአሉታዊ ምላሹ በልጦ ይታያል።

3.4 መምህሩ ተማሪዎችን የሚያንቋሽሽ ቁጡና ጉጋቢ ነው።

በዚህ ሐሳብ ላይ 10.5% " በጣም እስማማለሁ "፣ 7.4% " እስማማለሁ "፣ 8.3% " መወሰን ያስቸግረኛል "፣ 22.6% " አልስማማም "፣ 51.2% " ፍጹም አልስማማም " በማለት መልሰዋል። አማካይ ነጥቡም 3.97 ነው።

ከመረጃው በግልጽ እንደሚታየው በአሉታዊ ሐሳቡ ላይ የተስማሙት 17.9% ብቻ ሲሆኑ መወሰን ያልቻሉትም ጥቂቶች ናቸው። በርካታ ተማሪዎች /73.8%/ ሐሳቡን ተቃውመውታል። ስለዚህ በርካታዎቹ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎችን አያንቋሽሹም፣ አይቆጡም፣ አይሳደቡም ማለት ነው።

3.5 መምህሩ የግል ጥረቱን እያከለ የቋንቋ ችሎታዎችን / ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ / በሚገባ ያለማምዳል።

ለዚህ ሐሳብ 40.7% " በጣም እስማማለሁ "፣ 23.8% " እስማማለሁ "፣ 9.7% " መወሰን ያስቸግረኛል "፣ 11.7% " አልስማማም "፣ 19% " ፍጹም አልስማማም " ብለዋል አማካይ ነጥቡም 3.65 ነው።

ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የግል ጥረታቸውን እያከሉ እንደሚሠሩ ብዙ ተማሪዎች / 64.5% / መስክረዋል።

3.6 መምህሩ ብዙ ጊዜ ሳይዘጋጁ ክፍል ይገባሉ::

በዚህ ሃሳብ ላይ 9.5 % "በጣም እስማማለሁ" ፣ 7.6 % "እስማማለሁ" 12.6 % "መወሰን ያስቸግረኛል" ፣ 24 % "አልስማማም" ፣ 46.2 % "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል:: አማካይ ነጥቡም 3.90 ነው::

ይህንን አሉታዊ ሃሳብ የደገፉት 17.1 % ብቻ ሲሆኑ 70.2 % ተቃውመውታል:: ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሳይዘጋጁ ክፍል አይገቡም ማለት ነው::

3.7 መምህሩ ተማሪዎች ከፍላጎታቸው መሠረት ተደስተው እንዲማሩ ያማክራቸዋል::

ለዚህ ሃሳብ 30.2 % "በጣም እስማማለሁ" ፣ 19.3 % "እስማማለሁ" ፣ 16.9 % "መወሰን ያስቸግረኛል" ፣ 18.1 % "አልስማማም" ፣ 15.5 % "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል:: አማካይ ነጥቡም 3.31 ነው::

በመረጃው መሠረት የሃሳቡ ደጋፊዎች 49.5 % ሲሆኑ ተቃዋሚዎች 33.6 % ናቸው:: ስለዚህ የሃሳቡ ተቃዋሚዎች ቁጥር የማይናቅ ቢሆንም ደጋፊዎች በልጠው በመገኘታቸው ሚዛኑ ወደ አዎንታዊ ሃሳብ አጋድሎ ይታያል::

3.8 መምህሩ ማርክ /ነጥብ/ አሰጣጡ አድሏዊ ነው::

በዚህ ሃሳብ ላይ 9.5 % "በጣም እስማማለሁ" ፣ 2.6 % "እስማማለሁ" ፣ 8.8 % "መወሰን ያስቸግረኛል" ፣ 21.9 % "አልስማማም" ፣ 57.1 % "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል:: አማካይ ነጥቡም 4.15 ነው::

ከመረጃው በግልጽ እንደሚታየው አሉታዊ ሃሳቡን 12.1 % ብቻ የደገፉትና ጥቂቶች "መወሰን ያስቸግረኛል" ሲሉ 79 % ሃሳቡን ተቃውመውታል:: ስለዚህ የአማርኛ መምህራን የማርክ /ነጥብ/ አሰጣጣቸው አድሏዊ አይደለም ማለት ነው::

3.9 መምህሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንዲገፉ ያበረታታቸዋል::

ለዚህ ሃሳብ 35.7 % "በጣም እስማማለሁ" ፣ 28.1 % "እስማማለሁ" ፣ 13.6 % "መወሰን ያስቸግረኛል" ፣ 11.9 % "አልስማማም" ፣ 10.7 % "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል:: አማካይ ነጥቡም 3.66 ነው::

በመረጃው መሠረት 63.8 %. ተማሪዎች ሃሳቡን የደገፉ ሲሆን የ ተቃወሙት 22.6 %. ና ቸው:: ቀሪዎቹ መወሰን ያልቻሉ እንደመሆናቸው መጠን ሁለቱን ወገኖች ስናነፃፀር አወንታዊ ሃሳብ የሰጡት በለጠው ስለታዩ በብዙሃን ሃሳብ መሠረት መምህራኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንዲደገፏ ያበረታቷቸዋል ማለት ነው::

3.10 መምህሬ አማርኛን እንደማይወዱና ለደቆዙ ሲል ብቻ እንደሚያስተምር ይናገራል::

ለዚህ ሃሳብ 6.2 %. "በጣም እስማማለሁ" ፣ 1.2 %. "እስማማለሁ" ፣ 10 %. "መወሰን ያስቸግረኛል" ፣ 21 %. "አልስማማም" ፣ 61.7 %. "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል:: አማካይ ነጥቡም 4.31 ነው::

ከመረጃዎቹ በግልጽ እንደሚታየው አሉታዊ ሃሳቡን 7.4 %. መሳሽች ብቻ ሲደገፉት 82.7 % መሳሾች ተቃውመውታል ስለዚህ የአማርኛ መምህራን አማርኛን እንደሚጠሉና ለደቆዝ ሲሉ ብቻ እንደሚያስተምሩ አይናገሩም::

3.11 መምህሬ የሚሰጠውን የክፍልና የቤት ሥራዎች ያርማል::

በዚህ ሃሳብ ላይ 42.1 %. "በጣም እስማማለሁ" ፣ 31 %. "እስማማለሁ" ፣ 7.1 %. "መወሰን ያስቸግረኛል" ፣ 10.7 %. "አልስማማም" ፣ 9 %. "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል:: አማካይ ነጥቡም 3.93 ነው::

ከመረጃው እንደሚታየው 73.1 %. ሃሳቡ የተደገፈ ሲሆን 19.7 % ብቻ ተቃውሞ ገጥሞታል:: ስለዚህ በብዙሃን አስተያየት መሠረት የአማርኛ መምህራን የሚሰጡትን የክፍልና የቤት ሥራ ያርማሉ ማለት ነው::

3.12 መምህሬ ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ በቂ ዕድል አይሰጥም::

ለዚህ ሃሳብ 12.6 %. "በጣም እስማማለሁ" ፣ 11.9 %. "እስማማለሁ" ፣ 6.7 %. "መወሰን ያስቸግረኛል" ፣ 24.8 %. "አልስማማም" 44 %. "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል:: አማካይ ነጥቡም 3.76 ነው::

ቁጥራቸው 24.5 %. ሲሆኑ ጥቂቶቹ መወ ይህን አሉታዊ ሃሳብ የደገፉት 24.5 %. ሲሆኑ ጥቂቶቹ መወ

68.8 %. በ ሃሳቡ ላይ ተቃውሞ ስላቀረቡ

በብዙሃን ሃሳብ መሠረት መምህራን ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ በቂ ዕድል ይሰጧሉ ማለት ነው።

የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን በተመለከተ በዚህ ተሳጥመ የቀረቡት ጥያቄዎች ሁሉ አዎንታዊ ምላሽ ያገኙ ሲሆን አማካይ ነጥቡም 3,84 ነው። ስለ ተሳውጦ ሰስት የተጠቃለሉ መረጃዎችን ለማግኘት አባሪ "ሰ" ን ይመልከቱ።

## 4.3.4 የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ሁኔታ

ይህ ክፍል ስለመማሪያ መጻሕፍት አጠቃላይ ሁኔታ ተማሪዎች የሚያውቁትን እንዲመልሱ የሚጠይቅ ሲሆን አሥራ ሁለት ጥያቄዎችን አቀፏል። ቀጥለን ዝርዝር ጥያቄዎችንና መልሶቻቸውን እንመለከታለን።

4.1 በትምህርት ቤታችን በቂ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት አሉ።

ለዚህ ሃሳብ 35%. "በጣም እስማማለሁ" ፣15.5%. "እስማማለሁ" 16.4 "መወሰን ያስቸግረኛል" ፣ 12.4%. "አልስማማም" ፣20.7%. "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል። አማካይ ነጥቡም 3.36 ነው።

በተገኘው መረጃ መሠረት 50.5%, መላሾች በቂ መማሪያ መጻሕፍት እንዳሉ ሲያቀርቡ 33.1%. መላሾች ደግሞ በቂ መማሪያ መጻሕፍት እንደሌሉ ተናግረዋል። መወሰን ያልቻሉትም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። የሆነው ሆኖ አብላጫው እጅ በቂ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍት እንዳሉ አቅርበዋል።

4.2 የአሥራ አንደኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የተማሪዎችን ፍላጎት አያንፀባርቅም።

በዚህ ሃሳብ ላይ 18.8%. "በጣም እስማማለሁ" ፣ 17.6%. "እስማማለሁ" ፣ 21.2%. "መወሰን ያስቸግረኛል" ፣19%. "አልስማማም" ፣23.3%. "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል። አማካይ ነጥቡም 3.10 ነው።

የዚህ አሉታዊ ሃሳብ ደጋፊዎች 36.4%. ሲሆኑ ተቃዋሚዎች 42.3%. ናቸው። መወሰን ያልቻሉም በርካታ ናቸው። የደጋፊና የተቃዋሚ ቁጥሮች የተቀራረቡ ቢሆኑም አማካይ ነጥቡ ለትንሽ ወደ አወንታዊነት አዘንብሎ ይታያል።

4.3 በአማርኛ መማሪያ መጻሕፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ማራኪና ናቸው::

ለዚህ ሃሳብ 31 %. "በጣም እስማማለሁ" ፣ 35.2 %. "እስማማለሁ" ፣16.2 %. "መወሰን ያስቸግረኛል" ፣10.5 %. "አለስማማም" ፣7.1 %. "ፍጹም አለስማማም" ብለዋል:: አማካይ ነጥቡም 3.70 ነው::

በመረጃው መሠረት 66.2 %. መላሾች ሃሳቡን ሲደግፉ 17.6 % ብቻ ተቃውሞ አቅርበዋል:: ስለዚህ በብዙሃን ምላሽ መሠረት በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ማራኪ ና ናቸው::

4.4 የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ማንበብ ያስጠሏናል

በዚህ ሃሳብ ላይ 11.2 %. "በጣም እስማማለሁ" ፣7.6 %. "እስማማለሁ" ፣7.9 %. "መወሰን ያስቸግረኛል" ፣29.5 %. "አለስማማም" ፣43.8 %. "ፍጹም አለስማማም" በማለት መልሰዋል:: አማካይ ነጥቡም 3.83 ነው::

ከመላሾቹ እንደሚታየው አሉታዊ ሃሳቡን የደገፉት 18.8 %. ብቻ ሲሆኑ፣ ተቃዋሚዎች 73.3 %. ና ቸው:: ስለዚህ በብዙሃኑ ሃሳብ መሠረት ተማሪዎች የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ማንበብ አያስጠላቸውም::

4.5 በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ምንባቦች በግልጽ ቋንቋ የቀረቡ ና ቸው::

ለዚህ ሃሳብ 29 %. "በጣም እስማማለሁ" ፣33.3 %. "እስማማለሁ" ፣16.6 %. "መወሰን ያስቸግረኛል" ፣13.8 %. "አለስማማም" ፣6.9 %. "ፍጹም አለስማማም" ብለዋል:: አማካይ ነጥቡም 3.64 ነው::

ከመረጃው መረዳት እንደሚቻለው ሃሳቡ 62.3 %. ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን 20.7 %. ተቃውሞ ገጥሟታል:: ስለዚህ በብዙሃን ምላሽ መሠረት በአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ምንባቦች በግልጽ ቋንቋ የቀረቡ ና ቸው::

4.6 የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ በሥዕላዊ መግለጫዎች ስላልታጀበ አይስበኝም::

በዚህ ሃሳብ ላይ 13.1 %. "በጣም እስማማለሁ" 14.3 %. "እስማማለሁ" ፣13.3 %. "መወሰን ያስቸግረኛል" ፣ 27.4 %. "አለስማማም" ፣31.9 %. "ፍጹም አለስማማም" በማለት መልሰዋል::

አማካይ ነጥቡም 3.51 ነው::

በመረጃው መሠረት የአሉታዊ ሃሳቡ ደጋፊዎች 27.4 %. ሲሆን ተቃዋሚዎች 59.3 %. ና ቸው:: ስለዚህ መጽሐፉ በሥዐላዊ መግለጫዎች ባይ ታጀበም ተማሪዎችን መሳብ ችሏል ማለት ነው::

4.7 በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያቀረቡት መለመጃዎች ጥሩ ና ቸው::

በዚህ ሃሳብ 29,3 %. "በጣም እስማማለሁ" ፣37.6 %. "እስ ማማለሁ" ፣ 14.3 %. "መወሰን ያስቸግረናል" ፣10.2 %. "አለስማማም" 8.6 %." ፍጹም አለስማማም" ብለዋል:: አማካይ ነጥቡም 3.88 ነው::

በመረጃው መሠረት 66.9 %. መሰሾች ሃሳቡን ሲደግፉ 18.8 %. ብቻ ተቃወመውታል:: ስለዚህ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት መለመጃ ዎች ጥሩ ና ቸው ማለት ነው::

4.8 መጽሐፉ የቃላትን ዝርዝር ከነትርጓሜ ቸው የሚያሣይ አባሪ ስለሌለው ብቃት የለውም::

በዚህ ጥያቄ ላይ 29.5 %. "በጣም እስማማለሁ" 24 %. "እስማማለሁ" ፣21 %. "መወሰን ያስቸግረናል" ፣16 %."አለስማማም"፣ 9.5 %. "ፍጹም አለስማማም" በማለት መልሰዋል:: አማካይ ነጥቡም 2.52 ነው::

ይህን አሉታዊ ሃሳብ የደገፉት 53.5 %. ሲሆኑ 25.5 %. ደግሞ ተቃውመውታል:: በርካታ ተማሪዎችም ለመወሰን ተቸግረዋል:: ስለዚህ "መጽሐፉ የቃላትን ዝርዝር የሚያሳይ አባሪ ስለሌለው ብቃት የለውም" የሚለው ሃሳብ ሚዛን ደፋ ታይ ቷል::

4.9 መጽሐፉ አስ ተማሪ ባይኖርም ተማሪውን መምራት ይችላል::

ለዚህ ሃሳብ 17.9 %. "በጣም እስማማለሁ" ፣ 17.1 %. "እስማማለሁ" ፣19.3 %. "መወሰን ያስቸግረናል" ፣23.8 %. "አለስማማም" ፣21.9 %. "ፍጹም አለስማማም" ብለዋል:: አማካይ ነጥቡም 2.85 ነው::

ይህንን ሃሳብ የተቃወሙት 45.7 %. ሲሆኑ ደጋፊዎች 35 %. ና ቸው:: ቁጥሮቹ የተቀራረቡ ቢመስሉም አጠቃላይ ውጤቱ ወደ አሉታዊነት አዘንብሎ ይታያል:: ስለዚህ መጽሐፉ ያለአስ ተማሪ ተማሪውን መምራት

4.10 መጽሐፉ የቋንቋን ትምህርት ዓላማዎች አያንፀባርቅም::

በዚህ ሃሳብ 12.1%. “ በጣም እስማማለሁ” ፤13.1%. “ እስማማለሁ” ፤14.8%. “ ለመወሰን ያስቸግረኛል” ፤31% “ አልስማማም” ፤29%. “ ፍጹም አልስማማም” በማለት መልሰዋል :: አማካይ ነጥቡም 3.52 ነው ::

በተጠቀሱት መረጃዎች መሠረት 60%. መላሾች ሃሳቡን የተቃወሙት ሲሆኑ 25.2%. ደግፈውታል:: ስለዚህ በብዙዎች ሃሳብ መሠረት መጽሐፉ የቋንቋን ትምህርት ዓላማዎች አያንፀባርቃል ማለት ነው::

4.11 መጽሐፉ የቋንቋ ዘርፎችን ሁሉ አካቶ ያቀርባል::

ለዚህ ሃሳብ 18.8%. “ በጣም እስማማለሁ” ፤14.5%. “ እስማማለሁ” ፤16.7%. “ለመወሰን ያስቸግረኛል” ፤25.5%. “ አልስማማም” ፤24.5%. “ ፍጹም አልስማማም” ብለዋል:: አማካይ ነጥቡም 2.65 ነው::

በመረጃው መሠረት 50%. መላሾች ሃሳቡን ተቃውመውታል:: 33.3%. ደግሞ የሃሳቡ ደጋፊዎች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ለመወሰን የተቸገሩ ናቸው:: ስለዚህ መጽሐፉ የቋንቋ ዘርፎችን አካቶ እንደማያቀርብ ብዙዎቹ ተስማምተውበታል:: አማካይ ነጥቡም የሚያሳየው በአሉታዊ ክልል ውስጥ መሆኑን ያሳያል::

4.12 መጽሐፉ በምዕራፍና በክፍለ ጊዜ ስላልተከፋፈለ ለአጠቃቀም ምቹ አይደለም::

በዚህ ሃሳብ ላይ 11%. “ በጣም እስማማለሁ” ፤11.7%. “ እስማማለሁ” ፤21.4%. “ ለመወሰን ያስቸግረኛል” ፤28.6% “ አልስማማም” ፤27.4%. “ ፍጹም አልስማማም” በማለት መልሰዋል አማካይ ነጥቡም 3.50 ነው::

መረጃው እንደሚጠቁመው 22.7%. መላሾች ብቻ ሃሳቡን ሲደግፉት 55%. ተቃውመውታል:: ስለዚህ መጽሐፉ በምዕራፍና በክፍለ ጊዜ ባይከፋፈልም ለብዙዎቹ ተማሪዎች በአጠቃቀም ላይ ችግር አላመጣም::

በተሰጠው አራት ከቀረቡት አሥራ ሁለት ጥያቄዎች ሶስቱ ብቻ አሉታዊ መልስ ሲያገኙ የቀሩት በሙሉ አዎንታዊ ምላሽ አግኝተዋል:: የተሰጠው አማካይ ነጥብ 3.33 ነው:: ስለ ተሰጠው የተጠቃለሉ መረጃዎችን

... ይመለከቱ::

4.3.5. ትምህርት ቤቶችን፣መማሪያ ክፍሎችን፣ድጋፍሰጪ ነገሮችንና የማስ ተማር ዘዴዎችን በተመለከተ::

በዚህ ተሳውጦ ሥር በርዕሱ የተጠቀሱት አራት ጉዳዮች ተጠቃለው ቀርበዋል:: አራቱንም ጉዳዮች በተመለከተ አሥራ ሁለት አወንታዊና አሉታዊ ሃሳቦች ተደባልቀው የቀረቡ ሲሆን ዝርዝሩ እንደሚከተለው ይሆናል::

5.1 በመማሪያ ክፍሎቻችን በቂ መቀመጫ ስላለ ብዛናንተን እንቀመጣለን::

በዚህ ሃሳብ 25 %. " በጣም እስማማለሁ " ፣18.3 %. " እስማማለሁ " ፣7.4 %. " መወሰን ያስቸግረኛል " ፣ 13.1 %. " አልስማማም " ፣36.2 " ፍጹም አልስማማም " ብለዋል:: አማካይ ነጥቡም 2.83 ነው::

ከመረጃዎቹ መረዳት እንደሚቻለው በሃሳቡ ላይ ከተስማሙት መላሾች ይልቅ የተቃወሙት በልጠው ተገኝተዋል:: ተስማሚዎቹ 43.3 %. ሲሆኑ ተቃዋሚዎቹ 49.3 %.ና ቸው:: አማካይ ነጥቡም ምላሹ በአሉታዊ ክልል ውስጥ መሆኑን ያመለክታል:: ስለዚህ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ብዛናንተው ሊቀመጡ አልቻሉም::

5.2 የአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በአንድ ሰዓት ላይ ስለሆነ የመማሪያ ክፍሉ ሙቀት ያስጨንቀናል::

በዚህ ሃሳብ ላይ 18.6 % " በጣም እስማማለሁ " ፣ 11.4 %. " እስማማለሁ " ፣15.5 "መወሰን ያስቸግረኛል " ፣ 26.9 %. " አልስማማም " ፣27.6 %. " ፍጹም አልስማማም " በማለት መልሰዋል።አማካይ ነጥቡም 3.34 ነው::

በመረጃው መሠረት የተስነዘረው ሐሳብ 30% ድጋፍ ሲያገኝ 54.5% ተነቀፈ። ስለዚህ በርካታ ተማሪዎች የመማሪያ ክፍሉ ሙቀት አያስጨንቃቸውም::

5.3 በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የመማሪያ ክፍላችን ሥነ_ሥርዓት በሚገባ ይጠበቃል::

ለዚህ ሐሳብ 31.2% " በጣም እስማማለሁ " 24% " እስማማለሁ " ፣ 14.8% " መወሰን ያስቸግረኛል " ፣ " ፣ 14% " ፍጹም አልስማማም "

በለዋል:: አማካይ ነጥቡም 3.42 ነው::

መረጃው እንደሚጠቁመን 55.2% መላጆች ሐሣቡን ተቀብለውታል:: 30% መላሾች ሐሣቡን ቢቃወሙትም በብዙሃን ምስክርነት መሠረት በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የመማሪያ ክፍል ሥነ_ሥርዓት ይጠበቃል::

5.4 የክፍሏችን ጥቁር ሠሌዳ የተበላሸ ስለሆነ ጽሑፍ አይቀበልም::

በዚህ ሐሣብ ላይ 6.2% " በጣም እስማማለሁ " 7.4% " እስማማለሁ " ፣ 7.9% " መወሰን ያስቸግረኛል " ፣ 28.1% " አልስማማም " ፣ 50.5% " ፍጹም አልስማማም " በማለት መልሰዋል:: አማካይ ነጥቡም 4.09 ነው::

በመረጃው መሠረት 78.6 መላሾች ሐሣቡን ውድቅ አድርገውታል:: በሐሣቡ የተስማሙትም ሆኑ መወሰን ያልቻሉት ጥቂቶች ናቸው:: ስለዚህ በየ ክፍሎቹ የሚገኙት ጥቁር ሠሌዳዎች ደህና ናቸው ማለት ነው::

5.5 የአማርኛ መማሪያ ክፍሏችን ብርድ በማያስገባ ተስማሚ ቦታ ላይ ይገኛል::

ለዚህ ሐሣብ 23.1% " በጣም እስማማለሁ " ፣ 22.6% " እስማማለሁ " ፣ 16.9% " መወሰን ያስቸግረኛል " ፣ 18.1% " አልስማማም " ፣ 19.3 " ፍጹም አልስማማም " ብለዋል:: አማካይ ነጥቡም 3.12 ነው::

ይህ ሐሣብ 45.7% የተደገፈ ሲሆን 37.4% ተነቅፏል:: አቋም_ ያልወሰዱትም በርካታ ናቸው:: ስለዚህ ደጋፊዎችና ተቃዋሚዎች ተቀራራቢ ቢሆኑም አማካይ ነጥቡ ለትንሽ ወደ አወንታዊነት አድልቶ ይታያል:: ይህ ማለት በአማርኛ ትምህርት ክፍል ውስጥ ከሚበርዳቸው ተማሪዎች የማይበርዳቸው ይበዛሉ ማለት ነው::

5.6 የአማርኛ ትምህርት በሰፊ መረጃ መሣሪያ ቀርቦልን አያውቅም::

በዚህ ሐሣብ ላይ 42.6% " በጣም እስማማለሁ " ፣ 22.1% " እስማማለሁ " ፣ 88% " መወሰን ያስቸግረኛል " 10.5% " አልስማማም " ፣ 16% " ፍጹም አልስማማም " በማለት መልሰዋል:: አማካይ ነጥቡም 2.35 ነው::

ከመረጃው እንደምንረዳው 64.7% መላሾች ሐሣቡን የደገፉ ሲሆን 26.5% ተቃውመውታል:: ስለዚህ በብዙሃን ምስክርነት መሠረት የአማርኛ

ትምህርት በልዩ ልዩ መረጃ መሣሪያ አይቀርብም::

5.7 የአማርኛን ትምህርት በተለያዩ ዘዴዎች ስለምንማር ይስበናል::

ለዚህ ጠሣብ 19.8% " በጣም እስማማለሁ " ፣ 20.7% " እስማማለሁ " ፣ 15% " መወሰን ያስቸግረኛል " ፣ 20.7% "አልስማማም " ፣ 23.8% " ፍጹም አልስማማም " ብለዋል:: አማካይ ነጥቡም 2.92 ነው::

የቀረበው ጠሣብ 40.5% ሲደገፍ 44.5% ተነቀፏል:: ቀሪዎቹ መወሰን ያልቻሉ ና ቸው:: የደጋፍና የተቃውሞ ጠሣቦች ተቀራራቢ ቢሆኑም ለትንበ ተቃዋሚዎች ስለበለጡ አማካይ ነጥቡ ወደ አሉታዊ ከፊል አጋደሉ ይታያል:: ስለዚህ የአማርኛን ትምህርት በተለያዩ ዘዴዎች ስለማይማሩ ብዙ ተማሪዎች አይሣቡም::

5.8 የአማርኛ ትምህርት የአቀራረብ ዘዴው ትምህርቱን እንድጠላ አድርጓል::

በዚህ ጠሣብ ላይ 13.6% " በጣም እስማማለሁ " 11% " እስማማለሁ" ፣ 15.5% " መወሰን ያስቸግረኛል " ፣ 31.2% " አልስማማም" 28.8% " ፍጹም አልስማማም " በማለት መልሰዋል:: አማካይ ነጥቡም 3.51 ነው::

መረጃው እንደሚያሳየው ይህ አሉታዊ ጠሣብ 60% የተነቀፈ ሲሆን 24.6% ተደግፏል:: በዚሁ ተለጣጠ በ" 5.6 " እና በ" 5.7 " ላይ በቀረቡት መረጃዎች መሠረት የአማርኛ ትምህርት በልዩ መረጃ መሣሪያና በተለያዩ ዘዴዎች አይቀርብላቸውም:: ይሁን እንጂ ከዚህኛው መረጃ እንደምንረዳው የቱንም ያህል የአቀራረብ ዘዴው ደካማ ቢሆን ተማሪዎች ትምህርቱን እንዲጠሉ አላደረገም::

5.9 ት/ቤታችን ወቅታዊ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ስለሚያቀርብልን ለአማርኛ ትምህርት እየተከረታታን ነው::

በዚህ ጠሣብ ላይ 7.9% " በጣም እስማማለሁ" ፣ 9.8% " እስማማለሁ " ፣ 11.7% " መወሰን ያስቸግረኛል" ፣ 22.4% " አልስማማም" ፣ 48.3% " ፍጹም አልስማማም " በማለት መልሰዋል:: አማካይ ነጥቡም 2.06 ነው::

ከመረጃዎቹ ግለጽ ሆኖ እንደሚታየው የተሰነዘረው ሐሣብ 17.7% ብቻ ሲደገፍ 70.7% ተነቀፈ:: ስለዚህ ት/ቤቶች ወቅታዊ ጋዜጣችንና መጽሔቶችን እያቀረቡ ተማሪዎችን ለአማርኛ ትምህርት እያበረታቱም::

5.10. በትምህርት ቤታችን ቤተመጽሐፍት የአማርኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላት ባለመኖራቸው ተቸግረናል::

ለዚህ ሐሣብ 21.9%. " በጣም እስማማለሁ " ፣ 11% " እስማማለሁ " ፣ 19.3% " መወሰን ያስቸግረናል "፣ 23.3% " አልስማማም " ፣ 24.5% " ፍጹም አልስማማም " ብለዋል:: አማካይ ነጥቡም 3.18 ነው::

በመረጃው መሠረት በሐሣቡ ላይ የተስማሙት 32.9% ሲሆኑ ያልተስማሙት 47.8% ናቸው:: አቋም ያልወሰዱ ተማሪዎችም በርካታ ናቸው:: ያም ሆነ ይህ በትምህርት ቤታቸው መዝገበ ቃላት አጥተው ከሚቸገሩት ተማማሪዎች የማይቸገሩት በርከተው ተገኝተዋል::

5.11. በትምህርት ቤታችን ቤተመጻሕፍት የአማርኛን ትምህርት የሚያግዙ በቂ ልብለድና ልብለድ ያልሆኑ መጻሕፍት አሉ::

በዚህ ሐሣብ ላይ 24.8% " በጣም እስማማለሁ " ፣ 21.7% " እስማማለሁ " ፣ 20.2% " መወሰን ያስቸግረኛል " ፣ 14.3% " አልስማማም " ፣ 19% " ፍጹም አልስማማም " በማለት መልሰዋል:: አማካይ ነጥቡም 3.19 ነው::

ከመረጃው እንደሚታየው 46.5% መላሾች ሐሣቡን ሲቀበሉ 33.3% አልተቀበሉትም:: አቋም ያልወሰዱ ተማሪዎችም በርካታ ናቸው:: ስለዚህ በብዙዎች ግምት የአማርኛን ትምህርት የሚያግዙ በቂ ልብለድና ልብለድ ያልሆኑ መጻሕፍት አሉ::

5.12. በትምህርት ቤታችን የአማርኛን ትምህርት የሚያግዙ በቂ ክበባት አልተቋቋሙም::

ለዚህ ሐሣብ 33.6% " በጣም እስማማለሁ " ፣ 18.6% " እስማማለሁ " ፣ 11.4% " መወሰን ያስቸግረኛል " ፣ 16.7% " አልስማማም " ፣ 19.8% " ፍጹም አልስማማም " ብለዋል:: አማካይ ነጥ

በመረጃው መሠረት 52.2 % መላሾች ሃሣቡን ሲደግፉ .. 36.5 ተቃውመውታል:: ስለዚህ በብዙዎቹ ሃሣብ መሠረት በትምህርት ቤቶች የአማርኛን ትምህርት የሚያገዙ በቂ ከበቢት አል ተቋቋሙም::

በዚህ ጥናት መጠይቅ ውስጥ ከቀረቡት አምስት ተሳውጦዎች ውስጥ በርካታ አሉታዊ ሐሣቦች የተንፀበረቁት በዚህ ተሳውጠ ውስጥ ነው:: ከአሥራ ሁለቱ ጥያቄዎች ውስጥ አምስቱ በአሉታዊ መልክ ተመለስዋል:: ያም ሆኖ ሰባቱ ጥያቄዎች በአዎንታዊ መልክ በመመለሳቸው የተሳውጠው አማካይ ነጥብ <u>3.06</u> ሆኗል:: ይህ ነጥብ ወደ አወንታዊ ከለለ ያለ ቢመስለም ድንበር ላይ ስለሆነ በትምህርት ቤቶች ፣ በመማሪያ ክፍሎች፣ በድጋፍ ሰጪ ነገሮችና በማስተማር ዘዴዎች ዙሪያ ችገር መኖሩን ይጠቁ ማል:: ስለ ተሳውጠ አምስት የተጠቃለሉ መረጃዎችን ከአባሪ " ቀ " ይመልከቱ::

4.3.6 <u>የተማሪዎች አስተያየት፣</u>

በመጠይቁ ላይ ከአምስቱ ተሳውጦች መጨረሻ ላይ ተማሪዎች ፍላ ጎታቸውንና ስሜታቸውን በተመለከተ አጠቃላይ አስተያየት እንዲሰጡ ሁለት ጥያቄዎች የቀረቡላቸው ሲሆን የተገኙትን መልሶች ከሠንጠረዥ አሥራ አንድና አሥራ ሁለት ይመልከቱ::

## ሠንጠረዥ አሥራ አንድ

ሀ. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የምትወዱ ከሆነ በምን ዓይነት ዘዴ መማር ትፈልጋ ላችሁ?

| ተ.ቁ. | የቀረቡት ዘዴዎች | ብዛት | መቶኛ |
|---|---|---|---|
| 1 | በተለያዩ ልቦለዶችና ልቦለድ ባልሆኑ መጽሐፍት ተደገፍ ቢቀርብ | 141 | 33.6 |
| 2 | ቅኔና ምሣሌያዊ አነጋገሮች ትኩረት ተሰጥቷቸው ቢቀርቡ | 60 | 14.3 |
| 3 | በቃልና በድራማ መልክ ቢቀርብ | 35 | 8.3 |
| 4 | በዘይቤያዊ በፈሊጣዊ አነጋገር ታጅቦ ቢቀርብ | 29 | 6.9 |
| 5 | አሁን ባለው መልኩ ይቀጥል | 20 | 4.8 |
| 6 | በመጽሔቶችና በጋዜጦች ተደገፍ ቢቀርብ | 19 | 4.5 |
| 7 | በቋንቋዊ ትምህርት በልዩ ዘዴ ቢቀርብ | 17 | 4 |
| 8 | በተለያዩ መረጃ መጽሐፍት ተደገፍ ቢቀርብ | 16 | 3.8 |
| 9 | ለማትሪክ ፈተና የሚጠቅሙ ነጥቦች ተለቅመው ቢቀርቡልን | 16 | 3.8 |
| 10 | በጥያቄና መልስ መልክ ቢቀርብ | 14 | 3.8 |
| 11 | በውይይትና በክርክር መልክ ቢቀርብ | 11 | 2.6 |
| 12 | በቂ ዕውቀት ባለው የአማራ ተወላጅ ቢቀርብ | 5 | 1.2 |
| 13 | የቃላት ትምህርት ቢጨመርበትና በመዝገበ ቃላት ቢታገዝ | 5 | 1.2 |
| 14 | በግጥምና በሥነ ቃሎች ታጅቦ ቢቀርብ | 2 | 0.5 |
| 15 | በሬዲዮና በቴሌቪዥን እየታገዘ ቢቀርብ | 2 | 0.5 |
| 16 | ድርሰቶችን እየፃፍን እንድንለማመድ ቢደረግ | 1 | 0.2 |
| 17 | በቂ የክፍልና የቤት ሥራዎች ቢሰጡን | 1 | 0.2 |

በሠንጠረዥ አሥራ አንድ ላይ በቀረበው መረጃ መሠረት በርካታ መላሾች ከጠቆሙት ዘዴዎች ዋና ዋናዎቹ፡-

- የአማርኛ ትምህርት በተለያዩ ልቦለድ ጽሑፎች እንዲደገፍ፣
- ቅኔያዊ፣ ምሣሌያዊ፣ ዘይቤያዊ ፈሊጣዊ አነጋገሮች እንዲቀርቡ ነው፣
- ትምህርቱ ተማሪዎችን መሳብ እንዲችል በቃልና በድራማ መልክ እንዲቀርብ፣
- መጽሔቶችና ጋዜጦች ለተማሪ የትምህርት መሣሪያ እንዲሆኑ፣
- የበቀሰው ትምህርት በማይከብድ ልዩ ዘዴ እንዲቀርብ፣
- ትምህርቱ በልዩ መርጃ መሣሪያ እንዲደገፍ የሚሉ ናቸው። እነዚህ

ደግሞ በመምህራን እጅ ያሉና በተማሪዎች ሁሉ ሊተገበሩ የሚችሉ ናቸው።

## ሠንጠረዥ አሥራ ሁለት

ለ. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የማትወዱ ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው?

| ተ.ቁ. | የቀረቡ ምክንያቶች | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|---|
| 1 | መጽሐፉ ሰፊ ጽሑፍና መልመጃ ስለሚበዛው | 21 | 5 |
| 2 | ከአንዱ መጽሐፍ ስለምንማርና ተጨማሪ ባለመኖሩ | 20 | 4.8 |
| 3 | የመምህሩ አቀራረብ ስለማይስበኝና ስለማይማርከኝ | 20 | 4.8 |
| 4 | የሰዋስው ትምህርት ስለሚከብደኝ | 7 | 1.7 |
| 5 | የትምህርት አቀራረብ ዘዴው አሰልቺ ስለሆነ | 6 | 1.4 |
| 6 | ብዙ አሰልቺ ቃላትን ስለያዘ | 4 | 1 |
| 7 | ትምህርቱ ስለሚከብድ | 3 | 0.7 |
| 8 | ቅኔ ስለማይገባኝ | 3 | 0.7 |
| 9 | ቋንቋዬ ስለሆነና ተራ ሆኖ ስለታየኝ | 2 | 0.5 |
| 10 | ትምህርቱና ፈተናው ስለማይገናኝ | 2 | 0.5 |
| 11 | ምሣሌያዊ አነጋገርና የቅኔ ትምህርት በጥሩዘዴ ስለማይቀርቡ | 1 | 0.2 |
| 12 | ምንም ስሜት ስለማይሰጠኝ | 1 | 0.2 |

በሠንጠረዥ አሥራ ሁለት መሠረት ከ1 _ 3 የተጠቀሱት የጥላቻ ምክንያቶች ፣ የመጽሐፉ የይዘት ምርጫ አለመስተካከልና ተጨማሪ ነገር አለመኖር እንዲሁም የመምህሩ የአቀራረብ ድክመት ናቸው:: እነዚህ ደግሞ በቀላሉ ሊስተካከሉ የሚችሉ ነገሮች በመሆናቸው ጥላቻው ሊቀንስ ወይም ሊወገድ ይችላል ማለት ነው::

## 4.4. የምላሾች ንፅፅር

በያንዳንዱ ተለውጦ ላይ የአራት መቶ ሃያ ተማሪዎች ምላሽ ከአነስተኛው እስከ ከፍተኛው ድረስ የተገኘው ነጥብ በትምህርት ቤት፣ በጾታ፣ በብሄረሰብና በትምህርት ዘርፋቸው አኳያ ተለያይቶ በሰንጠረዥ ቀርቧል:: /የትምህርት ቤቶችን ውጤት በተመለከተ፣ አባሪ "በ" ከ1–5፣ ከጾታ፣ ከብሄረሰብና ከትምህርት ዘርፍ አኳያ የተገኙ ውጤቶችን በተመለከተ፣ አባሪ "ተ" ከ1–5 ይመልከቱ/:: ሰንጠረዦችን በማየት በያንዳንዱ ነጥብ ላይ የመላሾችን ብዛት ማነፃፀር ይቻላል:: ንፅፅሩ ይበልጥ ሳይንሳዊና አሳማኝ እንዲሆን በተለያዩ ስታቲስቲካዊ ስሌቶች ተሰርቶ ቀርቧል::

በዚህ መሠረት በአምስቱም ተለውጦች ላይ:–

- በስድስቱ ት/ቤቶች ምላሾች መካከል፣
- በወንዶችና በሴቶች ምላሾች መካከል፣
- በአማሮችና በሌሎች ብሄረሰቦች ምላሾች መካከል፣
- በሳይንስና በአርት ተማሪዎች ምላሾች መካከል ስታትስቲካዊ ፋይዳ ያለው ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ በኮምፒውተር አማካይነት ስሌት ተሰርቶ እንዲነፃፀሩ ተደርጓል:: /የተሰራው በ"አናቫ"ስሌት ነው/

በሌላም በኩል ከሁለት እስከ አምስት ያሉት ተለዋጮች ከዋነኛው ተለዋጭ አንድ ጋር የውጤት ተመሳሳይነት እንዳላቸውና እንደሌላቸው ለማወቅ በ"ቲ–ቴስት"አማካይነት እንዲነፃፀሩ ተደርጓል::

በመጨረሻም የየተለዋጮቹ ምላሽ ተጣምር /correlation / ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ የ"ካይ ስኳር"ስሌት ተሰርቶ የቀረበ ሲሆን የሁሉንም ንፅፅራዊ ውጤቶች እንደሚከተለው እናቀርባለን::

### 4.4.1. የት/ቤቶች ምላሽ ንፅፅር

በተለዋጭ አንድ፣ ሁለት፣ አራትና አምስት ስሌት መሠረት የ"ኤፍ"ሬሺዮ እንደ ቅደም ተከተላቸው "1.21፣ 1.40፣ 0.48፣ 1.21"ሲሆን በ"0.05"የፋይዳ እርከን ላይ የተገኘው ነጥብ "3.84"ነው:: የሁሉም ተለውጦች የ"ኤፍ"ዋጋ ከ"አለፋው"ነጥብ /3.84/ ያነሰ በመሆኑ በተጠቀሱት ተለዋጮች ላይ በት/ቤቶች ምላሽ መካከል ስታትስቲካዊ ፋይዳ ያለው ልዩነት የለም:: ይህ ማለት የት/ቤቶችና የበታለበ ሁኔታ መስተናገድ በተማሪዎች አመለካከት ላይ ለውጥ አላመጣም::

በተለውጥ ቦስት ላይ በተሰራው ስሌት መሠረት የ"ኤፍ"ረሺዮ"14.62"ሲሆን በ"0.05"የፋይዳ አርከን ላይ የተገኘው ነጥብ "3.84"ነው:: የ"ኤፍ"ዋጋ ከ"አለፋው"ነጥብ /3.84/ የበለጠ በመሆኑ በተ/ቤቶች ምላሽ መካከል ስታተስቲካዊ ፋይዳ ያለው ልዩነት አለ ማለት ነው:: ተለዋጭ ቦስት መምህራንን የሚመለከት ሲሆን የመምህራንን አመለካከት፣ ችሎታና ጠባይ በተመለከተ በተ/ቤቶች ምላሽ መካከል ልዩነት መኖሩ የመምህራኑ ችሎታ፣ ጠባይና አመለካከት ከተ/ቤት ተ/ቤት የተለያዩ መሆኑን ያመለክታል:: ይህ ደግሞ ሊሆን የሚችል ጉዳይ ነው:: ዝርዝር ገን መምህራንን በተመለከተ ከሁሉም ተ/ቤቶች የተገኘው መረጃ አያገናዊ ነው::

4.4.2. <u>የወንዶችና የሴቶች ምላሽ ንፅፅር</u>

ከተለዋጭ አንድ እስከ አምስት ያሉት ሁሉ ስታቲስቲካዊ ስሌታቸው እንደሚያሳየው የ"ኤፍ"ረሺዮ እንደቅደም ተከተላቸው "2.25፣ 1.66፣ 2.05፣ 3.03፣ 0.81"ሲሆን በ"0.05"የፋይዳ አርከን ላይ የተገኘው ነጥብ "3.84"ነው :: የሁሉም የ"ኤፍ"ዋጋ ከ"አለፋው"ነጥብ /3.84/ ያነሰ በመሆኑ በወንዶችና በሴቶች ምላሾች መካከል ስታተስቲካዊ ፋይዳ ያለው ልዩነት የለም:: ስለዚህ በአምስቱም ተለዋጮች ላይ ጾታን ምክንያት ያደረገ ልዩነት እንደሌለ ለማረጋገጥ ተችሏል ::

4.4.3. <u>የአማርኛና የሌሎች ብሄረሰቦች ምላሽ ንፅፅር</u>

በተለዋጭ አንድና ሁለት ስሌት መሠረት የ"ኤፍ"ረሺዮ እንደቅደም ተከተላቸው "12.29፣ 10.33"ሲሆን በ"0.05"የፋይዳ አርከን ላይ የተገኘው ነጥብ "3.84"ነው:: በሁለቱም ተለዋጮች የ"ኤፍ"ዋጋ ከ"አለፋው"ነጥብ /3.84/ የበለጠ በመሆኑ በተለዋጭ አንድና ሁለት ላይ ከአማርኛና በሌሎች ብሄረሰቦች ምላሾች መካከል ስታቲስቲካዊ ፋይዳ ያለው ልዩነት አለ ማለት ነው::

በሌላ በኩል በተለዋጭ ቦስት፣ አራትና አምስት ስሌት መሠረት የ"ኤፍ" ረሺዮ እንደቅደም ተከተላቸው "0.20፣ 1.08፣ 0.0"ሲሆን በ"0.05"የፋይዳ አርከን ላይ ከሚታየው "3.84"ያነሱ በመሆናቸው በሶስቱም ተለዋጮች በአማርኛና በሌሎች ብሄረሰቦች ምላሾች መካከል ስታቲስቲካዊ ፋይዳ ያለው ልዩነት የለም ::

የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን፣ መማሪያ መጻሕፍትን፣ ተ/ቤቶችን፣ መማሪያ

ባለመሆን መካከል የምላሽ ልዩነት የለም፡፡ ነገር ግን የተማሪዎችን የግል አመለካከት፣ የወላጆችንና የኅብረተሰቡን እንዲሁም የእኩዮቻቸውን አመለካከት በተመለከተ የምላሽ ልዩነት አለ፡፡ በኅረሰባቸው እስከተለያዩ ድረስ የምላሻቸው መለያየት ሊኖር ይችላል፡፡ ታዲያ በሁለቱም ተላውጦዎች ላይ የነጥብ አሰጣጥ ልዩነት ይኑር እንጂ የሁሉም ምላሽ አዎንታዊ ነው፡፡

### 4.4.4. የሳይንስና የአርት ተማሪዎች ምላሽ ንፅፅር

ከተላውጥ አንድ እስከ አራት የ"ኤፍ"ረሺዮ የእንደቀደም ተከተላቸው "0.93፣ 0.96፣ 0.03፣ 0.68" ሲሆን በ"0.05" የፋይዳ እርከን ላይ የተገኘው ነጥብ "3.84" ነው፡፡ የአራቱም ተላውጦዎች የ"ኤፍ"ዋጋ ከ"አለፋው"/3.84/ ያነሰ በመሆኑ በሳይንስና በአርት ተማሪዎች ምላሽ መካከል ስታቲስቲካዊ ፋይዳ ያለው ልዩነት የለም፡፡

ተላውጥ አምስትን በተመለከተ በተሰራው ስሌት መሠረት የ"ኤፍ"ረሺዮ "5.88" ነው፡፡ በ"0.05" የፋይዳ እርከን ላይ የተገኘው ነጥብ "3.84" ሲሆን የ"ኤፍ"ዋጋ ከ"አለፋው" ነጥብ /3.84/ የበለጠ ነው፡፡ ስለዚህ በተላውጥ አምስት ላይ በሳይንስና በአርት ተማሪዎች መካከል ስታቲስቲካዊ ፋይዳ ያለው ልዩነት አለ ማለት ነው፡፡

በተላውጥ አምስት ውስጥ ከተጠቃለሉት አንቀፆች የመማሪያ ክፍሎች ሁኔታ ሲሆን በአንድ ክፍል የታጎሩት የአርት ተማሪዎች ከሳይንስ ተማሪዎች በቁጥር ይበልጣሉ ፡፡ ለምሳሌ በአፄ ናኦድ፣ በኢትዮጵያ ትቅደም፣ በወንድራድ ት/ቤቶች ከፍተኛውን ቁጥር ይዘው በአንድ ክፍል የተገኙት የአርት ተማሪዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ተማሪዎች ከሳይንስ ተማሪዎች ይበልጥ ክፍል ጠባቡብና ወንበር እጥረት ይስተዋላሉ፡፡ ስለዚህ በተላውጥ አምስት ላይ የሳይንስና የአርት ተማሪዎች ምላሽ መለያየት ሊሆን የሚችል ነው፡፡

### 4.4.5. የተላውጥ አንድና የሌሎች ተላውጦዎች ንፅፅር

በተላውጥ አንድና ሁለት እንዲሁም አንድና ሶስት መካከል የተሰራው ስሌት እንደሚያመለክተው የ"ቲ"ዋጋ እንደቀደም ተከተላቸው "1.49" እና "1.45" ነው፡፡ በ"0.05" የፋይዳ እርከን ላይ የተገኘው ነጥብ ደግሞ "1.96" ሲሆን የሁለቱም የ"ቲ"ዋጋ ከ"አለፋው" ነጥብ /1.96/ ያነስ ነው፡፡ ስለዚህ በተላውጥ አንድና

ስታቲስቲካዊ ፋይዳ ያለው ልዩነት

በተለዋጭ አንደኛ አራት እንዲሁም አንደኛ አምስት መካከል የተሰራው ስሌት እንደሚያሳየው የ"ቲ"ዋጋ እንደቅደም ተከተላቸው "13.36"እና "19.5"ነው :: በ"0.05"የፋይዳ እርከት ላይ የተገኘው ነጥብ "1.96"ሲሆን የሁለቱም የ"ቲ" ዋጋ ከ"እልፋው"/1.96/ የበለጠ ነው:: ስለዚህ በተለዋጭ አንደኛ አራት እንዲሁም አንደኛ አምስት ምላሾች መካከል ስታቲስቲካዊ ፋይዳ ያለው ልዩነት አለ ማለት ነው::

### 4.4.6. የተለዋጮቹ ተዛምር

የተዛምሯዊ ስሌት ውጤት ወደ አሉታዊ አንድ /—1/ እየተጠጋ ከሄደ ተዛምሮው አሉታዊ መሆኑን ሲያመለክት ወደ አዎንታዊ አንድ /1/ እየቀረበ ከሄደ ተዛምሮው አዎንታዊ መሆኑን ያሳያል:: በዚህ መሠረት ከአምስቱም ተለዋጮች የተገኙት ምላሾች እርስ በርስ ሲነፃፀሩ ሁሉም አዎንታዊ ተዛምሮነት ያላቸው ሲሆን በተለይ በተለዋጭ አንደኛ ሁለት ማለትም በተግባሩ ግላዊ አመለካከትና በወላጆች በኅብረተሰቡና በእኩዮች ምላሾች መካከል ከሁሉም የተሻለ ተዛምሮነት ታይቷል:: የስሌቱም ውጤት "0.55"ሲሆን ከአሉታዊ አንድ ወደ አዎንታዊ አንድ የቀረበ ነው :: ለዝርዝሩ የሚከተለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ::

ሠንጠረዥ አሥራ ሰባት

የተለዋጮቹ የርስ በርስ ተዛማጅነት

| ተለዋጮች | ተለዋጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 1 | 1.00 | 0.55 | 0.26 | 0.35 | 0.12 |
| 2 | 0.55 | 1.00 | 0.21 | 0.32 | 0.11 |
| 3 | 0.26 | 0.21 | 1.00 | 0.30 | 0.31 |
| 4 | 0.35 | 0.32 | 0.30 | 1.00 | 0.40 |
| 5 | 0.12 | 0.11 | 0.31 | 0.40 | 1.00 |

### 4.5. ቃለመጠይቃዊ መልሶች

አተኙው በስድስቱም ት/ቤቶች ከሚገኙት አስራ ሁለት የአሥራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን ጋር ቃለመጠይቃዊ ውይይት አድርጓል:: ቃለመጠይቁ ስድስት ጥያቄዎችን ያቀፈ ሲሆን ጥያቄዎቹና መልሶቹ የሚከተሉት ናቸው::

... ትምህርት ምን ዓይነት አመለካከት አላቸው?

ለዚህ ቃለመጠይቅ ሶስት መልሶች ተመዝግበዋል::

ሀ. በአማርኛ ቋንቋ ላይ አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ጥቂት ተማሪዎች ቢኖሩም አብዛኛዎቹ ጥሩ አመለካከት አላቸው /ሰባት መላሾች/58.3%/ ይህን መልስ ሰጥተዋል/

ለ. በአሁኑ ጊዜ ብዙ ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጠው ትምህርት አለገባ እያላቸው "ገብተን የምንግባረው አማርኛ ብቻ ነው"እያሉ በጥሩ ስሜት እየተማሩ ነው:: /ሶስት መላሾች /25%/ ይህን መልሰዋል/

ሐ. ተማሪዎች በሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ላይ ከሚያሳዩት ባሕርይ የተለየ በአማርኛ ቋንቋ ላይ የሚያሳዩት ነገር የለም:: /ሁለት መላሾች /16.7%/

2. ተማሪዎች የአማርኛን ትምህርት እንዴት ይቀበላሉ?

ለዚህ ቃለመጠይቅ ሁለት መልሶች ተሰጥተዋል:: አብዛኛዎቹ መላሾች ሁለቱ ንም ሃሳቦች ሲያቀርቡ ጥቂቶቹ አንዱን ብቻ አቀርበዋል::

ሀ. ለተማሪዎቹ የአማርኛ ትምህርት አቀባበል ወሳኙ የመምህሩ አቀራረብ ነው:: መምህሩ በመጽሐፉ ላይ ብቻ ሳይወሰን የተማሪዎችን ፍላጎትና ስሜት እየተ ቆጣጠረ ሳይጨነቁና ሳይጠበቡ በሳቅና በፈገግታ እንዲማሩ የሚያደርግ ከሆነ ክፍለጊዜውን በጉጉት የሚጠብቁትና የሚወዱት ይሆናል:: ተማሪዎች ጥሩ መምህር ካገኙ የአማርኛን ትምህርት በደንብ ይቀበላሉ:: /አሥራ ሁለቱም መላሾች /100%/ የሰነዘሩት ሃሳብ/

ለ. አብዛኛዎቹ በጥሩ ሁኔታ የሚቀበሉ ሲሆን ጥቂቶቹ ብቻ "እናውቃለን":: በሚል ስሜት ትምህርቱን የሚንቁ ይመስላሉ:: ጥቂቶቹ ደግሞ የብሄረሰ ባቸውና የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ካለመሆኑ የተነሳ እንዲሁ የሚጠሉት ይመስላሉ:: ያም ሆነ ይህ የሚንቁትና የሚጠሉት ተማሪዎች ከሚወዱት ጋር ሲነፃፀሩ እምንት በመሆናቸው የጎላ ችግር ሆኖ አይቀርብም :: እነሱም ሲሆኑ በመምህራን አቀራረብ ሊስተካከሉ ይችላሉ:: /ስምንት መላሾች /66.7%/

3. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ትልቁ ችግር ምንድነው? በዚህ ቃለመጠይቅ ላይ ሶስት መልሶች ቀርበዋል::

ሀ. የተማሪዎች ከአንደኛ ደረጃ ጥሩ መሠረት ይዞ አለመምጣትና ከደረጃ በታች ሆኖ መገኘት በመምህራን አቀራረብ ላይ ትልቅ ችግር ፈጥሯል:: አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ደረጃቸውን በመጠነ መልኩ ማንበብና መጻፍ አይችሉም:: /ዘጠኝ መላሾች /75%/

ለ. ጥቂቶችም ቢሆኑ በቋንቋው ላይ ነቀፌታና ጥላቻ ያላቸው ተማሪዎች እንዲሁም የት/ቤት መሪዎች በግልጽና በስውር ከሚሰነዝሩት ዘለፋ የተነሳ አንዳንድ መምህራን በዐኔ የመሥራት ቀረሳቸው ወድቋል:: /ስድስት መላሾች /50%/

ሐ. የማትሪክ የአማርኛ ጥያቄዎችና የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ትምህርት አለመጣጣማቸው በመጠኑም ቢሆን ተማሪዎች ለክፍሉ ትምህርት ያላቸውን ትኩረት እንዲቀንሱ አስተዋጽኦ አድርጓል:: /አምስት መላሾች /41.7%/

4. አሁን በሥራ ላይ ስላለው የዐሥራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ምን አስተያየት አለዎት? ለዚህ ቃለመጠይቅ አሥራ ሁለቱም መላሾች /100%/ "የአሁኑ መጽሐፍ ከበፊቱ የተሻለ ቢሆንም ብዙ ጉድለቶች አሉት" ካሉ በኋላ የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል::

ሀ. መጽሐፉ በምንባቦች ምርጫም ሆነ በአቀራረቡ ተማሪዎችን የመሳብ አቅም የለውም:: /ዘጠኝ መላሾች /75%/

ለ. በርካታ ርዕሶች በዘጠነኛና በአሥረኛ ክፍሎች የቀረቡ ሆነው በአሥራ አንደኛም ስለሚደገሙ አሰልቺ ይሆናሉ:: ለምሳሌ ምሳሌያዊ አነጋገር፣ ዘይቤ፣ ቅኔ፣ የስም ገላጭ፣ የግሥ ገላጭ፣ የግጥም ዓይነቶችና ስያሜያቸው ወዘተ. ተደጋጋሚዎች ናቸው:: /ስድስት መላሾች /50%/

ሐ. የይዘቶች ተከታታይነት የተዛባ ነው:: /አምስት መላሾች /41.7%/

መ. ከተማሪዎች ደረጃ ላይ የከበዱ ነጥቦችም አሉ /አራት መላሾች /33.3̂%/

5. ወደፊት የሚዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት በማን እንዴት ቢዘጋጁ ይሻላል?

5.1. አዘጋጆችን በተመለከተ

ሀ. የቋንቋው መምህራንና የሥርዓተ-ትምህርት ባለሙያዎች ባንድነት ሆነው ቢያዘጋጁ /ሰባት መላሾች /58.3%/

ለ. በማስተማር ሙያ ላይ ያሉና የተማሪዎችን ፍላጎት የሚያውቁት መምህራን ስለሆኑ እነሱ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል /አምስት መላሾች /41.7%/

5.2. ዝግጅቱን በተመለከተ

ሀ. ከዘጠነኛ እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል በየክፍሉ የሚቀርቡት ይዘቶች የተለያዩና ተከታታይነት ያላቸው ቢሆኑ /ሰባት መላሾች /58.3%/

ለ. ሁሉንም የቋንቋ ዘርፎች አመጣጥነው የያዙ ቢሆኑ /አምስት መላሾች /41.7%/

ሐ. የምንባቦች ምርጫ ወደ ልቦለዶች ያዘነበለና ተማሪዎችን መሳብ የሚችል ቢሆን /አራት መላሾች /33.3%/

መ. ተቀርጠው የሚወሰዱ ምንባቦች ምንጫቸው በተገቢው መልክ ቢጠቀስ:: ምክንያቱም አንዳንድ ቀንደኛ ሃሳቦችን መረዳት ስለሚያስቸግር መምህሩ ሙሉውን ፅሁፍ አንብቦ መረዳትና መግለጽ እንዲችል ነው:: /ሁለት መላሾች /16.7%/

ሠ. የመምህር መምሪያ ያለውና በክፍለ ጊዜ የተከፋፈለ ቢሆን /አንድ መላሽ /8.3%/

6. ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንዲማረኩና በደስታ እንዲማሩ ምን መደረግ አለበት? ለዚሁ ያለመጠይቁ በደብተ ሃሳቦች ቀርበዋል::

ሀ. ተማሪዎች መማር የሚፈልጉትን ይዘቶች በፍላጎታቸው መሠረት መምረጥና አቀልሉ ማቀረብ /ዘጠኝ መላሾች /75%/

ለ. መምህራን ዝግጅታቸውን ማሳመርና የአቀራረብ ስልታቸው አሰልቺ እንዳይሆን መቀያየር /ሰባት መላሾች /58.3%/

ሐ. ልቦለድ ጽሁፎችን ለተለያዩ የአማርኛ ትምህርት ዘርፎች የማስተማሪያ ጽሁፍ አድርጎ መጠቀም /አምስት መላሾች /41.7%/

መ. በክፍሉ መጽሐፍ ላይ ብቻ አለመወሰንና ወቅታዊ ነገሮችን ከጋዜጦችና ከመጽሔቶች ፈልጎ ማቀረብ/አምስት መላሾች /41.7%/

ሠ. የተማሪዎችን ሞራል የሚነኩ ቃላትን አለመናገርና አስፀያፊ ተግባራትን አለመፈፀም /ሦስት ወላጆች /25%/

ረ. ስለአማርኛ ቋንቋ የተዛባ አመለካከት ያላቸውን ተማሪዎች መለወጥ /ሁለት ወላጆች /16.7%/

4.6. ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች ንፅፅር

1. በ"1.2" ላይ ለተማሪዎች የቀረበው ጥያቄ "ግዴ ሆኖብኝ እንጂ አማርኛን መማር አልፈልገም" የሚል ሲሆን 82.3% ተማሪዎች ተቃውመውታል:: ስለዚህ "ተማሪዎች አማርኛን መማር ይፈልጋሉ" ብለን ነበር:: ከመምህራን የተገኘው መረጃም "ተማሪዎች ጥሩ መምህር ካገኙ የአማርኛን ትምህርት በደንብ ይቀበላሉ" የሚል ስለሆነ መረጃዎች ተመሳሳይ ናቸው::

2. በ"1.4" ላይ ለተማሪዎች የቀረበው ጥያቄ "የአማርኛ ትምህርት ስለሚቀለኝ እንቀዋለሁ" የሚል ሲሆን የተገኘው መልስ 80.5% ተቃውሞ ነው:: ስለዚህ "አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አማርኛን አይንቁም" ብለን ነበር:: ከመምህራን የተገኘው መረጃም "ጥቂቶች ብቻ እናውቃለን" በሚል ስሜት የሚንቁ ይምሰሉ እንጂ አብዛኛዎቹ በጥሩ ሁኔታ ይቀበላሉ" ስለሚል መረጃዎች ተመሳሳይ ናቸው::

3. በ"1.6" ላይ ለተማሪዎች የቀረበው ጥያቄ "አማርኛ ቋንቋ ያስጠላኛል" የሚል ሲሆን 91% ተቃውሞ ገጥሞታል:: በዚህ መሠረት አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አማርኛን እንደማይጠሉ አረጋግጠዋል:: ይኸው ጥያቄ በ"2.10" ላይ "ጓደኞቼ አማርኛ ቋንቋን ይጠላሉ" በሚል መልክ የቀረበ ሲሆን 77.3% ተቃውሞ ገጥሞታል:: ከዚህም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አማርኛን እንደማይጠሉ አረጋግ ጠናል:: ከመምህራን የተገኘው መረጃም "ከጥቂቶች በስተቀር አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በአማርኛ ላይ ጥሩ አመለካከት አላቸው" ስለሚል መረጃዎች ተደጋጋፊ ናቸው::

4. በ"1.13" ላይ ተማሪዎች ደስ ብሏቸው የሚማሩትን የአማርኛ ትምህርት ርዕሶች እንዲመርጡ በተጠየቁት መሠረት "ልቦለድን ማንበብ" የሚለው አንደኛ ሆኖ የተመረጠ ሲሆን ከመምህራን የተገኘው መረጃም በመጻሕፍት ዝግጅት ወቅት የምንባቦች ምርጫ ወደ ልቦለድ ጽሁፎች እንዲያዘነብልና ልቦለድ ጽሁፎችን ለተለያዩ የአማርኛ ትምህርት ዘርፎች መጠቀም ተማሪዎችን እንደሚያርክ

ይጠቅማል:: ስለዚህ የተማሪዎች ምርጫና የመምህራን ጥቆማ ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል::

4. መማሪያ መጽሐፉን አስመልክቶ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመን መጽሐፉ የቋንቋ ዘርፎችን አካቶ ያልያዘ፣ ያለአስተማሪ ተማሪ መምራት የማይችል፣ የያላት ዝርዝርና ትርጓሜዎችን የማያሳይ ብቃት የጎደለው መሆኑን ነው:: ከመምህራን የተገኘው መረጃ ደግሞ በጥቅሉ መጽሐፉ ከበረቱ የተሻለ ቢሆንም ብዙ ድክመቶች እንዳሉበት ነው:: ለምሳሌ ምንባቦች ተማሪዎችን መሳብ የማይችሉ፣ ቅደም ተከተላቸው ያልተስተካከለና ደረጃን ያልጠበቁ መሆናቸው በመምህራን ተገልጿል፤ ስለዚህ መረጃዎቹ ተመሳሳይ ናቸው::

5. "አማርኛን እንዴት ብትማሩ ትፈልጋላችሁ?" ከሚሉ በማጠያሳይ ጥያቄ "ሀ" ላይ ተማሪዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ ከቀረቡት በርካታ ሃሳቦች ዋነኞቹ የሚከተሉት ናቸው::

   • ትምህርቱ በልቦለድ ጽሑፎች፣ እንዲሁም በመጽሔቶችና በጋዜጦች ተደግፎ ቢቀርብ፣ በቀልድና በድራማ መልክ ተማሪን እንዲስብ ተደርጎ ቢሰጥ

"መምህራንም የአማርኛ ትምህርት እንዴት ቢቀርብ ተማሪዎች ተደስተው ይማራሉ?" ከሚሉ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ ሲመልሱ:-

   • ልቦለድ ጽሁፎችን ለተለያዩ የአማርኛ ትምህርት ዘርፎች የማስተማሪያ ፅሑፍ አድርጎ መጠቀም፣ ወቅታዊ ነገሮችን ከጋዜጦችና ከመጽሔቶች ለያቅም ማቅረብ እንዲሁም መምህራን አቀራረባቸው አሰልቺ እንዳይሆን መቀያየር ተማሪዎችን እንደሚያስደስት ጠቅሰዋል::

እነዚህ ሃሳቦች ተመሳሳይ ሲሆኑ በሌላም በኩል አማርኛን የሚጠሉ ጥቂት ተማሪዎች ለጥላቻቸው ምክንያት አድርገው የጠቀሷቸው ነጥቦች:-

   • መጽሐፉ ልቦለድ ያልሆኑ ፅሁፎችና መልመጃ ስለሚበዛው
   • ከአንድ መጽሐፍ ብቻ ስለምንማርና ተጨማሪ ስለሌለው
   • የመምህሩ አቀራረብ ስለማይስበንና ስለማይማርከን የሚሉ ናቸው ::

ስለዚህ በሁሉም አቅጣጫ የተጠቀሱት ነጥቦች ተደጋጋፊ ሲሆኑ ተማሪዎች መማር የሚፈልጉት፣ ትምህርቱ በልቦለድ ተደግፎ ሲቀርብ፣ ወቅታዊ ነገሮች ከጋዜጦችና ከመጽሔቶች

## 4.7. የምልከታ ሪፖርት

አጥኚው የስድስቱንም ት/ቤቶች ገቢና ቤተመጻሕፍት ዝርዝር የጎበኘ ሲሆን የአማርኛ ክፍለ ጊዜ ትምህርታዊ ሂደቶችን በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በመገኘት ተመለከቷል::

### 4.7.1. የት/ቤቶች ገቢና የቤተመጻሕፍት ሁኔታ

የጥናቱ ናሙና ት/ቤቶች አብዛኛዎቹ ገቢያቸው የተሟጠጠ ነው:: በተለይ ኢትዮጵያ ትቅደምና ጥቁር አንበሳ በጣም የተሟጠጡ ሲሆኑ ከፍተኛ አራትና ኢስ.ኦ.ኢስ. ት/ቤቶችም ከሁለቱ የተሻሉ ይሁን እንጂ ጠባቦች ናቸው በጣም ሰፊ ገቢ ያላቸው ት/ቤቶች ወንድራድና አያቴ ብሩ ናቸው::

ናሙና ት/ቤቶች ሁሉ ቤተመጻሕፍት አላቸው:: ይሁን እንጂ ት/ቤቶቹ ወቅታዊ ጋዜጦችንና መጽሄቶችን እንዲሁም ለአማርኛ ድጋፍ ትምህርት የሚያግዙ አዳዲስ መጻሕፍት እየተከታተሉ አይገዙም:: እንደዚያም ሆኖ ቤተመጻሕፍቱ የሚናቅ አይደሉም::

### 4.7.2. መማሪያ ክፍሎችና የትምህርት ሂደት

የመማሪያ ክፍሎችን ሁኔታ ስንመለከት አብዛኛዎቹ ከሚገባው በላይ በተማሪ ተጨናንቀው ይታያሉ:: ለምሳሌ አጥኚው ከጎበኛቸው ክፍሎች በአንዱ ክፍል ያገኛቸው ተማሪዎች አነስተኛው ቁጥር ስልሳ አራት ሲሆን ከፍተኛው አንድ መቶ አራት ነው:: በርካታዎቹ ክፍሎች ከሰባ እስከ መቶ ተማሪዎችን አጭቀው ይዘዋል:: ከተማሪዎቹ ብዛት የተነሳ መቀመጫ በማነሱ ሶስት ሆነው ሁለት ወንበሮችን በማገጣጠም የተቀመጡበት ክፍሎችም አሉ::

አጥኚው ስድስት የሳይንስና ስድስት የአርት ክፍሎችን በአማርኛ ድጋፍ ትምህርት ሂደት ላይ እንዳሉ የተመለከተ ሲሆን በኢትዮጵያ ትቅደም ት/ቤት ከታየት ሁለት ክፍሎች በስተቀር ሌሎቹ ክፍሎች እምብዛም አልተጨናነቁም:: ሁሉም ደህና ጥቁር ሰሌዳ አላቸው::

በተጎበኙት ሁሉም ክፍሎች ጥሩ የትምህርት ሂደት ይከናወን ነበር:: ተማሪዎቹ በፀጥታ ይማራሉ፤ በቂ ተሳትፎም ያደርጋሉ:: በርግጥ ከተመደበው የክፍሉ መጽሐፍ በስተቀር አንድም መምህር ሌላ መርጃ መሣሪያ ሲጠቀም አልታየም::

## 4.8. የምልከታ ውጤትና የተማሪዎች ምላሽ ንፅፅር

የአጥኚው የምልከታ ውጤት ሊታይ ከሚችለው የተማሪዎች ምላሽ ጋር ሲነፃፀር

../

ውሎ በውሎ ተመሳሳይ ነው፡፡ ለምሳሌ የመቀመጫ ማነስና መጨናነቅ፣ የተማሪዎች በፀሃይ መማር፣ የሰሌዳ አለመበላሸት፣ የመምህራን ለቁ መርጃ መሣሪያ አለመጠቀም፣ የት/ቤቶች ወቅታዊ ጋዜጦችና መጽሄቶችን አለመገዛት እነዚህን ሁሉ በተመለከተ ከተማሪዎች የተገኙት መረጃዎችና አጥኚው በምልከታ ያገኛቸው መረጃዎች አንድ ዓይነት ናቸው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ ፣ ግኝትና አስተያየት

### 5.1 ማጠቃለያ

በመግቢያው ክፍል እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ ሲሆን በዚህ አቢይ ዓላማ ሥር አምስት ዝርዝር ዓላማዎች ይገኛሉ:: እነዚህ ዝርዝር ዓላማዎች በጥያቄ መልክ ሲቀመጡ እንደሚከተለው ይሆናሉ::

1. በአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ዘንዱ አማርኛ ቋንቋና የቋንቋው ትምህርት ተቀባይነቱ ምን ያህል ነው?

2. ወላጆች ፣ ህብረተሰቡና የተማሪው እኩዮች ስለ አማርኛና ስለ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ምን ዓይነት አመለካከት አላቸው?

3. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በችሎታቸው ፣ በትምህርት አቀራረባቸውና በጠባያቸው ምን ያህል ተቀባይነት አላቸው?

4. የአሥራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ በተማሪዎች ዘንዱ ተቀባይነቱ ምን ያህል ነው?

5. ት/ቤቶችና መማሪያ ክፍሎች እንዲሁም ደጋፊ ሰጪ ነገሮችና የማስተማር ዘዴዎች ምን ያህል የተሟሉ ሆነው የተማሪውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎት ይቀሰቅሳሉ?

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ አራት አቢይ ተግባራት ተከናውነዋል::

1. በቋንቋና በቋንቋ ትምህርት አመለካከት ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች ተከልሰዋል:: በዚህ መሠረት ተማሪው በቋንቋና በቋንቋ ትምህርት ላይ ሊኖረው የሚገባውን አመለካከት የሚወስኑ በርካታ ነገሮች መኖራቸውንና በዋነኛነት ወላጆች ፣ ህብረተሰቡና እኩዮች እንዲሁም መምህራን ፣ መማሪያ መጻሕፍት፣ የትምህርት ቦታዎች ፣ ደጋፊ ሰጪ ነገሮችና የማስተማር ዘዴዎች እንደሚጠቀሱ ተብራርቷል::

2. አምስት ተሳጭጠያችንና ስልባ አራት ጥያቄዎችን የያዘ መጠይቅ ለአራት መቶ ሃያ ተማሪዎች ተበትኖ የተሰበሰበው መረጃ ውጤትና ማብራሪያው በምዕራፍ አራት ቀርቧል ፤ በታቢቲካዊ በሌትና ንፅፅርም ታይቷል:

3. በቃለ መጠይቅ አማካይነት ተጨማሪ መረጃዎች ከመምህራን ተሰብስበዋል:: መረጃዎቹም እንደአስፈላጊነታቸው ከተማሪዎች ምላሽ ጋር እየተነፃፀሩ ቀርበዋል::

4. ከተማሪዎች የተገኙ አንዳንድ መረጃዎችን በዓይን አይቶ ለማረጋገጥ በት/ቤቶች ገቢና ጠመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ትምህርት እየተከናወነ ምልከታ ተደርጓል:: በምልከታ የተገኙ መረጃዎችም ከተማሪዎች ምላሽ ጋር እየተነፃፀሩ ተብራርተዋል::

ከነዚህ ሁሉ ተግባራት በኋላ የተጠቀሱት ጥያቄዎች ያገኙት መልሶች የሚከተሉት ናቸው::

1. በአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ዘንድ አማርኛ ቋንቋና የቋንቋው ትምህርት ተቀባይነቱ በጣም ጥሩ ነው:: ጥቂት የሚጠሉና የሚንቁ ተማሪዎች መኖራቸው ቢረጋገጥም አብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋንና የቋንቋውን ትምህርት ይወዳሉ::

2. ወላጆች ፣ ህብረተሰቡና የተማሪው አኩዮች በአማርኛ ቋንቋ ላይ አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ቢሆን ተማሪዎችም ቋንቋውን እንዲማሩ ይደግፋሉ::

በተዛማጅ ጽሑፍ ክለሳ እንደተመለከተነው ወላጆች ፣ ህብረተሰቡና አኩዮች ቋንቋውን የሚጠሉና የተማሪዎችን መማር የማይደግፉ ቢሆን ኖሮ ተማሪ ዎቹም ባልወደዱት ነበር:: አሁን ግን ተመሳሳይ ሐሳብ በመገኘቱ ጽሑፉዊ መረጃዎችና አጥኚው የሰበሰባቸው መረጃዎች ተጣጥመዋል ማለት ነው::

3. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በችሎታቸው ፣ በትምህርት አቀራረባቸውና በጠባያቸው በጥሩ ሁኔታ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው::

በተዘጋጀው ጽሑፍ ክለሳ የቋንቋ መምህር ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደሆነና ተማሪዎች መምህሩን ከጠሉ የቋንቋውንም ትምህርት እንደሚጠሉ ተረድተናል:: በዚህ ጥናት ግን መምህራኑም ሆኑ የቋንቋው ትምህርት አልተጠሉም::

4. የአሥራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ተቀባይነቱ መካከለኛ ነው:: መጽሐፉ ብዙ ድክመቶች እንዳሉበት ከመምህራን የተጠቆመ ቢሆን ካለፈው መጽሐፍ የተሻለ መሆኑ አልተዘነጋም:: ከተማሪዎች የተገኘው መረጃም እንደሚያሳየው የተወሰኑ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉበት::

5. ት/ቤቶችና መማሪያ ክፍሎች ፣ እንዲሁም ድጋፍ ሰጪ ነገሮችና የማስተማር ዘዴዎች ፣ ተማሪውን ወደ ቋንቋው ትምህርት ለመሳብ እንዲችሉ መሟላት ከሚገባቸው ነገሮች፣ካገሪቱ አቅም ማነስ የተነሣ ያልተሟሉ ቢኖሩም መሠረታዊ የሆኑ ነገሮች ደግሞ አልታጡም:: በተማሪ ብዛት ይጨናነቁ እንጂ ክፍሎች ፣ ወንበሮች ፣ ሠሌዳዎች ፣ ቤተመጽሐፍት ወዘተ. አሉ:: ይህ በተማሪዎች ምላሽና በአጥኚው ምልከታ የተረጋገጠ ቢሆን ችግሩ ጎልቶ ተማሪዎች ትምህርቱን እንዲጠሉት አላደረገም::

እነዚህ አምስት ተናጠላዊ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው አቢይ የጥናቱን አላማ ከግብ ያደርሳሉ:: በዚህ መሠረት ፣ ውጤቱ ቢጠቃለል ፣ አብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አዎንታዊ አመለካከት አላቸው::

5.2 ግኝት

ቀጥለን ከተማሪዎችና ከመምህራን ምላሾች እንዲሁም ከአጥኚው ምልከታ የተጠናቀሩትን ግኝቶች ጠቅለል አድርገን እናቀርባለን::

1. አብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን አይንቁም ፣ አይጠሉም:: ይልቀስ ይወዳሉ ፣ መማር ይፈልጋሉ::

2. አብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በበፋት ይጠቀማሉ ፣ ቢያነቡና ቢያደምጡም ከሌሎች ቋንቋዎች ይልቅ በአማርኛ ቢሆን ይገባቸዋል::

3. አብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች አማርኛ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ አንዲሆን አይፈልጉም::

4. አብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች አማርኛ የኢትዮጵያ ኦፊሴላዊ ቋንቋ አንዲሆን ይፈልጋሉ::

5. የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ልብለድን ማደመጥ ፣ ቀኔና ምሳሌያዊ አነጋገሮችን መማር እንዲሁም ውይይት፣ ክርክርና ጭውውት ይበልጥ ያስደስታቸዋል::

6. አብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ወላጆቻቸው አማርኛን ይወዳሉ ፣ ልጆቻቸውም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸውን ዝንባሌ ይደግፋሉ:: በተጨማሪም ልጆቻቸው አማርኛን በቤት ውስጥ ቢናገሩበትና ከፍተኛ ትምህርት ቢገፉበት አይቃወሙም::

7. የአዲስ አበባ ህብረተሰብ የአማርኛ ቋንቋን ይወዳል ፣ ተማሪዎችም አንዲማሩት ይደግፋል::

8. ብዙዎቹ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የአማርኛ መምህራን ጥሩ ጠባይና በቂ እውቀት ያላቸው ቢሆን ቋንቋውን በደንብ ያስተምራሉ:: ተማሪዎቻቸውም አማርኛን አንዲወዱና በፍላ
ጎታቸው መሠረት አንዲማሩ ይመክራሉ ፣ ያበረታታሉ::

9. የአሥራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ለትምህርት አንዲ
መች ሆኖ ያልተከፋፈለና ሥዕላዊ መግለጫዎች የሌሉት ቢሆንም

በዚያም ተማሪዎች ምንባቡ ምንም ሆነ ማንበቡን ፣ እንዲሁም መጽሐፉን አይጠሉም:: መጽሐፉ ለሁሉም ተማሪዎች የተደረሰ ይሁን እንጂ ፣ አባሪዎችንና የቋንቋ ዘርፎችን ሁሉ አመጣጥኖ ስላልያዘና ያለአስተማሪ ተማሪን መምራት ስለማይችል ብዙት ይገኝበታል::

10. የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ፣ መማሪያ ክፍሉ ቻቸው ሠሌዳ ያሏቸውና ሥርዓታቸው የተጠበቀ ቢሆንም ተማሪዎች በክፍል ጥበት ተወናንቀዋል::

11. በአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የአማርኛ ትምህርት በልዩ መርጃ መሣሪያና በተለያዩ ዘዴዎች አይቀርብም::

12. በርካታዎቹ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የአማርኛን ትምህርት የሚያግዙ ክበባትን አላቋቋሙም ፣ ወቅታዊ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን በመከታተል ገዝተው አያውቁም::

13. የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች አማርኛን ለመማር የሚፈልጉት፣

- ትምህርቱ በልቦለድ ጽሑፎች ፣ በጋዜጦችና በመጽሔቶች ተደግፎ ሲቀርብ ፣
- ቀኒያዊ ፣ ምሳሌያዊ ፣ ዘይቤያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮች እንዲተ ረጎሙ ለማገዝ ብቻ ሳይሆን በቁምነገር ነገርባቸውና የሰቀቡ ትምህርት እንዳይከብዱ ሆኖ በልዩ ዘዴ ክርባቸውና የሰቀበው ትምህርት እንዳይከብዱ ሆኖ በልዩ ዘዴ ሲቀርብ ፣
- ትምህርቱ በቀልድና በድራማ እንዲሁም በልዩ መርጃ መሣሪያ ተደግፎ ሲቀርብ ነው::

## 5.3 አስተያየት

አጥኚው በጥናቱ ግኝት መሠረት የሚከተሉትን አስተያየቶች ያቀርባል::

አንዳንድ ትምህርቶች የማያስደስቱ ከሚያደርጉት ነገሮች ዋናኛው የተማሪ አንዱ ትምህርት እንዲወደዱ ከሚያደርጉት ነገሮች ዋናዎቹ የተማሪ ዎችን ደረጃና ፍላጎት መጠበቃቸው ናቸው:: በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ

ከሚቀርቡት ርዕሶች ተማሪዎች እንዲተኩርበት የፈለጉት ፣ ልቦለድ ጽሑፎችን ነው:: ስለዚህ የሥርዓተ ትምህርት ባለሙያዎች በዝግጅት ወቅት ልዩ ትኩረት ቢሰጧቸውና ልቦለድ ጽሑፎች ለተለያዩ የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ማስተማሪያ ሆነው ቢቀርቡ ጥሩ ነው:: ምክንያቱም የልቦለድ ታሪክ ስለሚስባቸው ተማሪዎች ለማንበብ ፣ ለማዳመጥና ለመናገር ደስ ይላቸዋል:: በዚህም የማንበብ፣የማዳመጥና የመናገር ክሂሎቻቸውን ያዳብራሉ:: ልቦለድ ጽሑፉን በተወሰነ ገፅ አሳጥሮ በመጻፍ ወይም እሱን የመሰለ ሌላ ልቦለድ ጽሑፍ ፈጥረው እንዲጽፉ በማድረግ የጽሑፍ ክሂሎቻቸውም እንዲዳብር ማድረግ ይቻላል:: በተጨማሪም ሰዋሰዋዊ ትምህርቶችን ማለትም ልዩ ልዩ ቃላትንና ቅጥያዎችን፣ ሐረጎችንና ዓ.ነገሮችን ፣ ስሞችን ፣ ግሶችን ፣ ቅጽሎችን ወዘተ. በልቦለድ ጽሑፎች ማስተማር ይቻላል:: ቅኔያዊ ፣ መሳሌያዊ ፣ ዘይቤያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮችም በልቦለድ ጽሑፉ ውስጥ ሊቀርቡ ይችላሉ:: ስለዚህ ልቦለድን ተማሪዎች እስከ ወደዱት ድረስ ለሁሉም የአማርኛ ቋንቋ ዘርፎች የማስተማሪያ መሣሪያ አድርጎ መጠቀም የበለጠ ውጤት ያስገኛል:: ጥቂት አማርኛን የሚጠሉ ተማሪዎችም "ልቦለድ ያልሆነ ጽሑፍ ስለሚበዛ ነው የጠላነው" ስላሉ ፣ ከላይ እንደተገለፀው ፣ ልቦለድ ጽሑፍ ከተተኮረበት እነዚህ የሚጠሉትም ይወዱታል ማለት ነው::

አብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን ጥሩ ጠባይ ፣ በቂ እውቀትና ሸጋ አቀራረብ ያላቸው ቢሆንም ጥቂቶቹ የተማሪዎችን ፍላጎች ጠብቀው የማያቀርቡ፣ አቀራረባቸውም የማይስብና የማይማርክ፣ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የግል ጥረታቸውን የማያክሉና ለተማሪዎች በቂ የጥያቄ ዕድል የማይሰጡ ናቸው:: በጣም ጥቂቶቹ ደግሞ የሰጡትን የክፍልና የቤት ሥራ የማያርሙ ፣ ሳይዘጋጁ ክፍል የሚገቡ ፣ ተማሪዎችን የሚያንቋሽሹ ቁጡና ተሳዳቢዎች ናቸው:: እነዚህ የተጠቀሱት የመምህራን ድክመቶች ለቋንቋ ትምህርት መጠላት አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ስለሚችሉ በሥራ ላይ ያሉት በሙያ ማሻሻያ ኮርስ ፣ ገና ማሰልጠኛ ውስጥ ያሉት ደግሞ በሚሰጧቸው የሙያ ትምህርቶች አማካይነት ከአንድ የቋንቋ መምህር የሚጠበቁ

ሙያዊ ግዴታዎችና ስለ ተማሪዎች አያያዝ ሥነ ልቦናዊ ዕውቀቶች በቂ ሥልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል:: ስለዚህ ትምህርት ሚንስቴር ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና ፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የሚያሰለጥኑ ኮሌጆች ሁሉ በሥልጠና ላይ ልዩ ትኩረት ቢያደርጉ መልካም ነው:: ይህ ከሆነ በቋንቋውና በትምህርቱ ላይ የሚታየው አዎንታዊ አመለካከት እየጎለበተ ይሄዳል::

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰልቺና አስጠሊታ እንዳይሆን በተገቢው መርጃ መሣሪያዎችና በልዩ ልዩ የማስተማር ዘዴዎች መቀረብ አለበት:: ስለዚህ ት/ቤቶች ለመርጃ መሣሪያዎች ዝግጅት የሚሆኑ ማቴሪያሎችን ማቅረብ ሲኖርባቸው ፣ መምህራን ደግሞ በአግባቡ ሰርተው ሥራ ላይ ማዋል ይኖርባቸዋል::

ከተማሪዎችና፣ በአብዛኛው ከመምህራን በተገኘው መረጃ መሠረት የአሥራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ብዙ ጉድለቶች አሉበት:: ምንባቦቹም ሆኑ የአቀራረብ ስልቶቹ ተማሪዎችን የመሳብ ኃይል የላቸውም:: ደረጃን አልመጠኑም ፣ የቋንቋ ዘርፎችን አመጣጥነው አልያዙም:: ስለዚህ አሁን በሥራ ላይ ያሉት የአሥራ አንደኛና የሌሎችም የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ልቦለድ ጽሑፎችን በርከት አድርገው ፣ የቋንቋ ዘርፎችን አመጣጥነው ፣ ለአቀራረብ በሚያመችና በሚማርክ መልክ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል:: ይህ ከሆነ መጻሕፍቱ ይወደዳሉ ፣ መጻሕፍቱ ከተወደዱ ደግሞ የቋንቋውም ትምህርት ይወደዳል::

አዘጋጆችን በተመለከተ ከሥራው ርቀው ያሉ ጥቂት የቢሮ ባለሙያዎች ብቻ ከሚያዘጋጁት ፣ ልምድና ብቃት ያላቸው መምህራን በልዩ መሥፈርት ተመርጠው ፣ በቂ ጊዜና ባጀት ተመድቦለት ከቢሮ ባለሙያዎችም ጋር እየተወያዩ ቢያዘጋጁ መልካም ነው::

አብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መማሪያ ክፍሎች ከሚገባው በላይ በተማሪዎች የተጨናነቁና መቀመጫም የታጣበት ሁኔታ አለ:: ይህ ደግሞ ለቋንቋ ትምህርት ምቹ አይደለም::

ተማሪዎችን ለመቆጣጠር ፣ የሁሉንም ደብተሮችና ሥራዎች በሚገባ ለማየትና [illegible] ችግር ነው:: ስለዚህ መንግሥትና ሕዝቡ ተረዳድተው የመማሪያ ክፍሎችን ቁጥር መጨመርና በየክፍሉ ያሉት የተማሪዎች ብዛት ከሰልባ እንዳይበልጥ ጥረት ማድረግ / ይህ ከአገሪቱ ሁኔታ አኳያ የተሰጠ አስተያየት እንጂ ፔዳጎጂካል በሆነ መልኩ ከታየ የአንድ ክፍል የተማሪ ብዛት ከአርባ መብለጥ የለበትም::/

ተማሪዎች ሁልጊዜ ለክፍሉ ከተመደበው መጽሐፍ ብቻ ከሚማሩ መምህራን ከተለያዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ወቅታዊ ጉዳዮችን እየፈለጉ በመጨመር ቢያቀርቡ ጥሩ ነው:: ሁልጊዜ አንድ ዓይነት ምግብ ብቻ መመገብ እንደሚሰለች ሁሉ ተማሪዎች በእጃቸው ከያዙት መጽሐፍ ብቻ መማራቸው እንዳያሰለቻቸው ለለውጥ ያህል ማደባለቅና ወቅታዊ ሁኔታዎችን ማሳወቅ ጥሩ ነው:: ይህ ከሆነ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት እየጨመረና እየጎለበተ ይሄዳል::

ት/ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያግዙና የሚያጠናክሩ ክበባትንና ፕሮግራሞችን ማደራጀት ይኖርባቸዋል:: ለምሳሌ የስነ ጽሑፍ ክበብ ፣ የጋዜጠኝነት ክበብ ፣ የድራማ ክበብ ፣ የውይይትና የክርክር ፕሮግራሞች ፣ ወዘተ. በየት/ቤቶች ተቋቁመው በሚገባ ተግባራዊ ቢሆኑ የአማርኛን ትምህርት ማገዝ ብቻ ሳይሆን ትምህርቱም እንዲወደድ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ::

## የቢ መጻሕፍት

Abraham Demoz. 1963. European Loan Words in an Amharic Daily News Paper. Language in Africa. Cambridge;

Alfred, N. Smith. 1972. "The Importance of Attitude in Foreign Language Learning". English Teaching Forum Vol. 10, No. 1, Page 15 - 20.

Allwright, L. 1982. "What Do We Want Teaching Materials For?" ELT Journal Vol. 36, No. 1, Page 5-8.

Anderson Anders, Norrl. 1967. Multilingualism and Attitude: An Explorative Descriptive Study Among Secondary School Students in Ethiopia and Tanzania. Uppsala University.

Azeb Desta. 1982. Elements of General Methods of Teaching. Addis Ababa: Addis Ababa University.

Bender, M.L. et al (eds ) 1976. Language in Ethiopia. London: Oxford University Press.

Bowntree, B. 1974. Educational Technology in Curriculum Development. London: Harper and Row Publishers.

Brumfit, C.J. and Robert, J. 1966. Introduction to Language and Language Teaching. New York: MC-Graw Hill Book Campany.

Cailods, Fled. 1989. The Prospects for Educational Planning. A Workshop Organized IIEP on the Occasion of Its Imperimerie Gauthiervillars.

Carroll, B. John. 1965. "The Contributions of Phychological Theory and Educational Research to the Teaching of Foreign Language ". Modern Language Journals Vol. 49, No. 5, Page 273 - 281.

Chastain Kenneth, 1988. Developing Second Language Skills: Theory and Practice. New York: Harcourt Brace Jovanovich, Publishers.

Coombs, P.H. 1968. The World Educational Crisis. London: Oxford University Press.

Cooper, R. L. 1976. "Government Language Policy " in Bender, M.L. et al ( eds ) 1976. Language in Ethiopia. London: Oxford University Press. Page 187 - 190.

Cunningsworth Alan. 1984. Evaluating and Selecting ELT Teaching Materials. Oxford: Heinmann Educational Books Ltd.

Desalegn Chalchisa. 1995. " Assessment of the Condition of Research in Educational Testing " Proceedings of the National Workshop on Strengthening Educational Research. Institute of Educational Research. Addis Ababa University. Page 239 - 252

Dubin, Frida. 1990. Course Design Programs and Materials for Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

Dubin, Frida and Olshtain, Elite. 1986. Course Design Developing Programs and Materials for Language Learning. Cambridge : Cambridge University Press.

Dunhill. 1964. Discipline in the Classroom. London: University of London Press Ltd.

Dunopal. 1983. Beghing English With Young Children. London: Macmilan Publishers.

ELY, M. Christopher, 1986. " An Analysis of Discomfort, Risktaking, Sociability, and Motivation in the $L_2$ " Language Learning Vol. 36, No. 1, Page 1 - 25.

Ferguson Charles A. 1971. A Sociolinguistic Survey of Language and Attitude in Ethiopia. Washington D.C. Geogge Town University.

Genesee Fred, Rogers Pierre, and Holobow Naomi. 1983. " The Social Psychology of Second Language Learning: Another Point of View ". Language Learning Vol. 33, No. 2, Page 209-224.

Harmer, Jeremy. 1983. The Practice of English Language Teaching. New York: Longman Inc.

Haycraft John. 1978. An Introduction to English Language Teaching. England: Longman Group Ltd.

Herric, J.H. and Others. 1956. From School Program to School Plant. New York: Henry Holt and Campany.

Kitchen, R.D. 1967. " Measuring Students Attitude ". Education for Teaching. Vol. 1 No. 69, Page 75-79.

Klausmeier, H.J. and William Goodwin. 1968. Learning and Human Abilities. New York: Harper and Row Publishers.

Lambert, E. 1972. Language Psychology and Culture. Stanford: Stanford University Press.

Leslau Wolf. 1945. The Influence of Cushitic on the Semetic Language of Ethiopia. ( A Problem of Substratum ) New York: On Microfilm 15/c/7.

Lewis, M. and Hill, J. 1990. Practical Techniques for Language Teaching. London: Commercial Colour Press.

Littlewood, William, 1984. Foreign and Second Language Learning: Language Acquisition Research and Its Implications for the Classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Mackay and Mount Ford ( eds ), 1978. English for Specific Purposes. London: Longman Group Ltd.

Mcnab Christine, 1989. Language Policy and Language Practice: Implementation Dilemmas in Ethiopia Education. Stockholm: Institute of International Education, University of Stockholm.

Medhane H/Giorgis. 1986. The Attitude of 11th Grade Students Towards The Learning of English as a Foreign Language. Graduate Studies Thesis, Addis Ababa University.

Murcia Celee, Marianne ( ed ). 1991. Teaching English as a Second or Foreign Language. Boston: Heinle Publishers.

Payne, David, A. 1992. Measuring and Evaluating Educational Outcomes. New York: Maclnillan Publishing Company.

Peal, E.A. Oliver and Boyd. 1956. The Psychological Basis of Education. London: Edinburgh Tweedale Court.

Pikunas Justin, 1976. Human Development 3rd Edition. New York: Mc Graw-Hill Book Companyl

Pimsleur P. et al. 1962. "Student Factors in Foreign Language Learning." The Modern Language Journals. Vol. 49. No. 4 Page 160 - 170.

Shelden, E. 1987. ELT. Textbooks and Materials: Problems in Evaluation and Development. London: Modern English Publishers.

Sherif, W. Carolyn. 1965. Attitude and Attitude Change: The Social Judgment Involvment Approach. Philadelphia: W. B. Sounders Company.

Spolsky Bernard. 1969. " Attitudinal Aspects of Second Language Learning " Language Learning Vol. 19, No. 3, and 4 Page 271 - 285.

________________. 1989. Conditions for Second Language Learning. Oxford: Oxford University Press.

Stainback, Susan ( ed ). 1980. Educating Children with Sever Maladaptive Behaviours. New York: Grune and Statton Inc.

Stern, H. 1983. Fundamental Concepts of Langugge Teaching. Oxford: Oxford University Press.

Taron, E. and G. Yale. 1989. Focuses on the Language Learning: London: Oxford University Press.

Tidyman, F. 1959. Teaching the Language Arts. New York: Mc Graw -Hill Book Company Inc.

Tsehaye Teferre. 1977. A Socio Linguistic Survey of Language Use and Attitudes Towards Language in Ethiopia: Implication for Language Policy in Education. ( PhD Thesis ) Georg Town University.

Wilga, M, Rivers. 1981. Teaching Foreign Language. Chicago: The University of Chicago Press.

Wlodkowski, J. 1985. Enhancing Adult Motivation to Learn. Sanfrancisco: Josseybass Publishers.

New Incyclopaedia Britannica Vol. 1, 15th Edition 1986. Page 687 - 688.

ዐብተማርያም ማርቆስ፡፡ 1972 ዓ.ም. "የኢትዮጵያ ቋንቋዎች" *አይማስ/ሰተታ ትምህርት/ ቅጽ* 1፡ ቁጥር 2፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የትምህርት ጥናት ምርምር ማዕከል ፤ ከገጽ 23_42፡፡

ብርሃኑ ገብረማርያም፡፡ 1976 ዓ.ም. *ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያሏቸው አመለካከት /Attitude /*፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፤ የቢ.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ

አምሳሉ አክሊሉ፡፡ 1976 ዓ.ም. *አጭር የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ*፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

አነዳናስ አይማሱ፡፡ 1966 ዓ.ም. *አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ የተዘጋጀ*፡፡ አርትስ ፋኩልቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ ቀ.ኃ.ሥ. ዩኒቨርሲቲ፡፡

ዐርቁ በሻዳ፡፡ 1982 ዓ.ም. *የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የማስተማሪያ ቋንቋ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ቢለወጥ በተማሪዎችና በመምህራን ዘንድ ያለው አመለካከት*፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፤ የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፡፡

ደሴ ሙሉዓለም፡፡ 1972 ዓ.ም. *ቋንቋና ትምህርት በኢትዮጵያ*፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፤ ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

አጠቃላይ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ረቂቅ 1985 ዓ.ም. የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡

የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ከዘጠነኛ እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል 1984 ዓ.ም. አዲስ አበባ፡፡

## ሙዳየ ቃላት

| እንግሊዝኛ | አማርኛ |
|---|---|
| 1. Abstract | አጠቃሎ |
| 2. Achievement | ትምህርት መቀበም |
| 3. Acquire | መቀበል |
| 4. Affective | ስሜትነኪ |
| 5. Alpha ($\alpha$) | አልፋ |
| 6. Anova | አናቫ |
| 7. Appendix | አባሪ |
| 8. Aptitude | ጥቀል ሰጩቀት |
| 9. Attitude | አመለካከት |
| 10. Calculation | ስሌት |
| 11. $Chi^2$ | ካይስኩር |
| 12. Cognitive | ገንዛቤያዊ |
| 13. Correlation | ተዟምሯዊነት |
| 14. Discomfort | አለመመቸት |
